## *በቅዱሳት መጻሕፍት ዘገባ*

# በርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

*ዓለሙን ሁሉ ሲያሚግት፣ ቀኝና ግራ ሲከፍል፣ ሲያወዛግብ የኖረ እስካሁን ድረስ ማንም እንደ እርሱ የለም። ይኸው አወዛጋቢነት ዕጣ ክፍሉ መሆኑ ገና ከጧቱ ተነግሮለታል። ለብዙዎች መነሣትና መውደቅ ምክንያት እንደ ሚሆን የናቱን ጡት ጠበቶ ሳይጨርስ ተተንብዮለታል። ይህ ሰው የእልፍ መጻሕፍት ርእስ ነው። የሌላ እልፍ ሙዚቃ ሥራዎቸ ጭብጥ ነው። ስሙም ኢየሱስ ክርስቶስ ይባላል[1]።*

*በብዙ አከራካሪ ጉዳይ ላይ፣ "እኔ ምንተዳዬ" ማለት ይቻላል። ተሚጋቾች ሲጯጯሁ ዳር ቆሞ ጨዋታ ማድመቅም ይቻላል። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ስለትምህርቱ ግን ገለልተኛ መሆን አይቻልም። ወይ ወደዚህ ወይም ወደዚያ መውደቅ ግድ ይኖናል[2]።*

**ሴ**ት አያት የልጅ ልጃቸው በወረቀት ላይ የምትጭረውን በአትኩሮት እየተመለከቱ፣ "የእኔ ልጅ ምን እየሣልሽ ነው?" ሲሉ ይጠይቋታል። ልጅቱም ቆፍጠን ብላ፣ "እግዚአብሔርን" "እግዚአብሔርን እየሣልሁ ነው"

- "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ አንድም ሰው አይቶት አያውቅም፤ እንዴት አንቺ እግዚአብሔርን ትስያለሽ?"
- "ማንም አይቶት እንደማያውቅ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪያችን ነግራናለች። እኔም ይኸው ጉዳይ ስላሳሰበኝ ነው እግዚአብሔርን የምሥለው። አይዞሽ አያቴ፣ ከእኔ ሥዕል በኋላ ሰዎች እግዚአብሔርን ያዩታል"።

**ይ**ህቺ ብላቴና ከቅን ልቡና በመነሣት በመረዳቷ መጠን እግዚአብሔርን በወረቀት ላይ አስፍራ፣ ሰዎች የእግዚአብሔርን ገጽ እንዲያዩ መሻቷ ክፋት ላይኖረው ይችላል። ነገር ግን በርካታ ሰዎች ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርን፣ "በመልካቸው እንደ ምሳሌአቸው" ፈጥረውታል፤ በመፍጠርም ላይ ናቸው። "ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል?" የሚለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ጥያቄ፣ "ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንዲሆንላቸው ይፈልጋሉ?" ወደሚል፣ በዲሞክራስያዊ መንገድ ለሚበየን ሕዝበ ውሳኔ አቅርበውታል። አንዳንድ አስረጆች እንመልከት።

- በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የእንስሳት መብት ተሚጋቾች፣ ኢየሱስ አትክልት ብቻ የሚበላ ሰው እንደ ነበር ያስረዳሉ።
- የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ በመባል የሚታወቀው የሐሰት ትምህርት ኢየሱስ በውስጡ ያለውን መለኮትነት ፈልጎ ያገኘ አስተዋይ ሰው ነው ባይ ናቸው[3]።
- እንስታዊነት (feminists) በመባል የሚታወቀውን ንቅናቄ የሚያራምዱ ሰዎች፣ ኢየሱስ የተባዕት ጾታ ካለው፣ በአንጻሩ ደግሞ አምላክ ከሆነ፣ የወንዶችን የበላይነት ከፍ ስለሚያደርግ ኢየሱስ አምላክ አልነበረም ባዮች ናቸው።
- ሙስሊሞች ኢየሱስ ከነቢይ የማይበልጥ ከዚያም የማያንስ ሰው ነው የሚል አቋም አላቸው።

---

[1] ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የዳ ቪንቺ ኮድ ድርሰነ ጠቢብ ወይስ ድርሳነ ባልቴት?* "መቅድም" ንጉሤ ቡልቻ።

[2] ዝኒ ከማሁ።

[3] በቅርቡ "The Secrete" በሚል ርእስ በCD እና በመጽሐፍ ተዘጋጅቶ፣ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ በከተማዪቱ ውስጥ እየተሠራጨ ነው። በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ ተሾመ ነጋሽ፤ *እስከ መጣ ድረስ* በሚል እንዲሁም ግርማዊ ቡሽ፤ *የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ* በሚል ርእስ ያዘጋጁትን መጻሕፍት ይመለከቷል።



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

- የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ድርጅትና የይሖዋ ምስክሮች በመባል የሚጠሩት የድርጅቱ ተከታዮች ኢየሱስ፣ ይሖዋ አምላክ መጀመሪያ የፈጠረው ፈጣሪ ሲሆን፣ ኢየሱስ ደግሞ ዓለማትን የፈጠረ፣ የተፈጠረ ፈጣሪ ነው ይላሉ:: ይህንንም አስተምህሮ በኅብረ ቀለማት ባሸበረቁ ጽሑፎቻቸው አማካይነት በስፋት ያሠራጫሉ[4]::
- የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን በመባል የሚጠራው ሃይማኖታዊ ድርጅት መምህራን ደግሞ፣ ኢየሱስ አብ ያደረበት ሥጋ ነው የሚል እምነት አላቸው[5]::
- እጅግ ባለጸጋ እንደ ሆነ የሚነገርለት፣ "የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ዘመን ቅዱሳን" (ሞርሞን) በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ ድርጅት፣ እግዚአብሔርም ሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደኛ ሰው የነበሩና ቀስ በቀስ ሥጋና ዐጥንት ያላቸው አማልክት እንደ ሆኑ ያስተምራል::
- የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ጨምሮ የኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ሆኖ በአንድ አካል የተገለጠ የዓለም መድኀኒት ነው የሚል ጽኑ አቋም አላቸው::

## እንግዲያው ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን:— ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ:: እነርሱም:— አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎችም ኤልያስ፣ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት:: እርሱም:— እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆነሁ ትላላችሁ? አላቸው:: ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ:— አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ:: ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ (ማቴዎስ 15÷13-17)::

ኢየሱስ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት፣ "ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል?" ሲል የጠየቀው ጥያቄ፣ እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ተደጋግሞ ይጠየቃል፤ ያኔ የተለየየ መልስ ይቀርብለት እንደ ነበረ ሁሉ ዛሬም የተለያየ እንዲያውም አንዱ ከሌላው ጋር እጅግ የሚቃረን መልስ ይቀርብለታል::

ጥያቄው ይህን ያህል አስቸጋሪ እንዲሁም አወዛጋቢ ከሆነ፣ ጥያቄውን "የሙጥኝ" ማለት አስፈላጊ አይደለም የሚል የመፍትሔ ሐሳብ ሊዘነዘር ይችላል:: ጥያቄውን ለአፍታ እንኳ፣ "ችላ" ማለት የማንችልበት ዐቢይ ምክንያት (1) የኀጢአት ሥርየት የምናገኘው ኢየሱስ ባካሄደው ወጀአዊ ሥራ ብቻ ሳይሆን፣ (2) ይህን ወጀአዊ ሥራ ሊሠራ የሚችለው ማነው? በሚለው መሠረተ ነጥብ ላይ ባለን አቋም ነው:: ለዚህም ነበር ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "'እናንተ ከታች ናችሁ፤ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም:: በኀጢአታችሁ እንደትሞቱ ነግሬአችኋለሁ፤ እኔ እርሱ ነኝ ስላችሁ እኔ እርሱ እንደ ሆንሁ ካላመናችሁ፤ በኀጢአታችሁ ትሞታላችሁ'" (ዮሐንስ 8÷23-24) በማለት የእርሱ የማንነት ጥያቄ ለመሞትም ሆነ የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ሁነኛ

---

[4] ስለዚህ ሃይማኖታዊ ድርጅት ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ፣ *የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን* በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል::

[5] ስለዚህ ሃይማኖታዊ ድርጅት ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ፣ *ሰባልዮሳውያን እንዲሁም ውሃውና ስሙ* በሚል ርእስ ያዘጋጀውን ተከታታይ መጻሕፍት (ቅጽ 1 እና 2) ይመለከቷል::



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

ነገር እንደ ሆነ ያስተማረው:: ለዚህም ነው ለዚህ መሠረታዊ ጥያቄ ያለን መልስ መሠረተ እምነታችንን፣ አስተምህሮአችንን፣ ጸሎታችንን እንዲሁም ከሌሎች ጋር ያለንን መስተጋብር ሙሉ ለሙሉ የሚቀይረው:: በአጠቃላይ የኢየሱስን ማንነት በተመለከተ የሚሰጡት ትንተናዎች በሁለት ጐራ ብቻ የሚፈረጁ ናቸው—ትክክል አልያም ስሕተት፤ ሌላ አማራጭ ሊኖር ከተውኑም አይችልም::

"ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?" ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ አወዛጋቢ የሆነበት ሁነኛ ምክንያት፣ ቅዱሳት መጻሕፍት በርእሰ ጉዳዩ ላይ ያላቸው ትምህርት አሻሚ ስለሆነ ወይም ትምህርቱ ግልጠት ስለሚጐድለው አልያም የተሰጠው ማብራሪያ በቂ ስላልሆነ ወይም ደግሞ በርእሰ ጉዳዩ ላይ አንዳችም ማብራሪያ ስላልቀረበ አይደለም:: ነገር ግን ርእሰ ጉዳዩን ለማጥናት ከመነሣታችን በፊት በርእሰ ጉዳዩ ላይ ያለን ዳራዊ ዕውቀት አዎንታዊ ወይም ደግሞ አሉታዊ የመሆኑ ጉዳይ በድምዳሜያችን ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ በማሳደሩ ጭምር ነው::

ለክርስቶስ የማንነት ጥያቄ የሚሰጡትን የተለያዩ ምልከታዎች ***ከዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሰባት*** ላይ ብቻ እንኳ የሚከተሉትን መረጃዎች እናገኛለን:—

- "ስለ እርሱ በሕዝቡ መካከል ብዙ ጉም ጉምታ ነበር:: አንዳንዶች፣ 'ደግ ሰው ነው' አሉ:: ሌሎች ግን፣ 'የለም፤ ሕዝቡን የሚያስት ነው' አሉ:: ይሁን እንጂ አይሁድን ከመፍራት የተነሣ፣ ስለ እርሱ በግልጽ የተናገረ ማንም አልነበረም" (ዮሐንስ 7÷12-13)::
- "ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ቃሉን ሰምተው፣ 'ይህ ሰው በእርግጥ ነቢዩ ነው' አሉ" (ዮሐንስ 7÷40)::
- "ሌሎችም፣ 'እርሱ ክርስቶስ ነው' አሉ:: ሌሎች ደግሞ እንዲህ አሉ፤ 'ክርስቶስ ከገሊላ እንዴት ሊመጣ ይችላል? መጽሐፍ፣ ክርስቶስ ከዳዊት ዘር፣ ዳዊትም ከኖረበት ከቤተ ልሔም እንደሚመጣ ይናገር የለምን?'" (ዮሐንስ 7÷41-42)::
- "ስለዚህም በኢየሱስ ምክንያት በሕዝቡ መካከል መለያየት ሆነ" (ዮሐንስ 7÷43)::
- "ፈሪሳውያንም እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ እናንተም ተታላችኋል ማለት ነው?" (ዮሐንስ 7÷47)::
- "ለመሆኑ ከባለሥልጣኖችና ከፈሪሳውያን በእርሱ ያመነ አለ?" (ዮሐንስ 7÷48)::

ሰዎች ተመሳሳይ/አንድ ዐይነት መረጃ እየተመለከቱ እጅግ ተቃራኒ ወደ ሆኑ የተለያዩ ድምዳሜዎች ላይ እንዴት ሊደርሱ ይችላሉ የሚለው ጥያቄ በተለይ የፍልስፍና፣ የነገረ መለኮት እንዲሁም የሥነ ልሳን/ቋንቋ ምሁራንን እጅግ የሚያሳስባቸው ርእሰ ጉዳይ ነው:: ለዚህ ችግር (ቢያንስ ልዩነት) ዋነኛ ምክንያት ሰዎች በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ መጠኑ የሚለያይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ግንዛቤ ያላቸው የመሆኑ ጉዳይ ነው:: ይህ ዳራዊ ዕውቀት መቅድመ ልባዊ ቅድመ ግንዛቤ፣ (presupposition) ይባላል:: በዚህ መልኩ ሲታይ ማናችንም ብንሆን ቢያንስ መሠረታዊ በሚባሉ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ትክክለኛም ሆነ ትክክለኛ ያልሆነ ግንዛቤ (በተለያየ መጠን) አለን:: ትምህርተ ዘለቅ፣ "የምንጀምርበት ቦታ የምንጨርስበትን ስፍራ ይወስነዋል"[6] የሚለው አነጋገራቸው፣ መቅድመ ልባዊ/ቅድመ ግንዛቤ በአተያያችን ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት ታሳቢ የሚያደርግ ነው::

"ለመቅድመ ልባዊ መከሠት ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነው?" ለሚለው ጥያቄ በነገረ መለኮት ምሁራን የሚሰጠው ትንታኔ፣ የሰው ልጅ ሙሉ ለሙሉ በኀጢአት የመውደቁ እውነታ

[6] Where a person starts powerfully shapes where he or she finishes)

(1) የአእምሮውን ጉልበት ማሳነሱ ብቻ ሳይሆን፣ (2) ቀና ምልከታውንም (ቢያንስ በተወሰነ ደረጃ) አደብዝዞበታል ባዮች ናቸው::

መቅድመ ልባዌአችን እየባረቀ እንዳያጠፋን፣ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ቃታ የሚጠብቅልን፣ "እምነቴ ወይም አቋሜ በቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃ ምን ያህል ተደግፎአል" የሚለው አካሄድ ነው:: ከዚህ በመቀጠል፣ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት:— *(1)* አምላካዊ ስም አለው፣ *(2)* አምላካዊ ባሕርይ አለው፣ *(3)* አምላካዊ ሥራ አለው፣ *(4)* አምላካዊ ክብር አለው፣ *(5)* አምላካዊ መንበር አለው በሚሉ አምስት ዐቢይ ርእሶች በመክፈል በስፋት ለመነጋገር እንሞክራለን::

# ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊ ስም አለው!

በቅዱሳት መጻሕፍት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ብቻ መጠሪያ በሆኑ አምላካዊ ስሞች መጠራቱ፣ አምላክ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቢሆንም፣ አምላክነቱን የማይቀበሉ የሃይማኖት ተቋማትም ሆኑ ግለሰቦች የሚከተሉትን የሙግት ነጥቦች በማቅረብ፣ አምላክነቱን ለማስተባበል ሙከራ ያደርጋሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ኢየሱስ አምላክ ነው የሚለውን ጉዳይ ቢቀበሉም፣ በአንደንድ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ላይ ያላቸው ግርንቢጥ አተያይ ይህን መሠረተ እምነት ለሚክዱ ሰዎች ጥርጊያ መንገድ ሊጠርግ ስለሚችል፣ ለትምህርታችን ጥሩ መደላድል እንዲሆነን ይህን ጭጋግ አጥርተን እንለፍ:—

1) "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" በመባል የሚታወቀው የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት፣ ኢየሱስ አምላክ ተብሎ መጠራቱ አምላክ መሆኑን አያሳይም፤ ምክንያቱም "እግዚአብሔር" ወይም "አምላክ" (በግሪክ "ቴዎስ" "θεός") የሚለው ቃል ለሰዎች ተሰጥቶ ይገኛል (መዝሙር 82÷1፤ ዘፀአት 7÷1፤ 4÷16):: ይህም የሰዎችን ክቡርነት ይኸውም ከመላእክት ጥቂት ብቻ ማነሳቸውን (መዝሙር 8÷5) የሚያመለክት ነው፣ የሚል አስተምህሮ አለው:: እንዲያውም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት በአንዳንድ ሁኔታ ሰይጠንም ሆነ ኾድ (2ቆሮንቶስ 4÷4፤ ፊልጵስዩስ 3÷19) አምላክ ተብለው ተጠርተዋል፤ አምላክ ተብለው መጠራታቸው ግን አምላክ መሆናቸውን እንደማያሳየው ሁሉ፣ ኢየሱስ አምላክ መባሉ አምላክ መሆኑን የሚያስተምር አይደለም የሚል የሙግት ነጥብ ያቀርባል[7]::

"ሰይጣን፣ መላእክት፣ ኾድ፣ አጋንት ወዘተ አምላክ/አማልክት (θεός) ተብለዋል፣ ስለዚህ ኢየሱስ አምላክ መባሉ አምላክ መሆኑን አያሳይም" የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የሙግት ነጥብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም:: ብሉያትም ሆኑ ሐዲሳት እግዚአብሔር/አምላክ የሚለውን የግሪክ ቃል አምላክን በሚያሳይ መልኩ ብቻ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደረጉ ሲሆን ሰይጣን፣ መላእክት፣ ኾድ፣ አጋንት ወዘተ አምላክ ወይም አማልክት (θεός) የሚለውን ቃል የተጠቀሙት በምፀት (irony) (ለምሳሌ መዝሙር 82÷1-2) ወይም "***እንደ*** እግዚአብሔር" ወይም "በእግዚአብሔር ***ፈንታ***" በማለት ወይም ደግሞ፣ "***የዚህ ዓለም*** አምላክ" የሚል ቅጽል ተቀጽሎባቸው ነው (ዘፀአት 4÷16፤ 7÷1፤ 2ቆሮንቶስ 4÷4)፤ በአንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት ደግሞ አምላክ የሚለውን ቃል የተጠቀሙት

[7] *በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1993), 28. ***ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር*** (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1994), 413.

*የመድብለ አማልክት አምላክያን የሆኑ አረማውያን ናቸው እንጂ እግዚአብሔር፣ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ወይም ደግሞ የእግዚአብሔር ነቢያት አይደሉም* (*ሕዝቅኤል* 32÷21፤ *ዘዳግም* 19÷17)[8]:: *በተለይ ደግሞ በብሉይ ኪዳን ምንባባት* (*መዝሙር* 82÷1:6፤ *መዝሙር* 8÷5፤ *ዘፀአት* 22÷8-9:28) *አምላክ የሚለው ቃል በብዙ ቊጥር አማልክት* (*በዕብራይስጡ "ኤል" ሳይሆን "ኤሎሂም" በግሪኩ "ቴዎስ" ሳይሆን "ቴዎይ"*) *መባሉ እንዲሁም የክፍሉ ዐውድ እውነተኛ አምላክ የሆነውን ጌታ የሚያሳይ ያለመሆኑ እነዚህን አካላት አማልክት እንዳላላቸው አመላካች ነው::*

**2)** *እንደ ኬኔት ሄገንንና ኬኔት ኮፕላንድ ያሉ የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን ደግሞ፣ ሰዎች "አምሳለ መለኮት" ናቸው ወይም አማኞች፣ "ክርስቶስን እንዲመስሉ ተጠርተዋል" ወይም ደግሞ ክርስቲያኖች፣ "የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ ሆነዋል" የሚሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት፣ ሰዎች መለኮት ቀመስ ባሕርይ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው የሚል ትምህርት አላቸው*[9]:: *ይህ ጉዳይ ኢየሱስም አምላክ መባሉ ፍጹም አምላክ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም ለሚለው የአርዮሳውያን አስተሳሰብ ጥርጊያ መንገድ የሚከፍት ነው:: እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት ሰዎች አምላክ ናቸው ወይም አምላክ የመሆን ዐቅም/ጕልበት ተሰጥቶአቸዋል የሚል አስተምህሮ የላቸውም:: ሰዎች፣ "እግዚአብሔርን ይመስላሉ" ወይም "አምሳለ መለኮት ናቸው" ሲባል፣ የእግዚአብሔርን ግብረገባዊ ባሕርይ ተካፋዮች ሆነዋል* (*ዘፍጥረት* 1÷26-27፤ 5÷1፤ *1ቆሮንቶስ* 11÷7፤ *ኤፌሶን* 4÷24፤ *ቈላስይስ* 3÷10) *ማለት ሲሆን፣ "ክርስቶስን መምሰል" ማለት ደግሞ* (1) *የኢየሱስ ክርስቶስን ግብረገባዊ ባሕርይ ተካፋይ መሆን* (*1ዮሐንስ* 3÷2፤ *ሮሜ* 8÷29) (2) *እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በከበረና በማይሞት አካለ ትንሣኤ ከሙታን መነሣትን የሚያመለክት ነው* (*ፊልጵስዩስ* 3÷21፤ *1ቆሮንቶስ* 15÷49)[10]::

**3)** *የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን ደግሞ የተጸውዖ ስም* (*ለምሳሌ ኢየሱስ*) *እንዲሁም የማዕረግ ስም* (*ለምሳሌ አባት/አብ*) *መካከል ልዩነት የሚፈጥረው ትምህርታቸው*[11] *ኢየሱስ አምላክ ተብሎ መጠራቱ አምላክ መሆኑን አያሳይም ለሚለው አርዮሳዊ አስተሳሰብ የተወሰነ ደረጃ ዕገዛ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ቃለ እግዚአብሔር በተጸውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል አንዳችም ልዩነት እንዳማያኖር የተወሰኑ ማስረጃዎችን እንመልከት*:—

- *"ቀናተኛ" የሚለው ስም የእግዚአብሔር ስም እንደ ሆነ ተገልጾአል* (*ዘፀአት* 34÷14)::
- *ድንቅ መካር፣ ኀያል አምላክ፣ የዘላለም አበት፣ የሰላም አለቃ የሚሉት ስያሜዎች የመሲሑ አራት "ስሞች" ናቸው* (*ኢሳይያስ* 9÷6)::
- *"ቅዱስ" የእግዚአብሔር "ስም" ነው* (*ኢሳይያስ* 57÷15)::
- *"አዳኝ" ስም ነው* (*ኢሳይያስ* 63÷16)::
- *"ክርስቶስ" ስም ነው* (*ማቴዎስ* 24÷5 ከ*1ጴጥሮስ* 4÷14 *ጋር ያነጻጽሩ*)::

---

[8] *ተስፋዬ ሮበሌ፤ የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት* (ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር: አዲስ አበባ፣ 1998 ዓ.ም)፤ *ገጽ* 25-32::

[9] Kenneth Hagin, *Zoe: The God-Kind of Life* (Tulsa: Kenneth Hagin Ministries, 1981). Kenneth Copeland, *Our Covenant with God* (Fort Worth: Kenneth Copeland Publications, 1987).

[10] *ተስፋዬ ሮበሌ፤ የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት፤ ገጽ* 25-32::

[11] *ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፤ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አዲስ ልደት፤* (አዲስ አበባ ኢትዮጵያ) *ገጽ* 117::

- *"ክርስቲያን" ስም ነው* (1ጴጥሮስ 4÷16)::
- *"የእግዚአብሔር ቃል" ስም ነው* (*ራእይ* 19÷13)::
- *"የነገሥታት ንጉሥ፣ የጌቶች ጌታ" ስም ነው* (*ራእይ* 19÷13)::

*ለምሳሌ እግዚአብሔር ወይም አምላክ የሚለው ቃል፣ የተጸውዖ ስም ነው ወይስ የማዕረግ ስም የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል:: መጽሐፍ ቅዱስ አምላክ በሚለው ስም ላይ "የእኛ"፣ "የእስራኤል" ወዘተ የሚሉት ቅጽሎች ተቀጽለውበት የሚገኝ ስለሆነ፣ ቃሉ የማዕረግ ስምን ማሳየቱ እሙን ነው:: ነገር ግን እነዚህ ቅጽሎች በሌሉበት ሁኔታ ግን አምላክ/እግዚአብሔር የሚለው ቃል የተጸውዖ ስምን ማመልከቱ የግድ ይሆናል:: ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው፣ "ክርስቶስ" የሚለው ቃል ነው:: በአንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት "መሲሕ" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ክርስቶስ የሚለው የግሪክ ቃል የማዕረግ ስምን በማያሳይ መልኩ ጥቅም ላይ ውሎአል (ለምሳሌ ማቴዎስ* 16÷16፤ *ሉቃስ* 24÷46፤ *ዮሐንስ* 1÷41):: *ነገር ግን በሐዲስ ኪዳን መልእክቶች ውስጥ፣ "ክርስቶስ" የሚለው ቃል በአብዛኛው የተጸውዖ ስምን በሚያመለክት መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል:: ከዚህ የምንማረው ነገር ቅዱሳት መጻሕፍት በተጸውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል አንዳችም ልዩነት እንደማያደርጉ የሚየሳይ ነው*[12]::

**4)** *ምናልባት አንዳንድ ሰዎች ደግሞ፣ "እግዚአብሔር በሚጠራበት ስም የተጠሩ ሰዎች መኖራቸው* (*ለምሳሌ "እረኛ" "ዐለት"*) *ግለሰቦቹ አምላክ በተጠራበት ስያሜ ስለተጠሩ ብቻ አምላክ ይሆናሉ ወይም ይህ ስያሜ አማላክ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ማለት ይቻላል?" የሚል ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ:: የሰው ልጅችም ሆኑ ሌሎች ፍጥረታት፣ አምላክ በተጠራበት ስም ስለተጠሩ ብቻ አምላክ ናቸው ወይም አምላክ ይሆናሉ ማለት ትክክል አይደለም:: የኢየሱስን ጉዳይ ከዚህ የሚለይበት በርካታ ምክንያቶች አሉ:: ይኸውም*:— (1) *ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ በተጠራበት ስም* ***ብቻ*** *የተጠራ ሲሆን፣ በቅዱሳት መጻሕፍት በዚህ ስያሜ የተጠሩ አንዳችም አካላት በሌሉበት ሁኔታ ቃሉ ለኢየሱስ ተሰጥቶ መገኘቱ፣ የኢየሱስን አምላክነት የሚያሳይ ይሆናል:: ለምሳሌ አምላክ/እግዚአብሔር* (*ግሪክ "ቴዎስ"* "θεὸς") *የሚለው ስያሜ ከእግዚአብሔር ውጪ ለሆኑ አካላት ጥቅም ላይ ውሎ እንደማይገኘው ሁሉ*[13]*፣ "አልፋና ዖሜጋ"፣ "መጀመሪያውና መጨረሻው"፣ "የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ" ወዘተ የሚሉት ስሞች ከእግዚአብሔር ውጪ ላሉ አካላት ጥቅም ላይ አልዋሉም:: ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ ክርስቶስን "አዳኝ/መድኀኒት"፣ "ዐለት" ወዘተ እንዳሉ ሁሉ ሰዎችንም "አዳኝ/መድኀኒት"፣ "ዐለት" ያሉበት ሁኔታ አለ:: ኢየሱስ አዳኝ/መድኀኒት ብቻ ሳይሆን፣ እነዚህ ስሞች በአንድ ላይ ኢየሱስን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውለዋል* (*ለምሳሌ*:— *"አምላኬና ጌታዬ"* (*ዮሐንስ* 20÷28) *"አምላካችንና መድኀኒታችን"* (*ቲቶ* 2÷13፤ 2ጴጥሮስ 1÷1) *"ጌታችንና መድኀኒታችን"* (2ጴጥሮስ 1÷11):: *እነዚህ ስሞችም ቢሆኑ በዚህ መልኩ ከእግዚአብሔር ውጪ ለሆኑ አካላት ጥቅም ላይ ውለው አይገኙም*:: (2) *ሐዲሳት ኢየሱስን አምላክ ያሉበት ዐውድ፣ ብሉያት አብን አምላክ ባሉበት ዐውድ መሆኑ፣ ቃሉ የኢየሱስ አምላክነት የሚያስረግጥ ነው ወደሚል ድምዳሜ እንድንደርስ የግድ ይላል:: ለምሳሌ፣*

[12] Robert M. Bowman Jr. and J. Ed Komoszewski, *Putting Jesus in His Place: The Case For The Deity of Christ* (Grand Rapids: Kregel, 2007), 127-28.

[13] ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት* (ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር: አዲስ አበባ፣ 1998 ዓ.ም)፤ ገጽ 25-32::



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

"ጌታ" ማለት አንድ ነገር ሲሆን፣ "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል" ወይም "የጌታ ቀን" የሚሉት ገለጻዎች ግን በብሉያት እግዚአብሔር አብን ለማመልከት ጥቅም ላይ በዋሉበት ትርጉማቸው ለኢየሱስ ክርስቶስ ውለው መገኘታቸው ኢየሱስ ጌታ የተባለው፣ አብ ጌታ በተባለበት ዐውድ እንደ ሆነ እንረዳለን:: (3) ለኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጡ አምላካዊ ***ስሞች*** የኢየሱስ ክርስቶስን **አምላካዊ *ባሕርይ*** (ለምሳሌ:— ዘላለማዊ መሆኑ፣ ሁሉን መቻሉ፣ ሁሉን ማወቁ፣ በሁሉ ባታ መገኘቱ)፣ **አምላካዊ *ሥራ*** (ለምሳሌ:— ሕያዋንንና ግዑዛንን ሁሉ መፍጠሩ፣ የዘላለምን ሕይወት መስጠቱ)፣ **አምላካዊ *ክብር*** (ለምሳሌ:— ስግደትን መቀበሉ፣ ጸሎትን መስማቱ፣ ዝማሬ ማኅሌት መቀበሉ)፣ እንዲሁም **አምላካዊ *መንበር*** (ለምሳሌ:— ከአብ ጋር እኩል መሆኑ፣ በፍጡራን ሁሉ ላይ ገዢ መሆኑ፣ በአብ ቀኝ መቀመጡ)፣ እንዳለው በሚያሳይ መለኩ ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው[14]:: በአጠቃላይ ከዚህ በመቀጠል የምንነጋገርባቸው አምላካዊ ስሞች ለኢየሱስ ተሰጥተው መገኘታቸው የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚያሳይ ነው የሚል የሙግት ነጥብ መሠረት አድርገን ነው ውይይታችንን የምንቀጥለው::

# I. የቴዎስ (θєὸς) ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንታኔ

## ዮሐንስ 1÷1፤ ዮሐንስ 1÷18፤ ዮሐንስ 20÷28፤ ሮሜ 9÷5፤ ሐዋርያት ሥራ 20÷28፤ ቲቶ 2÷13፤ 2ጴጥሮስ 1÷1፤ ዕብራውያን 1÷8፤ 1ዮሐንስ 5÷20-21

**ከዚህ በመቀጠለ ጌታንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "አምላክ"** (ግሪክ **"ቴዎስ"** "θєὸς") **የተባለባቸውን እነዚህን ዘጠኝ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት በስፋት ለመመርመር ሙከራ እናደርጋለን**[15]::

**"ቴዎስ"** (θєὸς) **የሚለው የግሪክ ቃለ በሰብዓ ሊቃናት** (LXX) **ትርጉም ላይ** 2,851 **ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ ያህዌ የሚለውን የእግዚአብሔር ስም ጨምሮ በብሉይ ኪዳን ላይ የሚገኙ የእግዚአብሔር ስሞችን ተክቶአል**[16]:: **በሐዲስ ኪዳን ግሪክም ቃሉ** 1,315 **ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣** 78.4% **የሚሆነው ውስን መስተኣምር ያለበት** (articular) **ሲሆን፣** 21.6% **የሚሆነው ደግሞ ውስን መስተኣምር የሌለው** (anarthrous) **ነው:: "ቴዎስ"** (θєὸς) **የሚለው ነጠላ ቃል** 1,307 **ጊዜ የሚገኝ ሲሆን፣ የብዙ ቊጥር የሚያመለክተው ቴዎይ** (θєοί) **ደግሞ** 8 **ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል**[17]::

---

[14]Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place: The Case For The Deity of Christ*, 129.

[15] **"የቴዎስ ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንታኔ" የሚለው የጥናት በአብዛኛው መሠረት ያደረገው የሚከተሉትን ሁለት መጻሕፍት ነው**:— Murray J. Harris, *Jesus as God: The New Testament Use of Theos in Reference to Jesus* (Grand Rapids: Baker, 1992). Robert M. Bowman Jr., *Jehovah's Witnesses, Jesus Christ, and the Gospel of John* (Grand Rapids: Baker, 1989). **በርእሰ ጒዳዩ ላይ ሰፊ ማብራሪያ የሚፈልጉ ሰዎች እነዚህን መጻሕፍት እንዲያነቡ ይበረታታሉ:: የመጀመሪያው መጽሐፍ ኮይኔ ግሪክን ለተማሩ የነገረ መለኮት ተማሪዎች የተዘጋጀ ሲሆን፣ ሁለተኛው መጽሐፍ ግን ግሪክን የማያውቁ ሰዎች፣ ርእሰ ጒዳዩን በትክክል እንዲረዱት ታስቦ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው፤ ነገር ግን ይህ የ**Robert M. Bowman Jr. **መጽሐፍ ትኵረት የሚያደርገው በዮሐንስ** 1÷1 **እና** 8÷58 **ላይ ብቻ ነው::**

[16] Murray J. Harris, *Jesus as God*, 22-29.

[17] **ዝኒ ከማሁ፤** 31::

ከዚህ በመቀጠል ኢየሱስ አምላክ/እግዚአብሔር ነው የሚሉትን እነዚህን ምንባባት ወደ መመርመሩ እንዝለቅ[18]። በዮሐንስ ወንጌል ቢያንስ ሦስት ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ/እግዚአብሔር ተብሎአል (ዮሐንስ 1÷1:18፤ 20÷28) ቅድሚያ ሰጥተን የምናጠናው እነዚህን ክፍሎች ነው።

## ዮሐንስ 1÷1-18 ዐውዳዊ ትንተና

የዮሐንስ ወንጌል መግቢያ (prologue) በመባል የሚታወቀው ዮሐንስ 1÷1-18 ያለው ክፍል ሲሆን፣ በወንጌሉ የመግቢያ ክፍል ማለትም ቍጥር 1 ላይም ሆነ በመግቢያው ድምዳሜ ማለትም ቍጥር 18 ላይ፣ ኢየሱስ አምላክ/እግዚአብሔር (ግሪክ "ቴዎስ" "θεὸς") መባሉ አምላክነቱን የሚያጸና ነው።

በዘፍጥረት 1÷1 ላይ እና በዮሐንስ 1÷1 ላይ፣ "በመጀመሪያ" የሚለው ቃል በአጋጣሚ የተከሠተ ክሥተት ሳይሆን፣ ዮሐንስ ወንጌሉን ሲጽፍ ታሳቢ ያደረገው ዘፍጥረት አንድን እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ዘፍጥረት አንድንና ዮሐንስ አንድን የሚያመሳስላቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ሁለቱም ክፍሎች ስለ ብርሃንና ስለ ጨለማ ይናገራሉ (ዘፍጥረት 1÷1:3-5፤ ዮሐንስ 1÷3-5:9)። ዮሐንስ ዓለማትን ጨምሮ ፍጥረታት ሕልውናቸውን ያገኙት በቃል አማካይነት እንደ ሆነ ይገልጻል (ቍጥር 3:10)። እነዚህ መረጃዎች ቃል የተባለው ክርስቶስ ፍጥረታት ከመፈጠራቸው በፊት እንደ ነበረ ማሳየታቸው እንዲሁም እርሱ የፍጠረታት ሁሉ መገኛ መሆኑ፣ ኢየሱስ ዘላለማዊና ያልተፈጠረ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። ዘላለማዊ መሆኑ ደግሞ አምላካዊ ባሕርይውን የሚያሳይ ነው። እንዲያውም ዮሐንስ በወንጌሉ መግቢያ ክፍል ማጠናቀቂያ (ቍጥር 12) ላይ ሰዎች፣ "በስሙ እንዲያምኑ" ጥሪ ያቀርባል። እግዚአብሔር አብን እንደምናምነው ኢየሱስንም "እመኑ" የሚለው ጥሪ ኢየሱስ አምላካዊ ***ክብር*** እንዳለው የሚያሳይ ነው።

የቃል ማንነት ግልጽ የሆነው ዮሐንስ፣ "ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከለችንም ዐደረ" (ቍጥር 14 አመት) ባለበት ጊዜ ነው። አማርኛቹ ቅጆች "በመካከላችን ዐደረ" (ግሪክ "ኤኬኖሲን ኢን ሁሞን" "ἐσκήνωσεν ἐν ἡμῖν") ሲሉ የተረጐሙት ቃል በቀሉሙ (ቃል በቃል ሲተረጐም)፣ "ድንኳኑን በእኛ መካከል ደኮነ" የሚል ትርጕም ይኖረዋል። ይህም እግዚአብሔር በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በእስራኤላውያን መካከል ማደሩን (መኖር መጀመሩን) እንዲሁም ሕዝበ እስራኤል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለማድረግ ወደ እርሱ መሄድ እንዳለበት የሚያሳይ ትእምርት ነው። ከድንኳኑ በኋላ የተሠራው ቋሚው የመገናኛ ድንኳን እየታነጸ በነበረበት ወቅት እንኳ፣ ሙሴ ጊዜያዊውን ድንኳኑ ከሰፈሩ ውጪ በመትከሉ ምክንያት እስራኤላውያን

[18] የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ድርጅት አባላት፣ "ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው" የሚሉትን ክፍሎች፣ "ኢየሱስ ራሱ እግዚአብሔር አብ ነው" ወይም "አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው" ለሚለው የድርጅቱ አስተምህሮ ማጽኛ ይጠቀሙባቸዋል። ይህ አስተምህሮ እጅግ የተሳሳተ መሆኑን፣ ተስፋዬ ሮቤሌ፤ ***ውሃውና ስሙ*** እንዲሁም ***ሰባልዮሳውያን*** በሚል ርእስ ያዘጋጀውን ተከታታይ መጻሕፍት (ቅጽ 1 እና 2) ይመለከቷል።



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

ከእግዚአብሔርን ጋር በዚያ ግንኙነት ያደርጉ ነበር (ዘፀአት 33÷7-11)[19]:: በሰፈሩ መካከል የተሠራው የመገናኛ ድንኳን ሲጠናቀቅ፣ "ደመናው የመገናኛውን ድንኳን ሸፈነ፤ የእግዚአብሔርም (የያህዌም) ክብር ማደሪያውን ሞላ" (ዘፀአት 40÷35)::

ዮሐንስ፣ "ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም ዐደረ [ἐσκήνωσεν ἐν ἡμῖν]፤ እኛም ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ ["ፕሌሬስ" "πλήρης"] ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጁን ክብር [δόξαν] አየን" (ቍጥር 14) የሚለው ገለጻው፣ "ደመናው የመገናኛውን ድንኳን ሸፈነ፤ የእግዚአብሔርም (የያህዌም) ክብር ["ዶክሳን" "δόξαν"] ማደሪያውን ሞላ ["ፕሌሬስ" "πλήρης"]" (ዘፀአት 40÷35) ከሚለው ጋር የሚጐዳኝ ምንባብ ነው:: ከመገናኛው ድንኳን በኋላ የታነጸውም ቤተ መቅደስ፣ ይህንኑ ተግባር እንዲፈጽም የተዘጋጀ ነበር (ለምሳሌ መዝሙር 74÷7 "መቅደስህን አቃጥለው አወደሙት፤ የስምህንም ማደሪያ አረከሱ"):: ዮሐንስ በእኛ መካከል ያደረው ቃል፣ "ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጁን ክብር" (ቍጥር 14) እንደ ሆነ ይገልጻል:: ይህ የ"ክብር" ገለጻ ሙሴ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያየውን የእግዚአብሔርን "ክብር" የሚያጣቅስ ነው (ዘፀአት 33÷18):: እግዚአብሔር አምላክ በደመና በመገናኛ ድንኳኑ ላይ ሲወርድ፣ እግዚአብሔር ስለራሱ እንዲህ ይል ነበር፣ "እግዚአብሔር እግዚአብሔር ርኅሩኅና ቸር አምላክ ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩና ታማኝነቱ የበዛ" (ዘፀአት 34÷6):: ዮሐንስ በእርሱ ዘመን የነበሩትን አይሁድ የሚያስደንቃቸው በሁለት መልኩ ነው፤ ይኸውም:— (1) በኢየሱስ ክርሰቶስ አማካይነት የተገለጠው የእግዚአብሔር ርኅራኄ፣ ቸርነት፣ ምሕረት ወዘተ በሙሴ በኩል የተገለጠው እጅግ እንደሚልቅ ይገልጻል:: ዮሐንስ ይህን የሚገልጸው ከሁለት ቍጥሮች በኋላ በቍጥር 17 ላይ ነው፣ "ሕግ በሙሴ በኩል ተሰጥቶ ነበር፤ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መጣ":: (2) ሙሴ ስለ እግዚአብሔር ክብር የተገለጠለት መገለጥ፣ እግዚአብሔር ራሱን በክርስቶስ አማካይነት ለሚገልጠው መገለጥ ጥላ እንደ ሆነ ይገልጻል:: እግዚአብሔር ለሙሴ፣ "ማንም እኔን አይቶ መኖር ስለማይችል" (ዘፀአት 33÷20) የሚለው አንጋገሩ፣ "ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም የለም" (ቍጥር 18ሀ) የሚለውን የሚያጸና ሲሆን፣ "ነገር ግን በአብ ዕቅፍ ያለው አንድያ ልጁ የሆነው አምላክ እርሱ ገለጠው" (ቍጥር 18ለ) የሚለውን የሚያመላክት ነው::

# 1) ዮሐንስ 1÷1 ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንተና

## "'Eν ἀρχῇ ἦν ὁ λόγος, καὶ ὁ λόγος ἦν πρὸς τὸν θεόν, καὶ θεὸς ἦν ὁ λόγος"[20]

- "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ" (**ትርጒም የእኛ**)

[19] ከሰፈሩ ውጪ ስለተተከለው ስለ ጊዜያዊው መገናኝ ድንኳን እንዲሁም በሰፈሩ መካከል ስለተሠራው የመገናኛ ድንኳን የአዲሱ መደበኛ ትርጒም በዘፀአት 33÷7 ላይ የቀረበውን የጥናት መምሪያ ይመለከቷል::

[20] Nestle, E., & McReynolds, P. R. 1997, c1993. *Nestle Aland 27th Edition Greek New Testament with McReynolds English Interlinear*. Includes the Nestle Aland Greek New Testament with morphology, lemmas, glosses, and interlinear translation in modern English.; The Greek New Testament copyright 1998 Deutsche Bibelgesellschaft, D-Stuttgart. Logos Research System: Oak Harbor በዚህ መጽሐፍ የተጠቀምንባቸውን የግሪክ ምንባባት የወሰድነው የወሰድነው ከዚህ መጽሐፍ ነው::

- “ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ፤ ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር፤ ውእቱ ወእግዚአብሔር ውእተ ቃል” (**ልሳነ ግእዝ—ማኅበረ መጽሐፍ ቅዱስ ዘኢትዮጵያ**)
- “አስቀድሞ ቃል ነበረ፡፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡ እግዚአብሔርም ቃል ነበረ” (**የ1879 ትርጉም—ዘ ብሪቲሽ ኤንድ ፎሪን ባይብል ሶሳይቴ**)
- “በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ” (**የ1954 ትርጉም—የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር**)
- “በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ” (**የ1993 አዲሱ መደበኛ ትርጉም—ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር**)
- “ቃል በመጀመሪያ ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ይህም ቃል እግዚአብሔር” ነበረ (**የ1980 አዳስ ትርጉም—ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር**)

*ይህን ክፍል፣ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ሺህ ዓመት ካስተማረችው ትምህርት ጋር በሚጻረር መልኩ የሚያስተምሩ በርካታ የሃይማኖት ድርጅቶች አሉ፡፡ “የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር” በመባል የሚታወቀው “የይሖዋ ምስክሮች” ድርጅት እንዲሁም “የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን” በዚህ ረገድ ቀዳሚ ተጠቃሾች ሊሆኑ ይችላሉ—በተለይ በአገራችን፡፡ የይሖዋ ምስክሮች የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚናገረውን ይህን ክፍል በተቃራኒ መልኩ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ያነሰ ፍጡር ነው ለሚለው ትምህርታቸው ማስደገፊያ ይጠቀሙበታል፡፡ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ፣ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት ናቸው የሚለውን የክፍሉን አስተምህሮ በሚጣረስ መንገድ አብም ወልድም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ለሚለው ትምህርታቸው ማስደገፊያ አዘውትረው ይጠቅሱታል፡፡ እነዚህ የሃይማኖት ድርጅቶች የክፍሉን አስተምህሮ እንደ ገዛ ፈቃዳቸው እንዲተረጒሙት በር የከፈተላቸው፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን የበኵረ ጽሑፋቱን ሰዋስው፣ ታሪክ፣ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽና መቼት ለመተርጐም ፈቃደኛ ያለመሆናቸው እንዲሁም ፈቃደኛ እንሆናለን የሚሉ ከሆነ ደግሞ ኑፋቄአቸው የእንቧይ ካብ ስለሚሆንባቸው ነው፡፡ በርግጥ የክፍሉ ትምህርት ምንድን ነው የሚለው ጒዳይ በትክክል የሚበየነው፣ ክፍሉን በቅርበት በመመርመር ብቻ ስለሆነ፣ ክፍሉን በሰከነ መንገድ እንመርምር፡፡*

*በዚህ ክፍል ውስጥ ሦስት ዐረፍተ ነገሮች ያሉ ሲሆን፣ እያንዳንዱም ዐረፍተ ነገር የምንባቡ ባለቤት ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መሠረታዊ ትምህርት የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ እነዚህን ዐረፍተ ነገሮች ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጻቸውን በተከተለ መንገድ ሰዋስዋዊና ዐውዳዊ ትርጒማቸውን እንተነትናለን*:—

## ሀ. “ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ”
## “’Eν ἀρχῇ ἦν ὁ λόγος,”

“*በመጀመሪያ ቃል ነበረ*”፡፡ “*በመጀመሪያ*” (*ግሪክ “ኢን አርኬ”* “’Eν ἀρχῇ”) *የሚለው ቃል በሰብዓ ሊቃናት ትርጒም* (LXX)[21] *የዘፍጥረት መጽሐፍ መጀመሪያ ላይም እናገኘዋለን፡፡ ትምህርተ ዘለቅ ይህንን ምስስል አዘውትረው የሚጠቅሱበት ዋነኛ ምክንያት ዮሐንስ* 1፥1 *ላይ፣*

---

[21] *በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ አይሁዶች የዕብራይስጡን የብሉይ ኪዳን ቅጅ* (*የተወሰኑ ምንባባቱ አረማይስጥ*) *ወደ ግሪክ ቋንቋ ተተርጒሞአል ይህ ቅጅ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም* (LXX) *በመባል ይጠራል፡፡*

"በመጀመሪያ" (ግሪክ "ኢን አርኬ" "Ἐν ἀρχῇ") የሚለው ቃል ከዘፍጥረት 1፥1 ጋር አንድ ዐይነት ጅማሬን ስለሚያመለክት ነው። የይሖዋ ምስክሮች ይህን መጓደን አጥብቀው ይቃወማሉ፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ከዘፍጥረት 1፥1 በፊት ነበረ የሚባል ከሆነ፣ ከጊዜ ጅማሮ በፊት ነበረ ወደሚለው ድምዳሜ ስለሚያደርስ ነው—ይህ ደግሞ ከድርጅቱ አስተምህሮ ጋር ይጣረሳል። ከዚህም የተነሣ ድርጅቱ በ1984 ዓ.ም ያሳተመው የአዲስ ዓለሚቱ ትርጒም የእንግሊዝኛ ቅጅ (NWT) ዮሐንስ 1፥1 ያጣቀሰው ከዘፍጥረት 1፥1 ጋር ሳይሆን፣ ምሳሌ 8፥22፤ ቈላስይስ 1፥15፤ ራእይ 3፥14 ጋር ነው[22]።

የዘፍጥረት 1፥1 ዐውድና የዮሐንስ 1፥1 ዐውድ መጀመሪያ የሚለው ቃል የጊዜን ጅማሬ የሚያመለክት ነው። በዮሐንስ 1፥1 ላይ ያለው "በመጀመሪያ" በዘፍትረት 1፥1 ላይ ካለው "በመጀመሪያ" ጋር አንድ ለመሆኑ የሁለቱ ክፍሎች ዐውድ አንድ መሆኑ ታላቅ ማስረጃ ነው:—

1. "በመጀመሪያ" የሚለው ቃል በዘፍጥረትም መጽሐፍም ሆነ በዮሐንስ ወንጌል መጀመሪያ ክፍል ላይ ይገኛል።
2. "እግዚአብሔር" (ግሪክ "ሆ ቴዎስ" "ὁ λόγος") የሚለው ቃል በሁለቱም ክፍሎች የመክፈቻ ዐረፍተ ነገር ላይ ይገኛል።
3. ሁለቱም ክፍሎች ስለፍጥረታት ጅማሬ የሚናገሩ ናቸው።
4. "ቃል" (ግሪክ "ሆ ሎጎስ" "ὁ λόγος") የሚለው ቃል፣ በሁለቱም ክፍሎች መግቢያ ላይ ይገኛል።
5. በሁለቱም ክፍሎች ውስጥ የሚከተሉት ቃላት በብዛት ይገኛሉ ተፈጠረ/ፍጥረት (ግሪክ "ኤግኒቶ" "ἐγένετο")፣ ብርሃን (ግሪክ "ፎስ" "φῶς")፣ ጨለማ (ግሪክ "ስኮትያ" "σκοτίᾳ") ወዘተ፣

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ጊዜን እንደ ፈጠረ በግልጽ ማስተማሩ ብቻ ሳይሆን (ዕብራውያን 1፥2፤ 11፥3) ቢግ ባንግ በመባል የሚታወቀውም ሳይንሳዊ ማስረጃ ባታና ጊዜ (time & space) ህልውናቸውን ያገኙት ቊሳዊው ዓለም ሲፈጠር ነው የሚል ትምህርት አለው።

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት፣ ዮሐንስ 1፥1 ከዘፍጥረት 1፥1 ጋር የሚጐደኝ ነው ቢባል እንኳ፣ የአማርኛቹ ትርጒሞች፣ "በ" እንዲሁም "አስቀድሞ" ሲሉ የተረጐሙት መስተዋድድ (ግሪክ "ኢን" "Ἐν") ዓለማት በተፈጠሩበት ጊዜ ኢየሱስ እንደ ተፈጠረ የሚያሳይ ነው የሚል ሙግት አላቸው። ነገር ግን የይሖዋ ምስክሮች ራሳቸው ዓለማት የተፈጠሩት በኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ይቀበላሉ። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ የዓለማት ፈጣሪ ኢየሱስ ዓለማት ከመፈጠራቸው በፊት መኖሩ የግድ ይሆናል። መጠበቂያ ግንብ፣ "ኢን" "Ἐν" የሚለው የግሪክ መስተዋድድ ኢየሱስ ዓለማት በተፈጠሩበት ጊዜ ህልውናውን እንዳገኘ የሚያመለክት ነው የሚለው ትምህርታቸው ስሕተት ነው። ዮሐንስ ይህን ማለት ቢፈልግ ኖሮ "ኢን" ("Ἐν") ከሚለው መስተዋድድ ይልቅ፣ በዮሐንስ አንድ ላይ ተደጋግሞ የቀረበውን "ኤግኒቶ" ("ἐγένετο") (ዮሐንስ 1፥3:6:10:14:17) የሚለውን የግሪክ መስተዋድድ ስለሚጠቀም ክፍሉ፣ "በመጀመሪያ ቃል ***ህልውናውን አገኘ***

[22] *New World Translation of the Holy Scriptures: With References* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1984), 1281. ለዘፍጥረት 1፥1 ማጣቀሻነት ደግሞ ዕብራውያን 1፥10 ጠቅሶአል፤ አስገራሚው ጒዳይ ዕብራውያን 1፥10 የድርጅቱን አስተምህሮ በተቃረነ መልኩ፣ የክርስቶስን ዘላለማዊነት የሚያሳይ ምንባብ መሆኑ ነው።

ተብሎ ይተረጎም ነበር:: ዮሐንስ "ኤግኒቶ" የሚለውን መስተዋድድ ተጠቅሞ ቢሆን ኖሮ የይሖዋ ምስክሮ አስተምህሮ ሚዛን መድፋት ይችል ነበር::

"በመጀመሪያ ቃል *ነበረ*":: የአማርኛ ትርጉሞች፣ "ነበረ" ሲሉ የተረጎሙት ቃል (ግሪክ "ኢን" "ἦν")፣ በኮይኔ ግሪክ ሰዋስው ህልውናው ቀጣይነት እንደ ነበረው (durative/imperfect)[23] የሚያመለክት ነው:: ኢየሱስ ጊዜያት/ዓለማት ከመፈጠራቸው በፊት እንኳን ህልውናው ቀጣይነት የነበረው ከሆነ ደግሞ የመጠበቂያ ግንብ ኢየሱስ ህልውናውን ያገኘው ዓለማት ሲፈጠሩ ነው የሚለው ትምህርቱ ስሕተት ይሆናል::

"የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር" (የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት) ለዮሐንስ 1÷1 ማጣቀሻነት ዘፍጥረት 1÷1 ያልጠቀሰበትን ምክንያት ሲገልጽ፣ በዮሐንስ 1÷1 ላይ "በመጀመሪያ" ከሚለው ቃል ፊት ውስን መስተኣምር ስለሌለ ነው ይላል:: ይህ ግን ስሕተት ነው፤ ምክንያቱም "በመጀመሪያ" ከሚለው ቃል ፊት ውስን መስተኣምር የሌለው በዮሐንስ 1÷1 ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በዘፍጥረት 1÷1 ላይም ነውና::

"የመጠበበቂያ ግንብ ድርጅት" "መጀመሪያ" (ግሪክ "አርኬ" "ἀρχῇ") የጊዜን ጅማሬ የሚያመለክት አይደለም የሚል አስተያየት አለው (ሐዋርያት ሥራ 11÷15፤ ፊልጵስዩስ 4÷15):: ነገር ግን የአንድን ቃል ትርጉም የሚወስነው ዐውዱ እስከ ሆነ ድረስ፣ የዮሐንስ 1÷1 ሆነ የዘፍጥረት 1÷1 ዐውድ የዓለማትን መፈጠር (የጊዜንና የቦታን ጅማሬ) የሚያመለክቱ ስለሆነ ቃሉ የጊዜን ጅማሬ ማመልከቱ አይቀሬ ይሆናል::

ዮሐንስ የጊዜን ጅማሬ የሚያስተምር ከሆነ በአንጻሩ ደግሞ ኢየሱስ (ቃል) ከጊዜ በፊት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ነበረ ማለት፣ ኢየሱስ ዘላለማዊ ነው ማለት ነው:: የይሖዋ ምስክሮች እየካዱ ያሉት ይህን እውነት ነው::

በአጠቃላይ ከዮሐንስ 1÷1 የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር የምንማረው እውነት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ/ጅማሬ የሌለው መሆኑን ነው::

## ለ. "...ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር... "
## "καὶ ὁ λόγος ἦν πρὸς τὸν θεόν"

አሁን ደግሞ፣ "...ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ..." የሚለውን ሁለተኛ ዐረፍተ ነገር እንመልከት:: ከዚህ ዐረፍተ ነገር የምንማረው ቀዳም ነገር ደግሞ፣ ቃል የተባለው ኢየሱስ ፍጥረታት ህልውናቸውን ከማግኘታቸው በፊት ከእግዚአብሔር *ጋር አብሮ* እንደ ነበረ ነው::

---

[23] "ኢን" ἦν durative/imperfect እንደሚያመለክተው ሁሉ፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ነጠላ የሆነ ዐላፊ ክሥተትን (aorist) ሊያሳይ ይችላል:: ነገር ግን ቃሉ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተጠቀሰው በdurative ትርጉሙ ብቻ ነው (ዮሐንስ 1÷1ሀለሐ: 2: 4ሀለ):: A. T. Robertson, *A Grammar of the Greek New Testament in the Light of Historical Research* (Nashville: Broadman Press, 1934), 883.

**ይኸውም ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ የተለየ ማንነት እንዳለው የሚያስተምር ነው**[24]**:: "ጋር"/ "ዘንድ" ተብሎ በአማርኛቹ ቅጆች ላይ የተተረጐመው የግሪክ ቃል (ግሪክ "ፕሮስ"** "πρὸς"**)፣ በእንግሊዝኛቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች ላይ የተተረጐመው** "with" **ተብሎ ሲሆን፣ በግሪኩ ሰዋስው "ጋር"/"ዘንድ" (ግሪክ "ፕሮስ"** "πρὸς"**) የሚለው በተሳቢ ሙያ** (objective case) **በሚቀደምበት ጊዜ መስተጋብርን/ግንኙነትን ያመለክታል**[25]**::**

**በተጨማሪም ዮሐንስ፣ አብና ወልድ የተለያየ ማንነት እንዳላቸው ያሳየው አብን በሚያሳየው በመጀመሪያው "እግዚአሐብሔር" ላይ የተወሰነ መስተኣምር በማኖር** ("τὸν θϵόν") **እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስን በሚያሳየው በሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ላይ ውስን መስተኣምሩን በማግደፍ** ("θϵὸς")[26] **ነው:: አብን በሚያመለክተው "ቴዎስ" ላይ ውስን መስተኣምር እንዳለው ሁሉ**

---

[24] **ትምህርተ ሥላሴ የማይዋጥላቸው እነዚህ መናፍቃን አብና ወልድ የተለያየ ማንነት እንዳላቸው ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ከሁለቱ የተለየ ማንነት እንዳለው ሆኖ በክፍሉ ውስጥ ያልተጠቀሰበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ይጠይቃሉ:: የዚህ ጥያቄ አጭር መልስ፣ ዮሐንስ ለማስተማር የፈለገው ስለ ኢየሱሰ እንጂ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስላልሆነ ነው:: ለምሳሌ ማቴዎስ ኢየሱስ በተቀበረበት ስፍራ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛዪቱ ማርያም እንደ ነበሩ ዘግቦአል (ማቴዎስ** 28÷1) **ነገር ግን ከማርቆስና ከሉቃስ ዘገባ የምንማረው እውነት በመቃብሩ ስፍራ ሁለቱ ብቻ እንዳልነበሩ ነው (ማቴዎስ** 16÷1፤ **ሉቃስ** 24÷10)**:: በአጠቃላይ መንፈስ ቅዱስ በዮሐንስ** 1÷1 **ላይ አልተጠቀሰም ማለት አልነበረም ወይም አካላዊ ህልውና የለውም ማለት አይደለም::**

[25] Arndt, W., Gingrich, F. W., Danker, F. W., & Bauer, W. 1996, c1979. *A Greek-English Lexicon of the New Testament and Other Early Christian Literature: A Translation and Adaption of the Fourth Revised and Augmented Edition of Walter Bauer's Griechisch-deutsches Worterbuch zu den Schrift en des Neuen Testaments und der ubrigen urchristlichen Literatur*. University of Chicago Press: Chicago. 709. **በግሪክ ሰዋስው፣ "ጋር"/"ዘንድ" (ግሪክ "ፕሮስ"** "πρὸς"**) የሚለው ቃል ግንኙነትን የማያሳይ መስተዋድድ ሆኖ ጥቅም ላይ የዋለባቸው በርካታ ምንባባት ያሉ ሲሆን፣ [ለምሳሌ በእንግሊዝኛው መስተዋድድ** "to", "among", "from", "against", "about", "according to", "with regard to", "to the point of", "at the time" **ተብሎአል፤ ይህ የሚሆነውም፣ "ፕሮስ" የሚለውን ቃል ከተሳቢ ሙያ** (objective case) **ውጪ ያሉ ሙያዎች ቀድመውት ሲገኝ ብቻ መሆኑን ግን ልብ ይሏል]፣ ቃሉ በተሳቢ ሙያ** (objective case) **ሲቀደም ግን ከሁለት በላይ የሆኑ አካላትን ግንኙነት እንደሚያመለክት በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ተያይዞ የቀረበውን *አባሪ 1* እንዲሁም የሚከተሉትን የሐዲስ ኪዳን ግሪክ ሰዋስው መጻሕፍት ይመለከቷል**:— Daniel B. Wallace, *Greek Grammar Beyond the Basics: An Exegetical Syntax of the New Testament* (Grand Rapids: Zondervan, 1996). A. T. Robertson, *A Grammar of the Greek New Testament in the Light of Historical Research* (Nashville: Broadman Press, 1934), 883. A. T. Robertson, *Word Pictures in the New Testament* (Nashville: Broadman Press, 1932), 4-5. Murray J. Harris, *Jesus as God: The New Testament Use of Theos in Reference to Jesus* (Grand Rapids: Baker, 1992). **ከላይ የተጠቀሰው ግሪክ-እንግሊዝኛ ላክሲከንን ጨምሮ እነዚህ የግሪክ ሰዋስው መጻሕፍት "ፕሮስ" በተሳቢ ሙያ** (objective case) **ሲቀደም ግንኙነትን እንደሚያመለክት በናሙናነት ከጠቀሷቸው የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ዮሐንስ** 1÷1 **በቀዳሚነት ተጠቅሶ መገኘቱን ልብ ይሏል::**

[26] **አንዳንድ የይሖዋ ምስክሮች አብን በሚያመለክተው ቴዎስ (ቴዎን** θϵόν) **እና ወልድን የሚያመለክተው ቴዎስ (ቴዎስ** θϵὸς) **የሆህያ ልዩነት አለ፤ ይህ የትርጒም ልዩነት ያመጣል የሚል አስተሳሰብ አላቸው:: ይህ ለሐዲስ ኪዳን ግሪክ አንዳችም ዕውቀት ካለመኖር የተነሣ የሚፈጠር ጥያቄ ነው:: ኮይኔ ግሪክ አምስት ዐይነት ሙያዎች** (case) **አሉት** θϵὸς—**ባለቤት ሙያ (ለምሳሌ "እግዚአብሔር ዓለምን ስለወደደ"** "Οὕτως γὰρ ἠγάπησϵν ὁ θϵὸς τὸν κόσμον" **(ዮሐንስ** 3÷16)፣ Θϵέ—**ጥሪ ሙያ (ለምሳሌ "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ"** "Θϵέ μου θϵέ μου, ἱνατί μϵ ἐγκατέλιπϵσ" **(ማቴዎስ** 27÷46)፣ θϵόν—**ተሳቢ ሙያ (ለምሳሌ "በየትኛውም ጊዜ ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድም ሰው የለም"** "θϵὸν οὐδϵὶς ἑώρακϵν πώποτϵ" **(ዮሐንስ** 1÷18)፣ θϵόῦ—**ዘርፍ ሙያ (ለምሳሌ "እነሆ የእግዚአብሔር በግ"** "Ἴδϵ ὁ ἀμνὸς τοῦ θϵοῦ" **(ዮሐንስ** 1÷29)፣ θϵόῳ—**ተቀባይ ሙያ (ለምሳሌ "የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን**

ወልድን በሚያመለክተው ቴዎስ ላይ ውስን መስተኣምር በሚያደርግ ኖሮ፣ አብና ወልድ አንድ አካል እንደ ሆኑ ያሳይ ነበር።

"የይሖዋ ምስክሮች" ቃል የተባለው ኢየሱስ ከአብ ጋር ነበር ተብሎ እርሱ ራሱ ሁሉን ቻይ አምላክ መሆን አይችልም የሚል የሙግት ነጥብ አላቸው[27]። የሥላሴ አማንያንም ቢሆኑ ቃል የተባለው ኢየሱስ እርሱ ራሱ አብ ነው የሚል እምነት የላቸውም። አብ አምላክ በተባለበት ዐውድ ውስጥ ወልድም አምላክ መባሉ የወልድን አምላክነት ያሳያል የሚል ሙግት ነው ያላቸው። በአጠቃላይ ከሁለተኛው ዐረፍተ ነገር በግልጽ የምንማረው እውነት፣ አብና ቃል/ወልድ የተለያየ ማንነት እንዳላቸው ነው።

## ሐ. "...ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል..."
## "καὶ θεὸς ἦν ὁ λόγος"

ወደ ሦስተኛውና ወደ መጨረሻው ዐረፍተ ነገር እንሂድ "...ቃልም እግዚአብሔር ነበረ... "። በአንድ ዐውድ ውስጥ አብ እግዚአብሔር በተባለበት መልኩ ወልድም እግዚአብሔር መባሉ አምላክነቱን ያስረዳል የሚለውን እውነት በርካታ መናፍቃን አይቀበሉም።

አብ እግዚአብሔር በተባለበት መልክ ኢየሱስ እግዚአብሔር መባሉ፣ ኢየሱስን ልክ እንደ አብ አምላክ አያስኘውም የሚሉ ሰዎች የሚያቀርቡት ማስረጃ እንደሚከተለው ነው። አብን በሚያመለክተው እግዚአብሔር በሚለው ቃል ላይ የተወሰነ መስተኣምር ሲኖር ወልድን በሚያመለክተው እግዚአብሔር ላይ የተወሰነ መስተኣምር ያለመኖሩ ወልድን ከአብ ያነሰ አምላክ ነው እንድንል ያደርገናል የሚል ትንተና ነው። ይህ ፍጹም ስሕተት ነው። በግሪክ ሰዋስው በስም ፊት በተለይም "እግዚአብሔር" (ግሪክ "ቴዎስ" "θεὸς") ከሚለው ስም ፊት ውስን መስተኣምር መኖሩም ሆነ ያለመኖሩ የትርጒም ልዩነት አያመጣም። እንዲያውም በመጀመሪያው ቴዎስ ላይ ውስን መስተኣምር እንዳለው ሁሉ በሁለተኛውም ቴዎስ ላይ ውስን መስተኣምር ቢኖር ኖሮ አብ ራሱ ውልድ ነው ወደሚለው ትርጒም ይወስደን ነበር።

በግሪክ ሰዋስው በስም ፊት በተለይም ቴዎስ ከሚለው ስም ፊት ውስን መስተኣምር መኖሩም ሆነ ያለመኖሩ የትርጒም ልዩነት አያመጣም። ለዚህ ቢያንስ አምስት አስረጆችን ማቅረብ ይቻላል:—

1. እግዚአብሔር (ግሪክ "ቴዎስ" "θεὸς") ከሚለው ቃል ፊት ውስን መስተኣምር ሳይኖር ቴዎስ የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለከተባቸው በርካታ ስፍራዎች አሉ። እንዲያውም በሐዲስ ኪዳን ግሪክ ቴዎስ የሚለው ቃል 1,315 ጊዜ ያህል የተጠቀሰ ሲሆን፣ 282 ጊዜ የተጠቀሰው ውስን መስተኣምር ሳይኖረው ነው። በዚያው በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ

---

ለእግዚአብሔር ስጡ" "Τὰ Καίσαρος ἀπόδοτε Καίσαρι καὶ τὰ τοῦ θεοῦ τῷ θεῷ" (ማርቆስ 12÷17) ናቸው። ሙያ በዐረፍተ ነገሩ ውስጥ ቃሉ ያለውን አሰካክ የሚወስን እንጂ ይቃሉን ትርጒም የሚለውጥ አይደለም።

[27] *በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1993), 26-8. *ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1984), 416-17.

**ላይ ብቻ ቴዎስ የሚለው ቃል አራት ጊዜ ያለውስን መስተኣምር፣ እግዚአብሔር አብን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል** (**ዮሐንስ** 1÷6:12:13:18)።

- Ἐγένετο ἄνθρωπος, ἀπεσταλμένος παρὰ ***θεοῦ,*** ὄνομα αὐτῷ Ἰωάννης·

  ***ከእግዚአብሔር*** **የተላከ ዮሐንስ የተባለ አንድ ሰው ነበረ**

  (**ቍጥር** 6)

- ὅσοι δὲ ἔλαβον αὐτόν, ἔδωκεν αὐτοῖς ἐξουσίαν τέκνα ***θεοῦ*** γενέσθαι, τοῖς πιστεύουσιν εἰς τὸ ὄνομα αὐτοῦ,

  **ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን *የእግዚአብሔር* ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው**

  (**ቍጥር** 12)

- οἳ οὐκ ἐξ αἱμάτων οὐδὲ ἐκ θελήματος σαρκὸς οὐδὲ ἐκ θελήματος ἀνδρὸς ἀλλ' ἐκ ***θεοῦ*** ἐγεννήθησαν.

  **እነዚህም *ከእግዚአብሔር* ተወለዱ እንጂ፣ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም**

  (**ቍጥር** 13)

- ***θεὸν*** οὐδεὶς ἑώρακεν πώποτε· μονογενὴς θεὸς ὁ ὢν εἰς τὸν κόλπον τοῦ πατρὸς ἐκεῖνος ἐξηγήσατο.

  **ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም የለም፤ ነገሬ ግን በአብ ዕቅፍ ያለው አንድያ ልጁ የሆነው አምላክ እርሱ ገለጠው**

  (**ቍጥር** 18)

2. **ቴዎስ ከሚለው ቃል ፊት ውስን መስተኣምር እያለ እንኳ ቴዎስ የሚለው ቃል ሰይጣንን የሚያመለክትበት ቦታ አለ** (2**ቆሮንቶስ** 4÷4)።

- ἐν οἷς ***ὁ θεὸς*** τοῦ αἰῶνος τούτου ἐτύφλωσεν τὰ νοήματα τῶν ἀπίστων

  **የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን ሰዎች ልቡና አሳውሮአል**

  (2**ቆሮንቶስ** 4÷4)

3. **በሐዲስ ኪዳን ግሪክ ቴዎስ የሚለው ቃል በተሳቢነት ውሎ ውስን መስተኣምር የሌለው** (anarthrous predicate) **አምስት ጊዜ ብቻ ነው**:: **በአምስቱም ቦታዎች ላይ ቴዎስ የሚለው ቃል የተተረጐመው እግዚአብሔር ተብሎ ነው** (**ማርቆስ** 12÷27፤ **ዮሐንስ** 8÷54፤ **ፊልጵስዩስ** 2÷13፤ **ዕብራውያን** 11÷16፤ **እንዲሁም ሮሜ** 8÷33)።

- οὐκ ἔστιν θεὸς νεκρῶν ἀλλὰ ζώντων· πολὺ πλανᾶσθε.

  **የሕያዋን እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም፤ ብዙ እየተሳሳታችሁ ነው**

  (**ማርቆስ** 12÷27)

- ἔστιν ὁ πατήρ μου ὁ δοξάζων με, ὃν ὑμεῖς λέγετε ὅτι θεὸς ἡμῶν ἐστιν,

  **የሚያከብረኝ ግን እናንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ ነው**

  (**ዮሐንስ** 8÷54)

- θεὸς γάρ ἐστιν ὁ ἐνεργῶν ἐν ὑμῖν καὶ τὸ θέλειν καὶ τὸ ἐνεργεῖν ὑπὲρ τῆς εὐδοκίας.

  **እንደ በጎ ፈቃዱ መፈለግንና ማድረግን በእናንተ ውስጥ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና**

  (**ፊልጵስዩስ** 2÷13)

- διὸ οὐκ ἐπαισχύνεται αὐτοὺς ὁ θεὸς θεὸς ἐπικαλεῖσθαι αὐτῶν·

  *ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ አላፈረም*

(*ዕብራውያን* 11÷16)

- τίς ἐγκαλέσει κατὰ ἐκλεκτῶν θεοῦ; θεὸς ὁ δικαιῶν·

  *እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሰዎች የሚከስ ማነው፤ የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው*

(*ሮሜ* 8÷33)

4. *ቴዎስ የሚለው ቃል ውስን መስተኣምር ተከትሎት እንዲሁም ሳይከተለው በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለባቸው ቦታዎች አሉ። ነገር ግን የውስን መስተኣምር መኖሩም ሆነ ያለመኖሩ የትርጕም ልዩነት አላመጣም* (ለምሳሌ *ዮሐንስ* 3÷2፤ 13÷3፤ *ሮሜ* 1÷21፤ 1*ተሰሎንቄ* 1÷9፤ *ዕብራውያን* 9÷14፤ *ሮሜ* 1÷21፤ 1*ጴጥሮስ* 4÷11-12)።

- Ῥαββί, οἴδαμεν ὅτι ἀπὸ ***θεοῦ*** ἐλήλυθας διδάσκαλος· οὐδεὶς γὰρ δύναται ταῦτα τὰ σημεῖα ποιεῖν ἃ σὺ ποιεῖς, ἐὰν μὴ ᾖ ***ὁ θεὸς*** μετ' αὐτοῦ.

  *ረቢ፤* ***እግዚአብሔር*** ከእርሱ *ጋር* ከሆነ ሰው በቀር አንተ *የምታደርጋቸውን ታምራዊ ምልክቶች ማንም ሊያደርገ ስለማይችል፣* ***ከእግዚአብሔር*** ዘንድ *የመጣህ መምህር እንደ ሆንህ እናውቃለን አለው*

(*ዮሐንስ* 3÷2)

- εἰδὼς ὅτι πάντα ἔδωκεν αὐτῷ ὁ πατὴρ εἰς τὰς χεῖρας καὶ ὅτι ἀπὸ ***θεοῦ*** ἐξῆλθεν καὶ πρὸς ***τὸν θεὸν*** ὑπάγει,

  *አብ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር እንዳደረገለት፣* ***ከእግዚአብሔር*** *እንደ ተላከና ወደ* ***እግዚአብሔርም*** *እንደሚመለስ ዐውቆ*

(*ዮሐንስ* 13÷3)

- διότι γνόντες ***τὸν θεὸν*** οὐχ ὡς ***θεὸν*** ἐδόξασαν

  *እግዚአብሔን ቢያውቁም እንኳ፣ እንደ እግዚአብሔርነቱ አላከበሩትም፤*

(*ሮሜ* 1÷21)

5. *በሐዲስ ኪዳን ግሪክ ቴዎስ የሚለው ነጠላ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው* 1,315 *ጊዜ ነው። ከዚህ ውስጥ ቃሉ ሐሰተኛ አማልክትን ለማመልከት አገልግሎት ላይ የዋለው ስድስት ጊዜ ብቻ ነው፤[ይህ ማለት ሁለት ከመቶ* (2%) *ማለት ነው* (*ሐዋርያት ሥራ* 7÷43፤ 12÷22፤ 28÷6፤ 2*ቆሮንቶስ* 4÷4፤ *ፊልጵስዩስ* 3÷19፤ 2*ተሰሎንቄ* 2÷7)።

***በ**አጠቃላይ ቴዎስ ከሚለው ቃል ፊት የውስን መስተኣምር መኖርም ሆነ ያለመኖር አንዳችም የትርጕም ልዩነት አያስከትልም። ስለዚህ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅትና “የይሖዋ ምስክሮች”* በዮሐንስ 1÷1 *ላይ በሦስተኛው ዐረፍተ ነገር ውስጥ የተጠቀሰውና ኢየሱስን የሚያሳየው* እግዚአብሔር አብን *ከሚያሳየው* እግዚአብሔር *ያነሰ ትርጕም አለው ለማለት የሚያቀርቡት የውስን መስተኣምር ማስረጃ፣ የግሪክ ሰዋስውን አካሄድ በፍጹም ያላገናዘበ ነው*[28]። *አብ*

---

[28] "በቴዎስ" (“θεὸς”) *ፊት ውስን መስተኣምር ሲኖር* (the God) *እንዲሁም ውስን መስተኣምር ከሌለ* (a god) *ተብሎ ይተርጐም የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ሙግት ትክክል ከሆነ ድርጅቱ ትልቅና ትንሽ የሚባሉ ሁለት አማልክትን የሚያመልክ አምላክ አልያም ኢየሱስ ክርስቶስ ከበርካታ አማልክት መካከል የሚገኝ አምላክ ነው ወደሚል ድምዳሜ መውሰዱ የግድ ይሆናል። በስም ፊት ውስን መስተኣምር ከሌለ* (a) *ወይም* (an) *ተብሎ ይተርጐም የሚባል ከሆነ፣ ውስን መስተኣምር የሌላቸው ስሞች በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ ብቻ እንኳ በብዛት የሚገኙ ስለሚገኙ ድርጅቱ ባሳተመው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕም እንዲሁም የግሪክ ኢንተር ሊኒየር ይህን ሕግ ባለመከተሉ ተሳስቶአል ማለት ነው [ለምሳሌ፡—* ζωὴ—a

እግዚአብሔር በተባለበት ዐውድ ውስጥ ኢየሱስም እግዚአብሔር መባሉ፣ አብ ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ ሁሉ ወልድም ፍጹም አምላክ መሆኑን የሚያስረግጥ ነው፡፡

ታዋቂ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" መምህር የሆኑትን ዴቪድ ኬ በርናርድን ጨምሮ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተማሪዎች፣ ሦስተኛው ዐረፍተ ነገር መተርጐም ያለበት፣ "ቃልም እግዚአብሔር ነበር" ተብሎ ሳይሆን፣ "እግዚአብሔርም ቃል ነበር" ተብሎ ነው የሚል ሙግት አላቸው[29]፡፡ ክፍሉ በዚህ መልክ መተርጐም አለበት የሚሉበት የነገረ መለኮት ፋይዳ "እግዚአብሔርም ቃል ነበር" ተብሎ ከተተረጐመ፣ ኢየሱስ አብ ነው የሚለውን የድርጅቱን መሠረተ እምነት የሚያጸናላቸው ስለመሰላቸው እንዲሁም "እግዚአብሔርም ቃል ነበር" ተብሎ ከተተረጐመ፣ ሁለተኛውን ዐረፍተ ነገረ በሚጻረር መልኩ አብና ወልድ ሁለት አካላት መሆናቸውን ያስወግድልናል በሚል ስሑት ቀመር ነው፡፡ ይህ ግን በሁለት ዐቢይ ምክንያት ስሕተት ነው፡፡ ይኸውም፡— (1) ክፍሉ "እግዚአብሔር ቃል ነበር" ተብሎ ቢተረጐምም እንኳ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን እንጂ አብ መሆኑን ሊያመለክት አይችልም፡፡ (2) ክፍሉ "እግዚአብሔር ቃል ነበር" ተብሎ ሳይሆን፣ "ቃልም እግዚአብሔር ነበር ተብሎ" መተርጐም ያለበት ዐቢይ ምክንያት "ቃል" ባለቤት ሙያ (Subjective) "እግዚአብሔር" የሚለው ቃል ደግሞ ተሳቢ ባለቤት ሙያ (Predicate Nominative) ስለሆነ ነው፡፡ (3) እንደ ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር፣ "ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ" ከነበረ ("ሆ ሎጎስ ሂን ፕሮስ ቶን ቴዎን" "ὁ λόγος ἦν πρὸς τὸν θεόν") እርሱ ራሱ ቃል መሆን አይችልም፡፡

በተራ ቍጥር ሁለት ላይ ያለውን የሰዋስው ሙግት በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር አድርገን እንመልከተው፡፡ በሦስተኛው ዐረፍተ ነገር ላይ "እግዚአብሔር" (ግሪክ "ቴዎስ" "θεὸς") እና "ቃል" (ግሪክ "ሎጎስ" "λόγος") የሚሉት ሁለት ስሞች በባለቤት ሙያ ተቀምጠዋል፡፡ እነዚህም ሁለት ስሞች "ነበር" (ግሪክ "ሂን" "ἦν") በሚለው የመሆን ግሥ[30] የተያያዙ ናቸው፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ፣ የትኛው ቃል ባለቤት ሙያ ነው የትኛውስ ቃል ተሳቢ ሙያ ነው የሚለው ጕዳይ እንዴት ሊወሰን ይችላል፡፡ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሓፍት፣ "እግዚአብሔር" (ግሪክ "ቴዎስ" "θεὸς") የሚለው ስም በመጀመሪያ ላይ ስለሚገኝና "ቃል" (ግሪክ "ሎጎስ" "λόγος") የሚለው ስም ደግሞ ከግሡ በኋላ ስለሚገኝ፣ ትርጕሙም ይህንኑ አካሄድ ተከትሎ መቀመጥ አለበት በዮች ናቸው፡፡ አንዳች የነገረ መለኮት ፋይዳ ለማግኘት ሲባል የግሪኩን ሰዋስው በእንግሊዝኛው ሰዋስው ሕግ ለመቃኘት የተደረገ ጥረት እንጂ፣ የግሪክን ሰዋስው አካሄድ የተከተለ አይደለም፡፡ በእንግሊዝኛ ሰዋስው የቃላት ቅደም ተከተል የትርጕም ልዩነት ያመጣል[31]፡፡ የግሪክ ሰዋስው ግን ከዚህ በብዙ የተለየ ነው፡፡

---

life (ቍ 4) θεοῦ— a god (ቍ 6) 'Ιωάννης— a John (ቍ 6) θεὸν— a god (ቍ 18) እነዚህ ስሞች ውስን መስተኣምር በሌለበት ሁኔታ ያልተወሰነ መስተኣምርን የሚያመለክቱት ሳይኖርባቸው የተተረጐሙበት ምክንያት ምንድን ነው?]፡፡

[29] David K. Bernard, *Oneness and Trinity A.D. 100-300: The Doctrine of God in Ancient Christian Writings* (Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1991), 79-80.

[30] verb to be/linking verb/copula.

[31] ለምሳሌ የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ያወዳድሩ፡— 1) You are here. 2) Are you here? 3) Here you are. 1) Abebe hits the car. 2) The car hits Abebe. የቃላቱ ቅደም ተከተል የትርጕም ልዩነት እንዳመጡ ልብ ይሏል፡፡

**እ**ንግዲያው የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት "እግዚአብሔር" (ግሪክ "ቴዎስ" "θεὸς") ይሁን ወይስ "ቃል" (ግሪክ "ሎጎስ" "λόγος") የሚለው ጉዳይ እልባት ሊያገኝ የሚችለው በየትኛው ቃል ላይ ውስን መስተኣምር አለ በሚለው የግሪክ የሰዋስው ሕግ ነው:: "ቃል" ውስን መስተኣምር (ግሪክ "ሆ ሎጎስ" "ὁ λόγος") ያለው ሲሆን፣ "እግዚአብሔር" (ግሪክ "ቴዎስ" "θεὸς") ግን ውስን መስተኣምር የለውም:: ስለዚህ የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ "እግዚአብሔር" ሳይሆን "ቃል" ነው:: ስለዚህ ዐረፍተ ነገሩ መተርጐም ያለበት፣ "እግዚአብሔርም ቃል ነበር" ተብሎ ሳይሆን፣ "ቃልም እግዚአብሔር ነበር" ተብሎ ነው:: ቃሉ በዚህ መልክ መተርጐም አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ የኮይኔ ግሪክ ቋንቋ ምሁራን ከሙሉ ልብ ይስማሙበታል[32]::

**በ**ዚህ አካሄድ፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የነገረ መለኮት፣ "ትምህርተ ዘለቅ" "እግዚአብሔር መንፈስ ነው" ("πνεῦμα ὁ θεός" ዮሐንስ 4÷24) የሚለውን፣ "መንፈስ እግዚአብሔር ነው" ብለው ይተረጒሙልን ይሆናል:: ምናልባትም፣ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" (Ὁ θεὸς ἀγάπη ἐστίν 1ዮሐንስ 4÷16) የሚለውን ክፍል፣ "ፍቅር እግዚአብሔር ነው" እንዲሁም "ቃልም ሥጋ ሆነ" (Καὶ ὁ λόγος σὰρξ ἐγένετο ዮሐንስ 1÷14) የሚለውን፣ "ሥጋም ቃል ሆነ" ብለው ሊተረጒሙልን ይችላሉ:: የቀመሩልን ሰዋስው ይፈቅድላቸዋል!

**ማ**ጠቃለያ የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ኢየሱስ ዘላለማዊ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን፣ ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ኢየሱስ ከአብ የተለየ ማንነት እንዳለው ያስተምራል፤ ሦስተኛው ዐረፍተ ነገር ደግሞ ቃለ የተባለው ኢየሱስ እርሱ ራሱ አምላክ እንደ ሆነ ያስረግጣል:: ዮሐንስ 1÷1 የኢየሱስን ዘላለማዊ መሆኑን፣ ከአብ የተለየ ማንነት ያለው አካል እንደሆነ እንዲሁም እርሱ ራሱ እንደ አብ ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ ያስተምራል::

## 2) ዮሐንስ 1÷18 ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ
## "θεὸν οὐδεὶς ἑώρακεν πώποτε· μονογενὴς θεὸς ὁ ὢν εἰς τὸν κόλπον τοῦ πατρὸς ἐκεῖνος ἐξηγήσατο"

- "እስከ ዛሬ ድረስ እግዚአብሔርን ያየው ማንም የለም፤ ነገር ግን በአብ ዕቅፍ ያለው አንድያ ልጁ የሆነው አምላክ እርሱ ገለጠው" (**(የ1993 አዲሱ መደበኛ ትርጒም—ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር)**
- "እግዚአብሔርን ከቶ ያየው የለም:: አንድ ልጅ ባባቱ ጕን ያለ እርሱ ተናገረበት" **(የ1879 ትርጒም—ዘ ብሪቲሽ ኤንድ ፎሪን ባይብል ሦሳይቴ)**
- "ለእግዚአብሔርሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ አላ ወልድ ዋሕድ ዘሀሎ ውስተ ሕፅነ አብሁ እውቱ ነገረነ" **(ልሳነ ግእዝ—ማኅበረ መጽሐፍ ቅዱስ ዘኢትዮጵያ)**
- "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው" **(የ1954 ትርጒም—የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር)**

[32] Murray J. Harris, *Jesus as God*, 60-61. A. T. Robertson, *Word Pictures in the New Testament* (Nashville: Broadman Press, 1932), 4-5.

- “እግዚአብሔርን ያየው ከቶ ማንም የለም፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ያለው አንድ ልጁ ብቻ ገልጦታል” **(የ1980 አዲስ ትርጒም—ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር)**

በስፋት ልንሞግትበት ካሰብነው የግሪክ ዕደ ክታባት ጋር አብሮ የሚሄደው አዲሱ መደበኛ ትርጒም ነው[33]:: በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ፣ የመጀመሪያው ቴዎስ (θϵὸν) አብን የሚያሳይ ሲሆን፣ ሁለተኛው ቴዎስ (θϵὸς) ግን ወልድን የሚያመለክት ነው::

“ሞኖጌኔስ” (“μονογϵνὴς”) የሚለው የግሪክ ቃል፣ በሐዲስ ኪዳን ግሪክ፣ በሉቃስ ወንጌል ሦስት ጊዜ (7÷12፤ 8÷42፤ 9÷38)፣ በዕብራውያን መልእክት አንድ ጊዜ (11÷17)፣ በዮሐንስ ወንጌል አራት ጊዜ (1÷14:18፤ 3÷16:18)፣ በአንደኛ ዮሐንስ መልእክት አንድ ጊዜ (4÷9)፣ በአጠቃላይ ዘጠኝ ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፣ በተለይ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ቃሉ የተጠቀሰው፣ ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማመልከት ነው:: ይኸውም ኢየሱስ የእግዚአብሔር አንዱና ብቸኛው የባሕርይ ልጅ መሆኑን ለማሳየት ነው::

የአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሞች፣ “ሞኖጌኔስ” (“μονογϵνὴς”) የሚለውን የግሪክ ቃል፣ “አንድ ልጁ” ወይም “አንድያ ልጅ” ሲሉ ነው የተረጐሙት:: “ሞኖጌኔስ” የሚለው የግሪክ ቃል፣ “አንድ ልጁ” ወይም “አንድያ ልጅ” ተብሎ በአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሞች ላይ የተተረጐምበት ዐቢይ ምክንያት ቃሉ፣ “ሞኖስ” (“μοῦνος”/“μῶνος” ማለትም “አንድ”/ “ብቸኛ”/“ነጠላ”) እና “ጊናኦ” (“γϵννάω” ማለትም ልጅ/ተወላጅ) ከሚለው ቃል የተዋቀረ ኅብረ ቃል ነው የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ በተርጓምያኑ ዘንድ ስላደረ ነው::

“ሞኖጌኔስ” የሚለው ጥምር ቃል፣ “ሞኖስ” እና “ጊናኦ” ከሚሉት ቃላት ተዋቅሮ “አንድያ ልጅ” የሚለውን ትርጒም የሚወክል ሳይሆን፣ “ሞኖስ” (“μοῦνος”/“μῶνος” “አንድ”/ “ብቸኛ”/“ነጠላ”) እና “ጊኖስ” (“γένος”[34] ማለትም “ዘር”/“ባሕርይ”/ “ቤተ ሰብ”)፣ ከሚሉት ቃላት የተገኘ፣ “ልዩ ባሕርይ” ወይም “አንድ ዐይነት ባሕርይ” የሚል ትርጒም ወክሎ በተገናኝ የሚነበብ ጥምር ቃል ነው[35]::

---

[33] አስደናቂው ጒዳይ፣ በቅርቡ “የይሖዋ ምስክሮች” በአማርኛ ቋንቋ የተረጐሙት፣ “የአዲሱ ዓለም” ትርጒም ይህን ክፍል፣ “አንድያ ልጁ የሆነው አምላክ” ሲሉ ተርጒመውታል:: ድርጅቱ ይህን ክፍል በዚህ መልኩ እንዲተረጒም ምክንያት የሆነው፣ እጅግ ተኣማኒ የሚባሉ የግሪክ ቅጆች ክፍሉን በዚህ መልክ ስላቀረቡት እንዲሁም የድርጅቱ የእንግሊዝኛ ቅጅ ክፍሉን በዚህ መልክ ስለተረጐመው ነው:: ጥንታዊና ተኣማኒነት ያላቸው የግሪክ ቅጆች ክፍሉን በዚህ መልክ ተርጒመውት ሳለ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ያስተረጐማቸው የአማርኛ ቅጆች ግን “አምላክ” የሚለውን ቃል አግድፈው/አጒድለው ተርጒመዋል:: ይህ ትልቅ ስሕተት ነው:: ይህ ጒዳይ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በሚያሳትማቸው የመጽሐፍ ትርጒሞች ላይ፣ የ1954 ትርጒም ከፍተኛ ተጽእኖ እንዳደረገ የሚያሳይ ነው::

[34] “ጂነስ” የሚለው የላቲን ቃል ከዚህ ቃል የተቀዳ ሲሆን፣ “ጂን” የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ደግሞ ከዚህ የላቲን ቃል የተገኘ ነው::

[35] Arndt, W., Gingrich, F. W., Danker, F. W., & Bauer, W. 1996, c1979. *A Greek-English lexicon of the New Testament and other early Christian literature: A translation and adaption of the fourth revised and augmented edition of Walter Bauer's Griechisch-deutsches Worterbuch zu den Schrift en des Neuen Testaments und der ubrigen urchristlichen Literatur.* (Chicago: University of Chicago Press, 1979), 527. Henry G. Liddell and Robert Scott, comps., *A Greek-English Lexicon,* rev. Henry S. Jones and Roderick McKenzie et al., 9th ed. (Oxford: Oxford University Press, 1940), 1144; James H. Moulton and George Milligan, *The Vocabulary of the Greek New Testament* (reprint, Grand Rapids:



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

**በ**ዚህ ምንባብ ላይ ያሉ የግሪክ ዕደ ክታባት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ይለያያሉ። በርካታ የግሪክ ዕደ ክታባት "አንድ ዐይነት ባሕርይ ያለው ልጅ" ("ሞኖጌኔስ ሁዮስ" "μονογενὴς υἱὸς") የሚሉ ሲሆን፣ እጅግ ጥንታዊና ተአማኒ የሚበሉ የግሪክ ዕደ ክታባት ደግሞ፣ "አንድ ዐይነት ባሕርይ ያለው አምላክ" ("ሞኖጌኔስ ቴዎስ" "μονογενὴς θεὸς") ይላሉ። "የኪንግ ጀምስ ትርጒም" የመጀመሪያውን አካሄድ በመከተሉ ምክንያት እርሱን መሠረት አድርገው የተተረጐሙት የአማርኛ ቅጆች፣ በኪንግ ጀምስ ትርጒም ላይ የሚታየው ችግር ይታይባቸው ዘንድ የግድ ሆኖአል። አዲሱ የኪንግ ጀምስ ትርጒም (NKJV) ይህን ስሕተትቱን አሻሽሎ ቢቀርብም ከዚያ በኋላ የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ያሳተመው የ1980 ትርጒምም ሆነ በኋላ ተሻሽሎ የወጣው ትርጒም ይህን ስሕተት ማረም ያለመቻሉ የሚያስገርም ነው።

**ሁ**ሉም የሐዲስ ኪዳን ግሪክ ሊቃውንት ይህን የኪንግ ጀምስ ትርጒም አመራረጥ ትክክል ነው የሚል እምነት የሌላቸውም ማለት የሚቻል ሲሆን[36] የክርስቶስን አምላክነት አጥብቀው በመቃወማቸው በስፋት የሚታወቁት "የይሖዋ ምስክሮች" እንኳ፣ የአዲስ ዓለሚቱ ትርጒም (NWT) በመባል በሚታወቀው የእንግሊዝኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም[37] እንዲሁም የኢንተር ሊኒየር ትርጒም[38] ላይ፣ "አንድያ ልጅ የሆነው አምላክ" ("ሞኖጌኔስ ቴዎስ" "μονογενὴς θεὸς") የሚሉትን ጥንታዊ የግሪክ ዕደ ክታባትን ተከትለዋል።

**እ**ጅግ ጥንታዊ የሚባሉ ሁለት የፓፒረስ ዕደ ክታባት P[66] እና P[75] እንዲሁም ኮዴክስ ሳይናቲከስ፣ ኮዴክስ ቫቲካነስ እንዲሁም ሌሎች ጥንታውያን የግሪክ ዕደ ክታባት፣ "አንድያ ልጅ የሆነው አምላክ" ("ሞኖጌኔስ ቴዎስ" "μονογενὴς θεὸς") ይላሉ። ከዚህ በተጨማሪ በርካታ የቤተ ክርስቲን አበው ለምሳሌ ቀለሜንጦስ፣ አርጌንስ፣ አውሳብዮስ፣ ባስልዮስ፣ የኒሳው ጎርጎርዮስ፣ ቄርሎስ "አንድያ ልጅ የሆነው አምላክ" ("ሞኖጌኔስ ቴዎስ" "μονογενὴς θεὸς") የሚለውን በጽሑፎቻቸው ውስጥ በቀጥታ ጠቅሰዋል[39]።

**አ**ስገራሚው ጒዳይ አብን የሚያመለክተውም፣ "ቴዎስ" ("ቴዎን" "θεὸν") ሆነ ወልድን የሚያመለክተው "ቴዎስ" ("ቴዎን" "θεὸς") ወስን መስተአምር የሌላቸው መሆኑ ነው። በቊጥር 1 ላይ ውስን መስተአምር ያለበት "ቴዎስ" ("τὸν θεόν") አብን የሚያመለክት ሲሆን፣ ውስን መስተአምር የሌለበት "ቴዎስ" ("θεὸς") ደግሞ ወልድን ያመለክት ነበር። "የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት" በቊጥር 1 ላይ "በቴዎስ ፊት ውስን መስተአምር ያለመኖሩ ወልድ ከአብ ማነሱን ያሳያል" የሚል አስተምህሮ ቢኖረውም፣ በቊጥር 18 ላይ አብን በሚያመለክተው "ቴዎስ" ("θεὸν") ላይ ውስን መስተአምር እንደሌለው እናያለን። ይህ አጭር ቅኝት እንኳ

Eerdmans, 1976), 417. ለዚህ ነው የNew International Version (NIV) ትርጒም "አንዱና ብቸኛው" (one and only) ሲል የተረጐመው።

[36] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place*, 327.

[37] *New World Translation of the Holy Scriptures: With References* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1984).

[38] *The Kingdom Interlinear Translation of the Greek Scriptures* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1985).

[39] Bruce M. Metzger, *A Textual Commentary on the Greek New Testament*, 2nd ed. (Stuttgart: United Bible Societies, 1994), 169-70

*የምንግረው መሠረታዊው ቊም ነገር፣ በቴዎስ ፊት ውስን መስተአምር መኖሩም ሆነ ያለመኖሩ አንጻችም የትርጒም ልዩነት እንደማያመጣ ነው*[40]::

***የ**እግዚአብሔር "አንድያ ልጅ" የሆነው ኢየሱስ ዓለማት ከመፈጠራቸው በፊት አምላክ እንደ ሆነው ሁሉ* (ዮሐንስ 1፥1)*፣ ትስብእት ሆነ አብን ለመተረክ/ለመተንተን* (ἐξηγήσατο) *በመጣበትም ጊዜ አምላክ ነው* (ዮሐንስ 1፥18)::

***የ**ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሓፍት፣ ኢየሱስ ሰው አብ ደግሞ በኢየሱስ ውስጥ ያለ አምላክ ነው የሚል ትምህርት እንዳላቸው ይታወቃል:: "[ኢየሱስ] የመለኮት አካል እንዲሆን የተዘጋጀ ሰው ነው"*[41]*:: "ይህም ከመጀመሪያው በእግዚአብሔር ውስጥ የነገረ የሕይወት ቃል፣ በድንግል ማርያም ማሕፀን ግብቶ ሰው ሆኖ ከተወለደ በኋላ፣ በዚህ [ፍጹም ሰው በሆነው አካል] ውስጥ አብ ተዋሕዶ ተገለጠ"*[42]*:: "አብ በመለኮትነቱ ከወልድ ይበልጣልና ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር በአንድ አካል ስለተዋሐደ ፍጹም አምላክና ሰው እንደ ሆነ ከዚህ...እናገራግጣለን"*[43]*:: ይህ አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው እንዲሁም አብ አምላክ ወልድ ደግሞ አብ የተለበጠበት ወይም የለበሰው ሥጋ ነው የሚለው ትምህርታቸው፣ ከዚህ ክፍል አስተምህሮ ጋር በቀጥታ ይቃረናል:: በዚህ ክፍል አብ አምላክ እንደ ሆነው ሁሉ አብን የተረከው ወልድም አምላክ መሆኑ እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል መግቢያ ክፍል በግልጥ እንደ ተመለከትነው ኢየሱስ የእግዚአብሔር አብ ልጅ እንደ ሆነ ሁሉ* (ዮሐንስ 1፥14:18) *እርሱ ራሱ አምላክ* (ዮሐንስ 1፥1:18) *መሆኑ ይህን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ኑፋቄ ያደርገዋል::*

# 3) ዮሐንስ 20፥28 ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንተና

## "ἀπεκρίθη Θωμᾶς καὶ εἶπεν αὐτῷ, Ὁ κύριός μου καὶ ὁ θεός μου"

- "ቶማስም፣ 'ጌታዬ፤ አምላኬም!' አለው" **(የ1993 *አዲሱ መደበኛ ትርጒም—ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር*)**
- "ቶማስም:— ጌታዬ አምላኬ ብሎ መለሰለት" **(የ1954 *ትርጒም—የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር*)**
- "ወአውሥአ ቶማስ ወይቤሎ እግዚእየ ወአምላክየ" **(*ልሳነ ግእዝ—ማኅበረ መጽሐፍ ቅዱስ ዘኢትዮጵያ*)**
- "ቶማስም መለሰ አለም:: ጌታዬ አምላኬም" **(የ1879 *ትርጒም—ዘ ብሪቲሽ ኤንድ ፎሪን ባይብል ሦሳይቱ*)**

---

[40] *"በቴዎስ" ፊት የውስን መስተአምር መኖርም ሆነ ያለመኖር አንጻችም የትርጒም ልዩነት እንደማያመጣ፣ ኬምብሪጅ ዩኒቨርስቲን ጨምሮ ስመ ጥር የዓለማችን ዩኒቨርስቲዎች በኮይኔ ግሪክ ሰዋስው ላይ የጻፉትን መጻሕፍት መመልከት ይቻላል:: አንድም የሰዋስው መጽሐፍ—ቢያንስ የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊዎች እስከሚያውቁት ድረስ—"በቴዎስ" ፊት ውስን መስተአምር መኖሩም ሆነ ያለመኖሩ አንጻችም የትርጒመ ለውጥ አያስከትልም::*

[41] *ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፤ ኢየሱስን ማን ይሉታል?* (1978) *ገጽ* 12:: *በቅንፍ ያለውን አይጨምርም::*

[42] *ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ* 41::

[43] *ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ* 42::

- “ቶማስም ‘ጌታዬ! አምላኬ!’ ሲል መሰሰት” (**የ1980 አዲስ ትርጒም—ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር**)

**የ**ዮሐንስ ወንጌል 21 ምዕራፎች ያሉት ቢሆንም እንኳ፣ የወንጌሉ የተጻፈበት ዐቢይ ዐላማ የሚገኘው በምዕራፍ 20 የመጨረሻዎቹ ቍጥሮች ላይ ነው:: ቶማስ ኢየሱስን፣ “ጌታዬና አምላኬ” (ቍጥር 28) ሲለው፣ ዮሐንስ የወንጌሉ ቀዳማይ ዐላማ፣ “ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ እንድታምኑ ዘንድ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት እንዲሆራችሁ ይህ ተጽፎአል” (ቍጥር 31) ሲል ወንጌሉን የጻፈበትን ዐላማ ይገልጻል:: በዮሐንስ ወንጌል መግቢያ ክፍል በግልጥ እንደ ተመለከትነው ኢየሱስ የእግዚአብሔር አብ ልጅ እንደ ሆነ ሁሉ (ዮሐንስ 1÷14:18) እርሱ ራሱ አምላክ ነው (ዮሐንስ 1÷1:18)::

**ዮ**ሐንስ 20÷28 በተመለከተ በሊቃውንቱ ዘንድ አንዳችም ክርክር ያለ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ይህ አመለካከት፣ “በግሪክ ቋንቋ ሊቃውንት፣ የግሪክ ቋንቋን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች የሚተረጒሙ ተርጓምያን፣ በሐዲስ ኪዳን የትርጓሜ መጻሕፍት እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓምያን ዘንድ አንዳችም ልዩነት የለም”[44]:: በአጠቃላይ “ቶማስ፣ 'ጌታዬና አምላኬ' ያለው ለአብ ነው የሚሉ ምሁራንን ማግኘት እጅግ አዳጋች ነው”[45]:: ለዚህ ዋነኛው ምክንያት “ቶማስም ጌታዬ አምላኬም ***አለው/ብሎ መለሰለት***” (ቍጥር 28) የሚለው ገለጻ፣ ቶማስ አምላኬና ጌታዬ ያለው ለማን ነው የሚለውን ጒዳይ አሻሚ እንዳይሆን አድርጎታል:: ዮሐንስ ወንጌሉን በዘገበበት ወቅት በዚህ ዐይነት መልክ የግለሰቦችን ንግግር በቀጥታ በመጥቀስ ማቅረቡን በበርካታ ምንባባት ላይ በግልጽ መመልከት እንችላለን (ዮሐንስ 1÷48-50፤ 2÷18-19፤ 3÷3:9-10:27፤ 4÷10:13:17፤ 5÷11፤ 6÷26:29:43፤ 7÷16:21:52፤ 8÷14:39:48፤ 9÷11:20:30:34:36፤ 12÷30፤ 13÷7፤ 14÷23፤ 18÷30፤ 20÷28)[46]:: ይህ ዐይነቱ የአተራረክ ስልት በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተለይ ደግሞ በመጽሐፈ ሳሙኤልና በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ በብዛት የሚገኝ ሲሆን፣ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ግን በሉቃስ 13÷15፤ 17÷20 ላይ ብቻ እንጂ፣ በሌሎቹ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ አይገኝም[47]:: ይህ ደግሞ ቶማስ በቀጥታ ኢየሱስን፣ “ጌታዬና አምላኬ” ብሎ መጥራቱን የሚያመለክት ነው::

**የ**መጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀው የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት፣ ቶማስ፣ ጌታዬ ያለው ለኢየሱስ እንዲሁም አምላኬ ያለው ደግሞ ለአብ ነው የሚል አስተምህሮ አለው[48]:: ይኸውም ቶማስ ኢየሱስ ከሙታን በመነሣቱ ምክንያት

---

[44] Harris, *Jesus as God,* 110.

[45] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place,* 142.

[46] ዝኒ ከማሁ::

[47] ዝኒ ከማሁ፤ 329::

[48] ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ድርጅቱ ይህ አቀራረቡ አላዋጣ ስላለው፣ “ጌታዬ አምላኬ” የሚሉት ቃላት ኢየሱስን የሚያመለክት ነው የሚል አቋም ይዞአል:: ለምሳሌ ***ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር*** በመባል የሚታወቀው የድርጅቱ መጽሐፍ ገጽ 214 ላይ እንዲህ ይላል፣ “ቶማስ ሊናገር የፈለገው ኢየሱስ፣ አምላክ መሆኑን ከነበረ፣ 'አምላኬ' ብሎ መጥራቱ ***የሚያከራክርበት ምንም ምክንያት የለም***”:: ይህ የአስተምህሮ ለውጥ ድርጅቱ ኢየሱስ አምላክ ነው እንዲል ያደረገው ሳይሆን፣ አላዋጣ ያለውን ትንተና በአዲስ ትንተና ለመቀየር ያደረገው ጥረት ብቻ ነው:: አዲሱ ትንተና ቶማስ ኢየሱስን፣ “ጌታዬና አምላኬ” ማለቱ የኢየሱስን አምላክነት እንደማያሳይ በዚህ መልኩ ይገልጻል፣ “ኢየሱስ ራሱ ከመዝሙር መጽሐፍ ጠቅሶ ኀያላን ሰዎችና ፈራጆች፣ አማልክት እንደ ተባሉ ከገለጸው ጋር ይስማማል የሐ. 10÷34:35፤ መዝ. 82÷1-6” (ገጽ 214):: በዮሐንስ 20÷17 ላይ ኢየሱስ ሰው በመሆኑ ምክንያት አብ የኢየሱስ አምላክ ተብሏል፤ ነገር ግን ቶማስ በዚያው ምዕራፍ ላይ ኢየሱስን አምላኬ ማለቱ ቍጥር 20



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

በመደነቅ ወደ አብ "አምላኬ" ብሎ በመጮኽ ኢየሱስን፣ "ጌታዬ እንዳለው" የሚገልጽ ነው ባይ ነው[49]:: ይህ ትንተና ግን የክፍሉን ዐውዳዊ ትርጉምና ታሪካዊ ዳራ የተከተለ አይደለም:—

1. "ኢየሱስ ቶማስን...አለው/ብሎ መለሰለት" እንዲሁም "ቶማስም ኢየሱስን፣ ...አለው/ብሎ መለሰለት" የሚሉት ገለጻዎች ንግግሩ በሁለቱ መካከል ብቻ እንደ ተካሄደ የሚያሳይ እንጂ፣ ቶማስ በመደነቅ ወደ አብ መጮኹን የሚያሳይ አይደለም[50]::
2. በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ አይሁድ፣ የእግዚአብሔርን ስም በዚህ መልኩ በመደነቅ አይጠሩም[51]::
3. በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሰዎች እግዚአብሔር አብን በዚህ መልክ ጠርተውታል [ለምሳሌ መዝሙር 35÷23 ይህ ክፍል "ጌታዬና አምላኬ" ("ሆ ኩርዮስ ሙ ካይ ሆ ቴዎስ ሙ" "Ὁ κύριός μου καὶ ὁ θεός μου") የሚሉት ቃላት የቦታ ለውጥ በማድረግ፣ "አምላኬና ጌታዬ" ("ሆ ቴዎስ ሙ ካይ ሆ ኩርዮስ ሙ" "ὁ θεός μου καὶ ὁ κύριός μου") ከማለታቸው በስተቀር የዐረፍተ ነገሩ ዐወቃቀር አንድ ነው:: በተጨማሪ ዮሐንስ 20÷28 ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያነጻጽሯል መዝሙር 5÷2፤ 84÷3]::
4. በቅዱሳት መጻሕፍት "ጌታዬና አምላኬ" የሚሉት ስሞች በጥምረት የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ብቻ የሚያመለክቱ መሆናቸው እንዲሁም ኢየሱስ በዚህ ስም መጠራቱ ኢየሱስም ልክ እንደ አብ አምላክ መሆኑን የሚያሳይ ነው::

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ቶማስ ኢየሱስን ጌታዬና አምላኬ ብሎ አልጠራውም፤ እንደዚያ ለመጥራት ፈልጎ ቢሆን ኖሮ፣ በባለቤት ሙያ (nominative case) ሳይሆን፣ በጥሪ ሙያ (vocative case) "ጌታዬና አምላኬ" ይል ነበር የሚል ሙግት አላቸው:: ይህ ሙግት ሁለት መሠረታዊ ችግሮች አሉበት፤ ይኸውም:— (1) ከላይ የተመለከትናቸው የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎች፣ ይህ የሰዋስው ትንተና ስሕተት እንደ ሆነ ያሳያሉ:: (2) በቅዱሳት መጻሕፍት "ጌታ" የሚለውን ቃል በጥሪ ሙያ መጥራት የተለመደ ቢሆንም፣ አምላክ የሚለውን ቃል ግን በጥሪ ሙያ መጥራት የተለመደ አይደለም:: ይህ ዐይነቱ አጠራር በብሉያት ይኸውም በመሳፍንት፣ በሕዝቅኤልና በነገሥት መጻሕፍት ላይ (መሳፍንት 16÷28፤ 21÷3፤ 2ነገሥት 7÷25፤ ሕዝቅኤል 4÷14) ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በማቴዎስ 27÷46 ላይ ብቻ ይገኛል:: አምላክ የሚለውን ስም በባለቤት ሙያ መጥራት የተለመደ ነው:: ለምሳሌ በግሪኩ የብሉይ ኪዳን ቅጅ (ሰብዓ ሊቃናት ትርጉም LXX) በመጽሐፈ መዝሙር ላይ ብቻ አምላክ ("ቴዎስ" "θεός") የሚለው ስያሜ በባለቤት ሙያ በመቶዎች የሚቈጠሩ ቦታዎች ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በሐዲስ ኪዳንም ውስጥ ተደጋግሞ ይገኛል (ለምሳሌ ማርቆስ 15÷34፤ ሉቃስ 18÷11:13)[52]::

በዮሐንስ 1÷1 ላይ አብን የሚያመለክተው "ቴዎስ" ውስን መስተአምር ያለው ሲሆን፣ ወልድን የሚያመለክተው ደግሞ ውስን መስተአምር የለውም፤ በዮሐንስ 1÷18 ደግሞ አብን የሚያመለክተውም ሆነ ወልድን የሚያመለክቱት ቴዎሶች ውስን መስተአምር የላቸውም፤ በዮሐንስ 20÷17 ላይ አብን በሚያመለክተው ቴዎስ ፊት ውስን መስተአምር የሌለ ሲሆን፣

---

ቍጥር 17 በታየበት መልኩ የማይታይበት ምክንያት ምንድን ነው? አብ፣ ወልድ ሰው በመሆኑ ምክንያት የወልድ አምላኩ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ወልድም የቶማስ አምላኩ ነው፤ ለቶማስ አምላኩ ከሆነ ደግሞ ለእኛ አምላካችን የማይሆንበት ምክንያት አይኖርም::

49 *በሥላሴ ማመን ይገባሃል?* ገጽ 29::

50 ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፤*

51 ዝኒ ከማሁ::

52 Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place,* 143.

ቶማስ ኢየሱስን "አምላኬ" ባለበት ስፍራ ደግሞ ውስን መስተአምር አለው፤ ይህ በቴዎስ ፊት ውስን መስተአምር መኖርም ሆነ ያለመኖር አንዳችም የትርጒም ልዩነት አያመጣም የሚለውን ጒዳይ የሚያጠናክር ነው::

ቶማስ ኢየሱስን፣ "ጌታዬና አምላኬ" ማለቱ ኢየሱስ አብም ወልድም እንደ ሆነ (አብና ወልድ አንድ አካል መሆናቸውን) ለማሳየት ነው የሚል ሙግት በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ዘንድ እንደሚቀርብ ይታወቃል:: ነገረ ግን በዚሁ ዐውድ ውስጥ ኢየሱስ አብን፣ "አምላኬ" ብሎ እንደ ጠራው ሁሉ (ዮሐንስ 20÷17) ቶማስም ኢየሱስን፣ "ጌታዬና አምላኬ" (ዮሐንስ 20÷28) ማለቱ ኢየሱስ ከአብ የተለየ እንደ ሆነ ነገር ግን፣ እርሱ ራሱ ልክ እንደ አብ አምላክ መሆኑን የሚያስረግጥ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ በዮሐንስ ወንጌል መግቢያ ክፍል በግልጥ እንደ ተመለከትነው ኢየሱስ የእግዚአብሔር አብ ልጅ እንደ ሆነ ሁሉ (ዮሐንስ 1÷14:18) እርሱ ራሱ አምላክ (ዮሐንስ 1÷1:18) መሆኑ ከአብ የተለየ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ ራሱ እንደ አብ አምላክ መሆኑን የሚያስረግጥ ነው::

ሐዋርያው ዮሐንስ፣ ተጠራጣሪ የነበረው የጌታ ደቀ መዝሙር ኢየሱስን፣ "ጌታዬና አምላኬ" እንዳለው ሁሉ ይህን ወንጌል የሚያነቡ ሰዎች እንደ ቶማስ ኢየሱስን፣ "ጌታዬና አምላኬ" እንዲሉት ይፈልጋል:: ኢየሱስም ቶማስ "ጌታዬና አምላኬ" በማለቱ ምክንያት ሲገሥጸው ሳይሆን፣ እርሱ በማየት ወደዚህ የእምነት ድምዳሜ ላይ እንደ ደረሰ ሁሉ፣ እርሱ ያየውን ክሥተት ሳያዩ ኢየሱስን፣ "ጌታዬና አምላኬ" የሚሉ ሰዎች ብፁዓን ናቸው::

ሐዋርያው ዮሐንስ የወንጌሉ ተደራስያን ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ እንዲያምኑ ጥሪ ሲያቀርብ (ዮሐንስ 20÷30-31) "ጌታ" የሚለው የዮሐንስ ንግግር፣ ኢየሱስ "ጌታዬና አምላኬ" (ዮሐንስ 20÷28) እንድንለው ታሳቢ ያደረገ ነው:: በመግቢያው ላይ ዮሐንስ ኢየሱስን አምላክ (ዮሐንስ 1÷1:18) እንዳለው ሁሉ የአምላክም ልጅ (ዮሐንስ 1÷14:18) ብሎታል::

በአጠቃላይ በዮሐንስ ወንጌል የመግቢያ ክፍል፣ ኢየሱስ አምላክ (ዮሐንስ 1÷1:18) እንደ ተባለው ሁሉ በዮሐንስ ወንጌል የመልእክቱ ቀዳማይ ዐላማ እንዲሁም የመልእክቱ ማሳረጊያ በሆነው ቦታ ላይ ኢየሱስ አምላክ መባሉ (ዮሐንስ 20÷28) አምላክ መሆኑን የሚያሳይ ነው:: ኢየሱስ በቅድመ ትስብእት አምላክ እንደ ሆነው ሁሉ (ዮሐንስ 1÷1) ትስብእት በሆነም ጊዜ እንዲሁም በድኅረ ትንሣኤ ሕይወቱ አምላክ ነው (ዮሐንስ 20÷28)[53]:: ዮሐንስ የኢየሱስ አምላክነት የክርስትና ሃይማኖት ታሪካዊና ሃይማኖታዊ መሠረት እንደ ሆነ ገልጾአል የሚለው የምሁራን አስተያየት ከዚህና ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ካላቸው ምንባባት የመነጨ ምሁራዊ ድምዳሜ ነው::

## 4) ሐዋርያት ሥራ 20÷28 ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንተና

## "ποιμαίνειν τὴν ἐκκλησίαν τοῦ θεοῦ, ἣν περιεποιήσατο διὰ τοῦ αἵματος τοῦ ἰδίου"

[53] Murray J. Harris, *3 Crucial Questions About Jesus* (Grand Rapids: Baker, 1994), 98-99

- “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ” **(የ1993 አዲሱ መደበኛ ትርጒም—ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር)**
- “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ” **(የ1954 ትርጒም—የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር)**
- “ከመ ትርዐዩ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንተ አጥረያ በደሙ” **(ልሳነ ግእዝ—ማኅበረ መጽሐፍ ቅዱስ ዘኢትዮጵያ)**
- “የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ እርሱ በደሙ የዋጃትን” **(የ1879 ትርጒም—ዘ ብሪቲሽ ኤንድ ፎሪን ባይብል ሦሳይቲ)**
- “ጌታ በገዛ ደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ” **(የ1980 አዲስ ትርጒም—ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር)**

**አዲሱ መደበኛ ትርጒም፣** 1954 **ትርጒምና** 1879 **ትርጒም ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የዋጃት “እግዚአብሔር” ሲሉ፣** 1980 **ትርጒም ግን “ጌታ” ይላል። ልክ እንደዚሁ ጥንታዊና ተአማኒ የሆኑ የግሪክ ዕደ ክታባት፣ “እግዚአብሔር”** (“**ቶ ቴዉ**” “τοῦ θεοῦ”) **እና “ጌታ”** (“**ኩርዩ**” “κυρίου”) **የሚል ልዩነት አላቸው። በአማርኛ ትርጒሞች ላይ የተንጸባረቀውም ልዩነት፣ በግሪክ ዕደ ክታባት ላይ የሚታየው ይህ ልዩነት ነው። ነገር ግን እንደ ጥንታውያን የግሪክ ዕደ ክታባት “እግዚአብሔር”** (“**ቶ ቴዉ**” “τοῦ θεοῦ”) **እና “ጌታ”** (“**ኩርዩ**” “κυρίου”) **በሚሉት ቃላት ላይ ልዩነት ቢኖርም እንደ ግእዙ ትርጒም “ክርስቶስ” የሚል ግን አንዳችም የግሪክ ዕደ ክታብ የለም። ጥቂት ቍጥር ያላቸው ጥንታውያን ቅጆች ደግሞ፣ “የጌታ እግዚአብሔር”** (“**ኩርዩ ቴዉ**” “κυρίου θεοῦ”) **ቤተ ክርስቲያን ይላሉ።**

**እጅግ በርካታ የግሪክና የምንባባዊ ሒያሴ ምሁራን፣ “እግዚአብሔር”** (“**ቶ ቴዉ**” “τοῦ θεοῦ”) **የሚለው ይበልጥ ተአማኒ ነው የሚሉ ሲሆን**[54]**፣ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የማይቀበሉት የይሖዋ ምስክሮች ራሳቸው፣ የአዲስ ዓለሚቱ ትርጒም**[55] **እንዲሁም ድርጅቱ ባዘጋጀው የኢንተር ሊኒየር ትርጒም**[56] **ላይ፣ “እግዚአብሔር”** (“**ቶ ቴዉ**” “τοῦ θεοῦ”) **የሚለውን አካሄድ ተከትለዋል።**

**በርካታ ሊቃውንት “እግዚአብሔር”** (“**ቶ ቴዉ**” “τοῦ θεοῦ”) **የሚለውን አካሄድ የተከተሉበት ዐቢይ ምክንያት እንደ ኮዴክስ ሳይናቲከስና እንደ ኮዴክስ ቫቲካነስ ያሉ ጥንታዊና ተአማኒ የሆኑ የግሪክ ዕደ ክታባት እንዲሁም እንደ አትናቴዎስ፣ ባስልዩስ፣ ኢጲፋኒዮስ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቄርሎስ፣ አምብሮስ ወዘተ ያሉ የቤተ ክርስቲያን አበው ይህን ክፍል ጠቅሰው**

---

[54] የሐዲስ ኪዳን ግሪክና የምንባባዊ ሒያሴ ሊቃውንት፣ "ቴዎስ" እጅግ ተአማኒ የሆነ ቃል እንደ ሆነ ያስረዳሉ። ይኸውም "የእግዚአብሔር ደም" የሚለው ስያሜ በርካታ የግሪክ ቅዱሳት መጻሕፍት ገልባጮች ትክክለኛ አስተምህሮ መስሎ ስላልታያቸው፣ "እግዚአብሔር" የሚለውን ቃል "ጌታ" ብለው እንደ ተኩት ይገመታል። ለምሳሌ የሚከተሉትን መጻሕፍት ይመለከቷል:— Metzger, *Textual Commentary on the New Testament*, 425-27; Harris, *Jesus as God*, 134-36.

[55] *New World Translation of the Holy Scriptures: With References* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1984).

[56] *The Kingdom Interlinear Translation of the Greek Scriptures* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1985).

በሚጽፉባቸው ጊዜያት ሁሉ፣ "እግዚአብሔር" ("ቶ ቴዉ" "τοῦ θεοῦ") የሚለውን ቃል ስለተጠቀሙ ነው።

"እግዚአብሔር" ("ቶ ቴዉ" "τοῦ θεοῦ") የሚለው ቃል አብን የሚያመለክት ነው ወይስ ወልድን የሚለው ጉዳይ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የመስኩን ምሁራን ያወዛግባል። "እግዚአብሔር" የሚለውን አማራጭ ትርጉም የተከተሉ የአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች፣ "እግዚአብሔር" የሚለው ቃል ወልድን በሚያሳይ መልኩ ነው ያቀረቡት[57]። የእንግሊዝኞቹ ቅጆች ግን በሁለት ዐቢይ ጐራ ሊፈረጁ ይችላሉ፤ ይኸውም:—

- "በደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን"[58]
- "በገዛ ልጁ ደም የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን"[59]

ምንም እንኳ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተተረጐሙ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ልክ እንደ አማርኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የመጀመሪያውን አካሄድ ቢከተሉም፣ ሁለተኛውን አካሄድ የተከተሉ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ይህን አካሄድ እንዲከተሉ ያደረጋቸው "ደም" እና "እግዚአብሔር" የሚሉት ቃላት አብረው ሊሄዱ አይችሉም የሚለውን ግምት ተሳቢ በማድረጋቸው አቋማቸውን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ለማስታረቅ ያደረጉትን ጥረት የሚያሳይ ነው።

የሁለተኛውን አተረጓጐም ችግር በውል ማስተዋል እንድንችል በዚህ ረገድ ያለውን የግሪክ ሰዋስው በተወሰነ ደራጃም እንኳ ቢሆን እንመልከት። በአማርኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆችና በበርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች፣ "በገዛ ደሙ" ተብሎ የተተረጐመው በግሪክ፣ "ተዉ ሂማቶስ ተዉ ኢድዩ" ("τοῦ αἵματος τοῦ ἰδίου") የሚለው ሐረግ ነው። ይህን ሐረግ ቃል በቃል ስንተረጉመው፣ "በደሙ በእርሱ በራሱ" የሚል ትርጉም ያለው ነው። "በእርሱ በራሱ" የሚለው የግሪክ ቃል ("ኢድዩ" " τοῦ ἰδίου") ቅጽል ሲሆን፣ "ደም" (ግሪክ "ሂማቶስ" "αἵματος") በሚለው ስም (noun) ላይ የሚቀጸል ነው። በግሪክ ሰዋስው፣ ቅጽል ከሚቀጸልበት ስም በኋላ መምጣቱ የተለመደ ጉዳይ ስለሆነ፣ በዚህ ረገድ የዐረፍተ ነገሩ ቅደም ተከተል የዐረፍተ ነገሩን ትርጉም አይቀይረውም[60]። ለምሳሌ በዚሁ ክፍል ላይ፣ "መንፈስ ቅዱስ" (ግሪክ "ቶ ኒውማ ቶ ሀግዮን" "τὸ πνεῦμα τὸ ἅγιον") የሚለውን ብንመለከት "ቅዱስ" (ግሪክ "ቶ ሀግዮን" "τὸ ἅγιον") የሚለው ቅጽል፣ መንፈስ (ግሪክ "ቶ ኒውማ" "τὸ πνεῦμα") ከሚለው ስም በኋላ እንደ መጣ እንመለከታለን። እስከ ዐሥራ ዘጠኝ መቶ አጋማሽ ድረስ አንድም ሰው፣ "በገዛ ደሙ

---

57 "ጌታ" የሚለውን ቃል የተጠቀመው የ1980 ትርጉምም ቢሆን "ጌታ" የሚለውን ቃል የተጠቀመው ወልድን በሚያሳይ መንገድ ነው።

58 New American Standard Bible (NASB), English Standard Version (ESV), New International Version (NIV), New King James Version (NKJV), Holman Christian Standard Bible (HCSB) እንዲሁም ሌሎች።

59 New Revised Standard Version (NRSV), Revised English Bible (RSV).

60 Wallace, *Greek Grammar Beyond the Basics,* 306-7. [article + noun + article + adjective የሚለው አካሄድ በሐዲስ ኪዳን ግሪክ ሰዋስው the second attributive postion በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ በኮይኔ በግሪክ ሰዋስው ምሁራን ዘንድ ሁሉ ተቀባይነት ያለው ሕግ ነው]።

የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን” የሚለውን አተረጓጐም የተቃወመ ወይም በሁለተኛ ደረጃ የቀረበውን የአተረጓጐም አካሄድ የተከተለ አንድም ሰው የለም[61]::

“በገዛ ልጁ ደም” የሚለው አተረጓጐም የሰዋስው መሠረቱ ግሪክ ስሞችን በቅጽልነት የሚጠቀምበት ሁኔታ አለ የሚለው የግሪክ ሰዋስው ነው[62]:: አንዳንድ ሰዎች፣ “በእርሱ በራሱ” (“ተዉ ኢድዩ” “τοῦ ἰδίου”) የሚለው ቃል ይህ ስሞችን በቅጽልነት በሚጠቀመው በሰዋስው ሕግ የሚገዛ ነው ስለዚህም “ተወዳጅ ወይም አንድያ” (the Beloved) ተብሎ ለክርስቶስ እንደሚውለው የፍቅር/የክበሬታ ስያሜ ሊያገለግል ይችላል የሚል ነው:: በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ይህ የሰዋስው ሕግ ሊያስሄድ እንደሚችል የመስኩ ሊቃውንት ቢያስረዱም[63] ካላይ እንደ ተመለከትነው እስከ ዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደርስ ይህ ዐይነቱን ትንተና የተከተለ ምሁር ያለመኖሩ ብቻ ሳይሆን፣ “በእርሱ በራሱ” (“ተዉ ኢድዩ” “τοῦ ἰδίου”) የሚለው ቃል ክርስቶስን የሚያመለክትበት አንዳችም የሐዲስ ኪዳን ክፍል የለም:: በቤተ ክርስቲያን ታሪክም ይህ ቃል ክርስቶስን እንደሚያመለክት የጻፈ አንድም የቤተ ክርስቲያን ሰው የለም::

ምናልባት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን፣ “በደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን” የሚለው ሐረግ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ አብ እንዳለ (አብና ወልድ አንድ አካል እንደ ሆኑ) የሚያመለክት ነው የሚል የሙግት ነጥብ ሊያቀርቡ ይችላሉ:: ነገር ግን ክፍሉ ቤተ ክርስቲያንን በገዛ ደሙ የዋጃት፣ “እግዚአብሔር ነው” ይላል እንጂ፣ “አብ” ነው አላለም:: ይህም ኢየሱስ አምላክ መሆኑን እንጂ፣ አብ መሆኑን ሊያሳይ አይችልም:: ከላይ በስፋት ለማየት በሞከርናቸው ክፍሎች ኢየሱስ፣ ከአብ ጋር አብሮ የሚኖር “አምላክ” (ዮሐንስ 1÷1) እንዲሁም ያልታየውን አምላክ ይፋ ያደረገው/የገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውና እርሱ ራሱ አምላክ የሆነው ኢየሱስ እንደ ሆነ (ዮሐንስ 1÷18) ቶማስም ይህን የእግዚአብሔር ልጅ “ጌታዬና አምላኬ” እንዳለው ተመልክተናል (ዮሐንስ 20÷28):: ይህ በግልጽ በተቀመጠበት ሁኔታ የእግዚአብሔር ልጅ የተባለው ኢየሱስ፣ እርሱ ራሱ አባቴ የሚለው አብ ነው ማለት የክፍሉን ትምህርት የተከተለ ባለመሆኑ፣ ደግመን እንላለን ኑፋቄ ነው!—ውጉዝ ከመሰባልዮስ[64]::

በአጠቃላይ “በእርሱ በራሱ” (“ተዉ ኢድዩ” “τοῦ ἰδίου”) የሚለው ቃል፣ “ደም” (ግሪክ “ሄማቶስ” “αἵματος”) በሚለው ስም ላይ የሚቀጸል ቅጽል (ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል:— ዮሐንስ 1÷41፤ 5÷43፤ ዮሐንስ 7÷18፤ ሐዋርያት ሥራ 1÷25) ስለሆነ፣ “በገዛ ደሙ የዋጃት የእግዚአብሔር ነው” የሚለው ነባሩ ትንተና ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያለው ስለሆነ፣ ክፍሉ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መባሉን የሚያስተምር ነው::

---

[61] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place*, 145. ይህን አማራጭ ትርጉም ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙት J. A. Bengel እና F. J. A. Hort የተባሉት ግለሰቦች መሆናቸውን Bowman and Komoszewski, 330-31 የሚከተሉትን መጻሕፍት በመጥቀስ ጽፈዋል Harris, *Jesus as God,* 139; Charles F. DeVine, *"The 'Blood of God' in Acts 20:28,"* CBQ 9 (1947): 405

[62] ይህ የሰዋስው ሕግ Substantival በመባል ይታወቃል::

[63] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place*, 145.

[64] ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው የሚለውን ርእሰ ጉዳይ ስንሞግት አምላክ መባሉ አብ መሆኑን የሚያሳይ ነው የሚለው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት አንዳችም መሠረት የሌለው መሆኑን ለመግለጽ ያህል የቀረበ አስተያየት እንጂ፣ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን በሚቀጥሉት የትምህርት ጊዜያት በስፋት የምንመለከተው ጉዳይ ይሆናል::

# 5) ሮሜ 9÷5 ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንተና
## "ὁ ὢν ἐπὶ πάντων θεὸς εὐλογητὸς εἰς τοὺς αἰῶνας, ἀμήν"

- "እርሱም ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘላለም የተመሰገነ አምላክ ነው፤ አሜን" (**የ1993 አዲሱ መደበኛ ትርጒም—ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር**)
- "እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን" (**የ1954 ትርጒም—የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር**)
- "ሰብእ ዘውእቱ አምላክ ቡሩክ ለዓለም ዓለም አሜን" (**ልሳነ ግእዝ—ማኅበረ መጽሐፍ ቅዱስ ዘኢትዮጵያ**)
- "እርሱ ከሁሉ የሚበልጥ አምላክ፡፡ ለርሱ በረከት የሚገባው ለዘላለም፡፡ አሜን" (**የ1879 ትርጒም—ዘ ብሪቲሽ ኤንድ ፎሪን ባይብል ሦሳይቲ**)
- "እርሱ ከሁሉ በላይ የሆነና የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን" (**የ1980 አዲስ ትርጒም—ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር**)

*የግእዝና የአማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲሁም በርካታ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሞች፣ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን በግልጽ የሚያሳዩ ቢሆንም እንኳ፣ "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" በመባል የሚታወቀው "የይሖዋ ምስክሮች" ድርጅት ያሳተመው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም* (NWT) *ክፍሉን የኢየሱስን አምላክነት በማያመለክት መልኩ አቅርቦታል፡፡ ለንጽጽር እንዲመች አዲሱ መደበኛ ትርጒምን የመጠበቂያ ግንብ ካሳተመው ከአዲሲቱ ዓለም የእንግሊዝኛ ትርጒም ጋር በማነጻጸር ለመመልከት እንሞክር፡—*

- *"አባቶችም የእርሱ ናቸው፤ ክርስቶስም በሥጋ የትውልድ ሐረጉ የሚቈጠረው ከእነርሱ ነው፤ እርሱም፣ ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘላለም የተመሰገነ አምላክ ነው፤ አሜን"፡፡ (አዲሱ በደበኛ ትርጒም)፡፡*
- *"አባቶች የእርሱ ናቸው፤ ክርስቶስም በሥጋ የመጣው ከእነርሱ ነው፤ ከሁሉ በላይ የሆነው አምላክ ይመስገን፤ አሜን"፡፡ (የአዲሲቱ ዓለም ትርጒም)፡፡*

*የመጀመሪያው ክፍል ክርስቶስ "ከሁሉ በላይ የሆነ አምላክ" ነው ሲል፣ የመጠበቂያ ግንብ ያዘጋጀው መጽሐፍ ደግሞ፣ "ከሁሉ በላይ የሆነ አምላክ" የሚለው አብን ነው፡፡ ከላይ ባለው ንጽጽር ከሄድን ደግሞ፣ "እርሱም፣ ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘላለም የተመሰገነ አምላክ ነው" እና "ከሁሉ በላይ የሆነው አምላክ ይመስገን" የሚለው ነው፡፡*

*ግሪኩን በቀኍ (ቃል በቃል) ተርጒመን ደግሞ እናቅርብ፡—*

**ሀ.** ὧν οἱ πατέρες => **አባቶች የእርሱ ናቸው**

**ለ.** καὶ ἐξ ὧν ὁ Χριστὸς τὸ κατὰ σάρκα, => **ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ/ሆነ**

**ሐ.** ὁ ὢν ἐπὶ πάντων => **እርሱ ከሁሉ በላይ የሆነ**

**መ.** θεὸς εὐλογητὸς εἰς τοὺς αἰῶνας, ἀμήν=> **እግዚአብሔር ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን አሜን**

በ"ለ" መጨረሻ ላይ አራት ነጥብ የምናደርግ ከሆነ፣ ክርስቶስ "ከሁሉ በላይ የሆነ እግዚአብሔር/አምላክ" ነው የሚል ትርጉም አይኖረውም፡፡ አራት ነጥቡን በ"ሐ" መጨረሻ ላይ ካደረግን ደግሞ ኢየሱስ ከሁሉ በላይ መሆኑን ቢያሳይም አምላክ መሆኑን ግን አያመለክትም፡፡ አራት ነጥቡን በ"መ" መጨረሻ ላይ ካደረግን ደግሞ፣ ኢየሱስ ከሁሉ በላይ እንዲሁም አምላክ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ሦስተኛው አማራጭ እውነት መሆን ከቻለ ብቻ ክፍሉ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ማሳየት ይችላል፡፡ "ከሁሉ በላይ የሆነው ማነው?" የሚለው ጥያቄ ቢጠየቅ መልስ መሆን የሚችለው "ክርስቶስ ነው" የሚለው ነው፤ ምክንያቱም ክፍሉን ቃል በቃል ስንተረጉመው፣ "አባቶች የእርሱ ናቸው ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ/ሆነ እርሱ ከሁሉ በላይ የሆነ ነው" ስለሚል ነው፡፡ በግሪኩ ሰዋስው "ሆ ኦን" ("ὁ ὢν") "የሆነው እርሱ" የሚለው የግሪክ ቃል "ክርስቶስ" ("ὁ Χριστὸς" "ሆ ክርስቶስ") ከሚለው ጋር የሚወዳጅ ነው፡፡ ምክንያቱም "የሆነው እርሱ" የሚለው ቃል፣ ስለ ክርስቶስ ተጨማሪ ሐሳብ ለመናገር የሚንደረደር ስለሆነ ("ሆ ኦን" "ὁ ὢν" "የሆነው እርሱ" የሚለው ቃል በ2ቆሮንቶስ 11÷31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጐም ልብ ይሏል)፡፡ ክርስቶስ ከሁሉ በላይ መሆኑም ከአንድ ምዕራፍ በኋላ ተገልጾአል (ሮሜ 10÷12)፡፡

"የተመሰገነ/የተባረከ" (ግሪክ "ኢሉጊቶስ" "εὐλογητὸς") የሚለው ቃል፣ "እግዚአብሔር" (ግሪክ "θεὸς") በሚለው ቃል ተቀድሞአል፡፡ ነገር ግን በሐዲስ ኪዳን ግሪክ እግዚአብሔር የሚመሰገንባቸው ቦታዎች ግን "የተመሰገነ/የተባረከ" የሚለው ቃል ከመለኮታዊው ስም በፊት የሚመጣ ነው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ቦታዎች በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ላይ ይመለከቷል (መዝሙር 66÷20፤ 68÷35፤ 28÷6፤ 31÷21፤ 89÷52፤ 41÷13፤ 106÷48፤ ዘፀአት 18÷10፤ ሩት 4÷14፤ 1ሳሙኤል 25÷32፤ ሉቃስ 1÷68፤ 1ቆሮንቶስ 1÷3፤ ኤፌሶን 1÷3፤ 1ጴጥሮስ 1÷3)፡፡ ሮሜ 9÷5 ግን ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማመስገን ሕግ የሚከተል አይደለም፡፡ ስለዚህ፣ "እግዚአብሔር ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን" የሚለው ዐረፍተ ነገር፣ "እርሱ ከሁሉ በላይ የሆነ" የሚለው ዐረፍተ ነገር አካል እንደ ሆነ እንረዳለን፡፡ ጳውሎስ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነውን የሰዋስው አወቃቀር በሌላም ስፍራ ላይ ተጠቅሞአል (የሮሜን መልእክት ጨምሮ)[65]፡፡ ለምሳሌ:—

- "የእግዚአብሔርን እውነት በሐሰት ለወጡ፤ በፈጣሪ ፈንታ ፍጡር አመለኩ፤ አገለገሉም፤ ፈጣሪም ለዘላለም የተመሰገነ ነው፤ አሜን" (ሮሜ 1÷25)፡፡
- "ለዘላለም የተመሰገነው [ὁ ὢν] የጌታ የኢየሱስ አምላክና አባት እንደማልዋሽ ያውቃል" (2ቆሮንቶስ 11÷31)[66]፡፡

ስለዚህ ነው በየዘመናቱ የነበረችው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሮሜ 9÷5 የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ያረጋግጣል የምትለው፡፡

[65] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place*, 147.
[66] ዝኒ ከማሁ፡፡

# 6) ቲቶ 2÷13 እንዲሁም 2ጴጥሮስ 1÷1 ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንተና

**“προσδεχόμενοι τὴν μακαρίαν ἐλπίδα καὶ ἐπιφάνειαν τῆς δόξης τοῦ μεγάλου θεοῦ καὶ σωτῆρος ἡμῶν Ἰησοῦ Χριστοῦ,”**
“ይህም የተባረከ ተስፋችን የሆነውን የታላቁን የአምላካችንንና የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ በመጠባበቅ ነው”
(**ቲቶ** 2÷13)

**“Συμεὼν Πέτρος δοῦλος καὶ ἀπόστολος Ἰησοῦ Χριστοῦ τοῖς ἰσότιμον ἡμῖν λαχοῦσιν πίστιν ἐν δικαιοσύνῃ τοῦ θεοῦ ἡμῶν καὶ σωτῆρος Ἰησοῦ Χριστοῦ,”**
“የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና ሐዋርያ ስምዖን ጴጥሮስ፤ በአምላካችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ በኩል እንደ ተቀበልነው ዐይነት ክቡር እምነት ለተቀበሉት”
(2**ጴጥሮስ** 1÷1)

***እ**ነዚህ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ ተመሳሳይ የሆነ የሰዋስው አወቃቀር ስላላቸው ክፍሎቹን ሰዋስዋዊ አወቃቀር በተመለከተ ክፍሎቹን በጥምረት ለማየት እንሞክራለን:: የቲቶው ምንባብ፣ “ታላቁ አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ” (ግሪክ “ቶው ሜጋሉ ቴዉ ካይ ሶቲሮስ ሁሞን የሱ ክርስቱ”* “τοῦ μεγάλου θεοῦ καὶ σωτῆρος ἡμῶν Ἰησοῦ Χριστοῦ”) ***ሲል ጴጥሮስ ደግሞ፣ “አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ” (ግሪክ “ቶው ቴዉ ሁሞን ካይ ሶቲሮስ የሱ ክርስቱ”*** “τοῦ θεοῦ ἡμῶν καὶ σωτῆρος Ἰησοῦ Χριστοῦ”) ***ይላል:: በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ኢየሱስ ክርስቶስ፣ “አምላካችንና መድኀኒታችን” የተባለ ሲሆን፣ የምንባባቱም የሰዋስው አወቃቀር አንድ ዐይነት ነው::***

***ግ**ራንቪል ሻርፕ በመባል የሚታወቀው የሰዋስው አወቃቀር፣* (1) ***ሁለት ነጠላ የሆኑ ነገር ግን*** (2) ***የተጸውዖ ስም ያልሆኑ ስሞች (ለምሳሌ ኢየሱስ፣ ጴጥሮስ፣ ጳውሎስ ነገር ግን አብ፣ ጌታ፣ ንጉሥ ወዘተ የሚሉትን የማዕረግ ስሞች አይጨምርም)*** (3) ***“እና” (ግሪክ “ካይ”*** “καὶ”) ***በሚለው የግሪክ አያያዥ ቃል ከተጣመሩ*** (4) ***በ“እና” የተያያዙት ሁለት ስሞች ተመሳሳይ ሙያ*** (case) ***ካላቸው እንዲሁም*** (5) ***በመጀመሪያው ስም ላይ ውስን መስተኣምር ኖሮ በሁለተኛው ስም ላይ ውስን መስተኣምር ከሌለ ሁለቱም ስሞች አንድን አካል የሚያመለክቱ ናቸው***[67]***::***

---

[67] ***ስለ ሻርፐስ ሕግ ጥሩ ማብራሪያ ከፈለጉ የሚከተሉትን መጻሕፍት ይመለከቷል***:— Daniel B. Wallace, Greek Grammar Beyond the Basics, 270-90. Daniel B. Wallace, "Granville Sharp: A Model of Evangelical Scholarship and Social Activism," JETS 41 (1998): 591-613. Robert M. Bowman Jr. ***ይህን ሕግ ከመናፍቃን የተከላከለበትን*** 41 ***ገጽ ጽሑፍ፣*** "Sharp's Rules and Antitrinitarian Theologies: A Defense of Granville Sharp's Argument for the Deity of Christ," ***ከሚከተለው ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል***:— <http://biblicalapologetics.net/NTStudies/Sharps_Rule.pdf>. "In Greek, when two nouns of the same case are connected by kai (“and”), and the definite article appears before the first noun but not before the second, both nouns refer to the same person if the nouns are (1)

**ይህን የሰዋስው ሕግ መሠረት ያደረጉ በርካታ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት አሉ፡፡ ለምሳሌ፡—** **"አምላካችንና አባታችን"** ("τοῦ θεοῦ καὶ πατρὸς ἡμῶν") (**ለምሳሌ ገላትያ** 1÷4፤ **ፊልጵስዩስ** 4÷20፤ 1**ተሰሎንቄ** 1÷3፤ 3÷1:13)፣ **"አምላክና አባት"** ("τὸν θεὸν καὶ πατέρα") (**ለምሳሌ ሮሜ** 15÷6፤ 1**ቆሮንቶስ** 15÷24)፡፡ **የሚሉት አወቃቀሮች ስለ አንድ አካል የሚናገሩ ናቸው እንጂ ስለተለያዩ ሁለት አካላት የሚናገሩ አይደሉም፡፡ ይህ የሰዋስው ሕግ ምን ያህል ተኣማኒ ለመሆኑ አንዳንድ ናሙናዎችን ከሐዲስ ኪዳን ምንባባት ለማየት እንሞክር**[68]:—

| የሐዲስ ኪዳን ምንባባት | ግሪክ | የአማርኛ ቊም ትርጉም |
|---|---|---|
| ማርቆስ 6÷3 | οὐχ οὗτός ἐστιν ὁ τέκτων, **ὁ υἱὸς** τῆς Μαρίας καὶ **ἀδελφὸς** Ἰακώβου | ይህ አናጢው፣ የማርያም *ልጅና* የያዕቆብ *ወንድም* አይደለምን? |
| ሉቃስ 20÷37 | κύριον **τὸν θεὸν** Ἀβραὰμ καὶ **θεὸν** Ἰσαὰκ καὶ **θεὸν** Ἰακώβ. | ጌታ የአብርሃም *አምላክ*፣ የይስሐቅ *አምላክ* የያዕቆም *አምላክ* |
| ሐዋርያት ሥራ 3÷14 | ***τὸν ἅγιον*** καὶ ***δίκαιον*** | ቅዱሱንና ጻድቁን |
| ኤፌሶን 6÷21 | Τυχικὸς ὁ ἀγαπητὸς **ἀδελφὸς** καὶ πιστὸς ***διάκονος*** ἐν κυρίῳ, | ቲኪቆስ የተወደደ *ወንድምና* በጌታ የታመነ *አገልጋይ* |
| ቈላስይስ 4÷7 | Τυχικὸς ὁ ἀγαπη***τὸς ἀδελφὸς*** καὶ πιστὸς ***διάκονος*** καὶ ***σύνδουλος*** ἐν κυρίῳ, | ቲኪቆስ የተወደደ ወንድምና የታመነ አገልጋይ ቤታም አብሮኝ ባርያ የሆነ |
| 1ተሰሎንቄ 3÷2 | Τιμόθεον, ***τὸν ἀδελφὸν*** ἡμῶν καὶ ***συνεργὸν*** τοῦ θεοῦ | ጢሞቴዎስ፣ *ወንድማችንና* የእግዚአብሔር *አገልጋይ* |
| ዕብራውያን 12÷2 | τὸν τῆς πίστεως ***ἀρχηγὸν*** καὶ ***τελειωτὴν*** | የእምነታችን *ጀማሪና ፈጻሚ* |
| ያዕቆብ 3÷9 | ***τὸν κύριον*** καὶ ***πατέρα*** | *ጌታና አባት* |
| ራእይ 1÷9 | Ἰωάννης, ***ὁ ἀδελφὸς*** ὑμῶν καὶ ***συγκοινωνὸς*** | *ወንድማችሁና አብሬአችሁ የምካፈል* ዮሐንስ |
| 1ጴጥሮስ 2÷25 | ***τὸν ποιμένα*** καὶ ***ἐπίσκοπον*** τῶν ψυχῶν ὑμῶν | ወደ ነፍሳችሁ *እረኛና ጠባቂ* |
| 1ጴጥሮስ 5÷1 | ὁ συμπρεσβύτερος καὶ μάρτυς τῶν τοῦ Χριστοῦ παθημάτων, | *አብሬው ሽማግሌና* የክርስቶስ መከራ *ምስክር* የሆንሁ |
| ራእይ 1÷6 | τῷ θεῷ καὶ πατρὶ | *ለአምላኩና ለአባቱ* |

personal, (2) singular, and (3) non-proper nouns, and if the nouns are (d) not normally paired semantically as denoting two persons.

[68] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place*, 145. Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place*, 151-52.



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

| የሐዲስ ኪዳን ምንባባት | ግሪክ | የአማርኛ ቊም ትርጉም |
|---|---|---|
| ሮሜ 15÷6፤<br>1ቆሮንቶስ 15÷24፤<br>2ቆሮንቶስ 1÷3 ሀ | τὸν θεὸν καὶ πατέρα | *አምላክና አባት* |
| ይሁዳ 4 | τὸν μόνον ***δεσπότην*** καὶ ***κύριον*** ἡμῶν Ἰησοῦν Χριστὸν | ብቻውን *አለቃችን/ንጉሣችንና ጌታችን* ኢየሱስ ክርስቶስ |
| ፊልሞና 1 | ὁ ἀδελφὸς Φιλήμονι ***τῷ ἀγαπητῷ*** καὶ ***συνεργῷ*** ἡμῶν | *የተወደደ* ወንድማችንና *የሥራ ባልደረባችን* ፊልሞና |
| ዕብራውያን 3÷1 | ***τὸν ἀπόστολον*** καὶ ***ἀρχιερέα*** τῆς ὁμολογίας ἡμῶν Ἰησοῦν, | የሃይማኖታችን *ሐዋርያና ሊቀ ካህናት* ኢየሱስ |

**የ*አዲሲቱ ዓለም ትርጕም*** (NWT) ***በመባል የሚታወቀው "የይሖዋ ምስክሮች" የመጽሐፍ ቅዱስ የእንግሊዝኛ ትርጕም በቲቶ*** 2÷13 ***እንዲሁም*** 2***ጴጥሮስ*** 1÷1 ***በሁለቱም ቦታዎች ላይ በሚገኙት "ታላቅ አምላክ" እና "መድኀኒት ኢየሱስ ክርስቶስ" በሚሉት ቦታዎች ላይ ከግሪኩ ጋር በተጻረረ መልኩ ውስን መስተኣምር በማስገባት ታላቁ አምላክ የሚለው ቃል አብን የሚያሳይ ሲሆን፣ መድኀኒት የሚለው ደግሞ ወልድን የሚያሳይ ነው ብሎአል***[69]:: ***ይህ የድርጅቱን ፍላጐት እንጂ የቅዱሳት መጻሕፍትን አስተምህሮ የሚያሳይ አይደለም::***

**ቲ**ቶ 2÷13 ***እንዲሁም*** 2***ጴጥሮስ*** 1÷1 ***ምንባባት ኢየሱስ ክርስቶስን "ታላቅ አምላክ" ይሉታል የሚለው የሙግት ነጥብ በሐዲስ ኪዳን ግሪክ ሰዋስው የተደገፈ ብቻ ሳይሆን፣ የምንባቡን ዐውዳዊ ትርጕም የተከተለ ነው:: የክፍሉን ዐውዳዊ ትርጕም ደግሞ እንመልከት:—***

**1)** ***"አዳኛችን/መድኀኒታችን"*** ***("ሶቲሮስ ሁሞን"*** "σωτῆρος ἡμῶν") ***የሚለው ሐረግ በቲቶ መልእክት ውስጥ ስድስት ጊዜ የሚገኝ ሲሆን፣ በአምስቱ ቦታዎች ላይ*** (1÷3:4፤ 2÷10፤ 3÷4:6) ***"አዳኛችን/መድኀኒታችን" የሚለው ቃል ውስን መስተኣምር ያለባቸው ናቸው:: በቲቶ*** 2÷13 ***ላይ ግን ውስን መስተኣምሩ ("ቴዉ"*** "τοῦ") ***የሚገኘው፣ "ታላቁ አምላክ" (ግሪክ "ቶው ሜጋሉ ቴዉ"*** "τοῦ μεγάλου θεοῦ") ***ከሚሉት ቃላት ፊት መሆኑ፣ "ታላቁ አምላክ" እና "መድኀኒታችን" የሚሉት ቃላት በአንድ ውስን መስተኣምር እንደሚተዳደሩ የሚያሳይ ነው::***

**2)** ***ቲቶ*** 2÷13 ***ላይ የሚገኘውና የአማርኛ ትርጕሞች፣ "መገለጥ" ሲሉ የተረጐሙት የግሪክ ቃል "ኢፒፋንያን"*** (ἐπιφάνειαν)***፣ በጳውሎስ መልእክቶች ላይ ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ (ይህ ቃል በአብዛኛው የሚገኘው በመልእክታተ ምጋቤ***[70] ***ላይ ነው*** 2***ተሰሎንቄ*** 2÷8፤ 1***ጢሞቴዎስ*** 6÷14፤ 2***ጢሞቴዎስ*** 1÷10፤ 4÷1:8፤ ***ቲቶ*** 2÷13) ***ሁል ጊዜ ቃሉ የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ የሚያመለክት ነው:: ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ ቲቶ*** 2÷13 ***ላይ የሚገኘው "መገለጥ" ከሌሎቹ ክፍሎች ጋር በተቃረነ መልኩ ኢየሱስን ሳይሆን አብን ያመለክታል ማለት ስሕተት ነው***[71]::

---

[69] Titus 2:13:- "of the great God and of [the] Savior of us, Christ Jesus"  2 Peter 1:1:- "of our God and [the] Savior Jesus Christ'" (NWT)

[70] ***መልእክታተ ምጋቤ/ኖሆሎት የሚባሉት*** 1***ጢሞቴዎስ፣*** 2***ጢሞቴዎስና ቲቶ መልእክቶች ናቸው::***

[71] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place*, 153.



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

**3)** አንዳንድ ምሁራን ክፍሉ ግራን ቪል ሻርፕ በሚባለው የግሪክ ሰዋስው ሕግ መገዛቱን ቢቀበሉም፣ "ታላቁ አምላካችንና መድኀኒታችን" የተባለው ስያሜ አብን የሚያመለክት ነው የሚል ሙግት አላቸው[72]። እንደነዚህ ምሁራን እምነት አብ፣ "ታላቁ አምላካችንና መድኀኒታችን" ሲሆን፣ ወልድ ደግሞ የ"ታላቁ አምላካችንና መድኀኒታችን" "***ክብር***" ነው። እንደዚህ አመለካከት ክርስቲያኖች፣ "የሚጠባበቁት የታላቁ አምላካችንንና የመድኀኒታችንን የተባረከ ተስፋና መገለጥ ነው [ይህ ክብር ደግሞ] ኢየሱስ ክርስቶስ ነው"[73]።

**ይ**ህ አመለካከት ትክክል ነው ብለን እንኳ ብናስብ ኢየሱስ በዳግም ምጽአቱ፣ የእግዚአብሔር ክብር ሙሉ መገለጥ መሆኑ አምላክነቱን የሚያሳይ ቢሆንም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ "ታላቅ አምላክና መድኀኒት" የተባለ እንጂ፣ "ታላቅ አምላክና መድኀኒት" የተባለው የአብ "ክብር" ነው የሚለው ትንተና በርካታ ስሕተቶች አሉበት። ይኸውም:— (1) ክፍሉ በማያሻማ መልኩ፣ "ታላቁ አምላካችንና መድኀኒታችን ***ኢየሱስ ክርስቶስ***" ነው ይላል። (2) ክፍሉ ስለ እግዚአብሔር ክብር መገለጥ ይናገራል እንጂ፣ የሚገለጠው ክብር አምላክ ይባላል አይልም። (3) ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቶቹ ውስጥ ሁሉ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ክብር ነው አላለም (ምንም እንኳ የሚከተሉት ክፍሎች ይህን መሰል መልእክት ያላቸው ቢመስልም እንኳ 2ቆሮንቶስ 4÷4:6)። (4) "ታላቁ አምላችንና መድኀኒታችን" የሚለው ገለጻ አካላዊ ህልውና ያለውን አካል የሚያመለክት እንጂ (ኢየሱስ ክርስቶስን)፣ ረቂቅ የሆነ "ክብርን" የሚያመለክት አይደለም። (5) ሐዋርያው በልእክታተ ምጋቤ ውስጥ ሁሉ "መገለጥ" ("ኢፒፋንያን" "ἐπιφάνειαν") የሚለውን ቃል የተጠቀመው የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ለማመልከት እንጂ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ያለውን ረቂቅ ክብር ለማመልከት አይደለም (2ተሰሎንቄ 2÷8፤ 1ጢሞቴዎስ 6÷14፤ 2ጢሞቴዎስ 1÷10፤ 4÷1:8፤ ቲቶ 2÷13)። (6) ሐዋርያው በመልእክቶቹ ሁሉ ውስጥ፣ "ክብር" የሚለውን ቃል 18 ጊዜ ያህል የተጠቀመ ሲሆን፣ 12 ጊዜ ቃሉን የተጠቀመው ገላጭ በሆነ መልኩ ማለትም በዘርፍ ሙያ (genitive case) ነው፤ ይኸውም ከፊለፊት ያለውን ስም በሚቀጽል መልኩ ማለት ነው (ሮሜ 8÷21፤ 9÷23፤ 1ቆሮንቶስ 2÷8፤ 2ቆሮንቶስ 4÷4፤ ኤፌሶን 1÷17:18፤ 3÷16፤ ፊልጵስዩስ 3÷21፤ ቈላስይስ 1÷11:27፤ 1ጢሞቴዎስ 1÷11፤ ቲቶ 2÷13)። ይህም ክብር ከሚለው ይልቅ እንደ ቅጽል "የተከበረ/ክቡር የሆነ" የሚል ትርጒም ይኖረዋል ማለት ነው። (7) ድነታችንን የፈጸመው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነ ሐዋርያው በዚሁ ዐውድ ውስጥ (ቲቶ 2÷14) ገልጾአል። (8) ሐዋርያው በቲቶ መልእክት ውስጥ፣ "መድኀኒታችን" የሚለውን ቃል ስድስት ጊዜ የተጠቀመው ኢየሱስ ክርስቶስን ለማመልከት ከሆነ (1÷3:4፤ 2÷10:13፤ 3÷4:6)፣ ሰባተኛው ቦታ ላይ ኢየሱስን አያመለክትም የሚለው ጒዳይ ከጳውሎስ አካሄድ ጋር የሚቃረን ነው[74]።

**በ**ተመሳሳይ መንገድ ግራንቪል ሻርፕ በመባል የሚታወቀውን የሐዲስ ኪዳን ግሪክ ሰዋስው እንዲሁም የክፍሉን ዐውድ ወደ ጐን በመተው አንዳንድ ግለሰቦች እንዲሁም የሃይማኖት ድርጅቶች በ2ጴጥሮስ 1÷1 ላይ፣ "አምላካችንና አዳኛችን" የሚለው ስያሜ ኢየሱስ ክርስቶስን አያመለክትም የሚል ሙግት አላቸው። ለዚህ አቋማቸው እንደ ዋነኛ የክርክር ነጥብ አድርገው የሚጠቅሱት፣ በዚሁ ዐውድ "እግዚአብሔር" ወይም "አምላክ" የሚለው ስያሜ አብን የሚየሳይ ሲሆን፣ ጌታችን ኢየሱስ የሚለው ስያሜ ደግሞ ወልድን የሚያመለክት ነው የሚለው ነጥብ ነው

---

72 ዝኒ ከማሁ።

73 ዝኒ ከማሁ።

74 ዝኒ ከማሁ፤ 154።

(ቊጥር 2):: ይህ፣ በሐዲስ ኪዳን ምንባባት ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ አልተባለም የሚለውን የተሳሳተ ግንዛቤ ታሳቢ ያደረገ አቋም ነው:: ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍት አብ አምላክ እንደ ሆነ ሁሉ ወልድም አምላክ መሆኑን በግልጥ ያስተምሩናል—እንዲያውም በተመሳሳይ ዐውድ ውስጥ (ቢያንስ እስካሁን የተመለከትናቸውን ምንባባት ይመለከቷል ዮሐንስ 1÷1:18፤ 20÷17:28:31፤ ዕብራውያን 1÷8-9)::

በሁለተኛ ጴጥሮስ መልእክት የግራንቪል ሻርፕን ሕግ በተከተለ መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደ ተባለ ሁሉ፣ "ጌታችንና መድኀኒታችን" ተብሏል የሚከተለውን ሰንጠረዥ ይመለከቷል[75]:—

| 2ጴጥሮስ | ግሪክ | አማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|
| 1÷1 | τοῦ θεοῦ ἡμῶν καὶ σωτῆρος Ἰησοῦ Χριστοῦ, | አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ |
| 2÷20 | τοῦ κυρίου [ἡμῶν] καὶ σωτῆρος Ἰησοῦ Χριστοῦ | ጌታ[ችን] እና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ |
| 3÷18 | τοῦ κυρίου ἡμῶν καὶ σωτῆρος Ἰησοῦ Χριστοῦ | ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ |

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "ጌታችንና መድኀኒታችን" በተባለባቸው በእነዚህ ምንባባት (1÷11፤ 2÷20፤ 3÷18) "ጌታ" እንዲሁም "መድኀኒት" የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በሚለው ጕዳይ ላይ ከየትኛውም ወገን አንዳችም ተቃውሞ አያውቅም:: ነገር ግን ተመሳሳይ የሰዋስው አወቃቀር ተከትሎ "ጌታ" የሚለው ስያሜ "አምላክ" በሚለው ስም ሲተካ ግን፣ አልቀበልም የሚሉ ሰዎች፣ "ጌታና መድኀኒት" የሚሉትንስ ምንባባት እንዴት ሊቀበሉት ቻሉ?

የሁለተኛ ጴጥሮስ ኢየሱስ ክርስቶስን፣ "አምላካችንና መድኀኒታችን" ነው በሚለው መሠረተ እምነት መልእክቱን ከፍቶ፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችንና መድኀኒታችን"ም ነው የሚለውን ጕዳይ ማስከተሉ እንዲሁም መልእክቱን፣ "በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት ዕደጉ፤ ለእርሱ አሁንም፣ ለዘላለምም ክብር ይሁን፤ አሜን" (3÷18) በሚለው ቃል መቋጨቱ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚያስተምር ነው::

የመክፈቻው ቊጥር "አምላካችንና መድኀኒታችን" (1÷1) ብሎ የመልእክቱ መዝጊያ ክፍል "ጌታችንና መድኀኒታችን" (3÷18) ማለቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችንና አምላካችን መሆኑን በአጽንኦት የሚገልጽ ነው:: የመዝጊያው ንግግር ሰዋስዋዊና ዐውዳዊ ትርጕሙ ክርስቶስን የሚሳየ ከሆነ፤ ይህንኑ ሰዋስው እንዲሁም ዐውዳዊ ትርጕም ተከትሎ ክርስቶስ አምላክና መድኀኒት ነው የሚለውን ጕዳይ መቀመል እንዴት ሊከብደን ቻለ!—**ወግድ አርዮስ፤ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ኢየሱስ ክርስቶስ "ጌታችንና አምላካችን" ነው!**

[75] ዝኒ ከማሁ፤ 155::


ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

# 7) ዕብራውያን 1÷8 ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንተና

## “πρὸς δὲ τὸν υἱόν, Ὁ θρόνος σου ὁ θεὸς εἰς τὸν αἰῶνα τοῦ αἰῶνος, καὶ ἡ ῥάβδος τῆς εὐθύτητος ῥάβδος τῆς βασιλείας σου”

- “ስለ ልጁ ግን እንዲህ ይላል፤ "አምላክ ሆይ፤ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ ዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤ ጽድቅም የመንግሥትህ በትር ይሆናል” **(የ1993 *አዲሱ መደበኛ ትርጒም—ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር*)**
- “ስለ ልጁ ግን:— አምላክ ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው” **(የ1954 *ትርጒም—የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር*)**
- “ወበእንተ ወልዱሰ ይቤ መንበርከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም በትረ ጽድቅ በትረ መንግሥትከ” **(*ልሳነ ግእዝ—ማኅበረ መጽሐፍ ቅዱስ ዘኢትዮጵያ*)**
- “ስለ ልጁ ግን አለ ዙፋንህ አምላክ ለዘላለም ነው፡፡ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው” **(የ1879 *ትርጒም—ዘ ብሪቲሽ ኤንድ ፎሪን ባይብል ሦሳይቴ*)**
- “ስለ ልጁ ግን፣ "አምላክ ሆይ! ዙፋንህ ለዘላለም ይኖራል፤ መንግሥትህን በጽድቅ ታስተዳድራለህ” **(የ1980 *አዲስ ትርጒም—ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር*)**

***የ*** *ዕብራውያን መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመላእክት ሁሉ በላይ እንደ ሆነ በሚገልጽበት ዐውድ ውስጥ የመዝሙር መጽሐፍን በመጥቀስ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ የተለየ መሆኑን ከገለጸ በኋላ እርሱ ራሱ አምላክ መሆኑን ያስተምራል፡፡*

> *“ስለ ልጁ ግን እንዲህ ያላል:—*
>
> *'አምላክ ሆይ፤ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ ዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤ ጽድቅም የመንግሥትህ በትር ይሆናል፤ ጽድቅን ወደድህ፤ ዐመፃን ጠላህ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከባልንጀሮችህ በላይ አስቀመጠህ፤ የደስታንም ዘይት ቀባህ'”* (1÷8-9)

***የ*** *ዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ ይህን ክፍል የጠቀሰው ከመዝሙር* 45÷6-7 *ነው፡፡ ይህ የመዝሙር ክፍል የሚናገረው ስለ እስራኤል ንጉሥ* 45÷1-5 *ስለሆነ፣ የእስራኤል ንጉሥ አምላክ በተባለበት መልኩ ኢየሱስ ክርስቶስም አምላክ መባሉ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት አያሳይም የሚል የሙግት ነጥብ ሊቀርብ ይችላል፡፡*

***በ*** *ክፍሉ ውስጥ የተጠቀሰው፣ “አምላክ” የሚለው መጠሪያ፣ የእስራኤልን ንጉሥ የሚያሳይ አይደለም*[76]*፡፡ በነቢዩ ኢሳይያስ የትንቢት መጽሐፍ፣ “አማኑኤል” የሚለው መጠሪያ የነቢዩ ኢሳይያስ ልጅ የማኸር ሻላል ሃሽ ባዝ መጠሪያ ይምሰል እንጂ* (*ኢሳይያስ* 8÷3፤ 7÷14) *ስያሜው ትንቢታዊ መልእክት ስለነበረው፣ “አማኑኤል” የሚለው ስም ለኢየሱስ ክርስቶስ መጠሪያ ሆኖ እናገኘዋለን* (*ማቴዎስ* 1÷22-23)*፡፡ ልክ እንደዚሁ ሁሉ መዝሙር* 45*ም ስለ እስራኤል ሰብአዊ*

---

[76] *አንዳንድ ምሁራን መዝሙር* 45 *የእስራኤልን ንጉሥ አምላክ አላለም ምክንያቱም ክፍሉ መተርጐም ያለበት፣ “ዙፋንህ ለዘላለም ነው”፣ “እግዚአብሔር በትረ መንግሥትህን ስለሚያጸናልህ መንግሥትህ ዘላለማዊ ይሆናል”፣ “መንበርህ ዘላለማዊ ነው” ወዘተ ተብሎ ነው ባይ ናቸው፡፡ ነገር ለእነዚህ አማራጭ ትርጒሞች ሁሉ አጥጋቢ ያለመሆናቸውን ፕሮፌሰር ሙሬ ሐሪስ ሞግተዋል፡፡ ነገር የእስራኤልን ንጉሥ እግዚአብሔር ማለቱ ንጉሡ አምላክ ነበር ለማለት ሳይሆን፣ ከዳዊት ዘር የሚወለደውን ንጉሥ የሚያመለክት ትንቢታዊ መልእክት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡* Harris, *Jesus as God,* 191.

ንጉሥ የሚያወራ ቢመስልም[77] የመዝሙሩ ትንቢታዊ መልእክት ግን የዳዊት ዘር እንዲሁም ዘላለማዊ ንጉሥ ስለሆነው ስለ መሲሑ የሚናገር ነው። ይህ ትንታኔ ተአማኒ ለመሆኑ፣ መዝሙር 45 በግልጽ ይናገራል። ቁጥር 2 ላይ መሲሑን፣ "ኀያል" (ዕብራይስጥ "ጊቦር" ከኢሳይያስ 9፥6 ጋር ያነጻጽሯል) ሲለው፣ ቁጥር 3 ደግሞ፣ "ግርማና ሞገስ" የሚሉት አምላካዊ ባሕርያት እንዳሉት ይገልጻል ከሰባውያን ንጉሥ ፍጹም የላቀና የተለየ መሆኑን ይገልጻል ይናገራል። ከቁጥር 4-7 ባለው ክፍል ደግሞ ንጉሡ እውነት፣ ትሕትናና ሞገስ ገንዘቡ እንደ ሆኑ፣ ዙፋኑ ዘላለማዊ ዙፋን እንደ ሆነ ይገልጻል። በተለይ ቁጥር 8-15 ባለው ክፍል ንጉሡ ሙሽራ እንዳለው እንዲሁም የንጉሡና የሙሽራዪቱ ክብር የተገለጠበት መንገድ የመሲሑንና የቤተ ክርስቲያንን መጻኢ ዕጣ ፈንታ የሚያመላክት ነው (ራእይ 21)። በተለይ የዓለም ነገሥታት ሁሉ እንደሚሰግዱለትና ምስጋናን እንደሚያቀርቡለት የሚናገሩት እነዚህ ምንባባት ንጉሡ ከሰብአዊ ነገሥታት ፍጹም የተለየ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው[78]። በአጠቃላይ መዝሙር 45 ስለ ሰብአዊ ንጉሥ የሚናገር ሳይሆን፣ ዘላለማዊ ስለሆነው ንጉሥና ስለ መሲሑ የሚያስተምር ትንቢታዊ ዝማሬ ነው[79]።

ለዚህም ነው የዕብራውያን ጸሓፊ መዝሙር 45 ስለ ልጁ የሚናገር ምንባብ ነው የሚለው (ዕብራውያን 1፥8)። ዳዊት፣ ሰሎሞን እንዲሁም ሌሎች የእስራኤል ነገሥታት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከኢየሩሳሌም ሆነው የሰጡት አመራር በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ሆኖ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመራውን የእግዚአብሔርን ልጅ አመላካች ነው (ዕብራውያን 1፥2-3)። ይህም የእግዚአብሔር ልጅ መላእክት የሚሰግዱለት (ቁጥር 6)፣ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ (ቁጥር 10) እንዲሁም ፍጥረታቱን የማጥፋት ክህሎት ያለው ነው (ቁጥር 11-12)። እነዚህ ሁሉ አስደናቂ ንግግሮች የሚነገሩለት ኢየሱስ ክርስቶስ ከመላእክት ስም ሁሉ በላይ የላቀ ስም ባለቤት መሆኑ ብቻ ሳይሆን (ቁጥር 4)፣ “አምላክ” የሚለውም ስም ባለቤት ነው (ቁጥር 8)[80]።

እስካሁን ለማየት እንደ ሞከርነው ዕብራውያን 1፥8 በማያሻማ መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ይለዋል የሚለውን አስተምህሮ የማይቀበሉ ሰዎች ለሙግታቸው መከራከሪያ ነጥብ አድርገው የሚጠቅሱት ቁጥር 8 ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ይበለው እንጂ ቁጥር 9 ደግሞ ከመዝሙር 45 በመጥቀስ፣ እርሱ ራሱ አብ አምላኩ እንደ ሆነ ይናገራል በዮች ናቸው። ነገር ግን ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ራሱ አምላክ እንደ ሆነ ሁሉ (ዮሐንስ 1፥1:14:18፤ 20፥28:31)፣ የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊም ልክ እንደ ሐዋርያው ዮሐንስ፣ መሳ ለመሳ ኢየሱስ አምላክ እንደ ሆነ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስም አባት አምላክ መሆኑን ገልጾአል (ዮሐንስ 20፥17:28፤ ዕብራውያን 1፥8:9)። ኢየሱስ ክርስቶስ ትስብእት ሲሆን፣ ሰው በመሆኑ ምክንያት የፍጡሩ አካል ሆኖአል (ዮሐንስ 1፥14፤ ፊልጵስዩስ

---

[77] መጽሐፈ መዝሙር ስለየትኛው የእስራኤል ንጉሥ እንደሚናገር ያለመታወቁ ጉዳይ መጽሐፈ መዝሙር "ንጉሥ" ሲል፣ መሲሑን ለማመላከት እንደ ሆነ የብሉይ ኪዳን ምሁራን ያስረዳሉ።

[78] ታላቁ የእስራኤል ንጉሥ፣ ንጉሥ ዳዊት ስለራሱ የተናገራቸው የሚመስሉ ንግግሮች እንኳ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስለራሱ ሳይሆን ዘላለማዊ ስለሆነው ንጉሥ ይኸውም ስለ መሲሑ የተነገሩ ትንቢታዊ ንግግሮች መሆናቸው ተገልጾአል (መዝሙር 16፥8-11 ያለውን ክፍል ከሐዋርያት ሥራ 2፥25-28 ጋር ያነጻጽሯል)።

[79] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place*, 149.

[80] ዝኒ ከማሁ፣ 150።

2÷6-7)። *ስለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ አባቱን እንደ አምላኩ ክብርን ሰጥቶታል* (*ራእይ* 3÷12)። *ይህ እንዳለ ሆኖ ኢየሱስ ባልተፈጠረው አምላካዊ ባሕርዩ ልክ እንደ አብ አምላክ ነው*።

# 8) 1ዮሐንስ 5÷20 ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንተና

## "οἴδαμεν δὲ ὅτι ὁ υἱὸς τοῦ θεοῦ ἥκει καὶ δέδωκεν ἡμῖν διάνοιαν ἵνα γινώσκωμεν τὸν ἀληθινόν, καὶ ἐσμὲν ἐν τῷ ἀληθινῷ, ἐν τῷ υἱῷ αὐτοῦ Ἰησοῦ Χριστῷ. οὗτός ἐστιν ὁ ἀληθινὸς θεὸς καὶ ζωὴ αἰώνιος"

- "የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መጣ፣ እውነተኛ የሆነውን እርሱን እንድናውቅ ማስተዋልን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እኛም እውነተኛ በሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርሰቶስ አለን፤ እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው" **(የ1993 *አዲሱ መደበኛ ትርጉም—ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር*)**
- "የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፤ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው" **(የ1954 *ትርጉም—የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር*)**
- "ናእምር ከመ ወልደ እግዚአብሔር መጽአ ወወሀበነ ልበ ከመ ናእምሮ ለእግዚአብሔር ዘበጽድቅ። ወሀለውነ ዘበጽድቅ በወልደ እግዚአበሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ውእቱ ዘበአማን እግዚአብሔር ወብነ ሕይወት ዘለዓለም" **(*ልሳነ ግእዝ—ማኅበረ መጽሐፍ ቅዱስ ዘኢትዮጵያ*)**
- "እናውቃለን ግን የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መጣ ዕውቀትንም ሰጠነ። እውነተኛው የሚሆነውን እናውቅ ዘንድ። እኛም በእውነተኛው እንኖራለን በልጁ በየሱስ ክርስቶስ። ይህ ነው እውነተኛ አምላክ የዘላለሙም ሕይወት" **(የ1879 *ትርጉም—ዘ ብሪቲሽ ኤንድ ፎሪን ባይብል ሶሳይቲ*)**
- "የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መጣና እውነት የሆነውን እርሱን እንድናውቅ አስተዋይ ልቡና እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እኛም በዚህ እውነት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ እንኖራለን። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው" **(የ1980 *አዲስ ትርጉም—ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር*)**

*"እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው"* በ*ሚለው ዐረፍተ ነገር ላይ፣* "*እርሱ*" (*ግሪክ* "*ሁውቶስ ኢስቲን*" "οὗτός ἐστιν") *የሚለው ቃል አብን ነው የሚያሳየው ወይስ ወልድን ነው በሚለው ጉዳይ ላይ ትምህርተ ዘለቅ ሲፈ ውዝግብ አላቸው። በነገረ መለኮት ዕውቀታቸውም ሆነ በክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ትልቅ ከበሬታ የተጐናጸፉት ስመ ጥር የቤተ ክርስቲያን አባቶች (ለምሳሌ:— አትናቴዎስ፣ የእስክንድርያው ቄርሎስ፣ የግሪክ ዕደ ክታባትን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ላቲን ቋንቋ የተረጐመው የሮም፣ መርሓያነ ተሐድሶዎቹ ማርቲን ሉተርና ጆን ካልቪን)* "*እርሱ*" *የሚለው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያሳይ በመሆኑ፣* "*እውነተኛ አምላክና የዘላለም*" *ሕይወት የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የሚል ጠንካራ አቋም ነበራቸው። ሬሞንድ ብራውን የተባሉትን ስመ ጥር የሐዲስ ኪዳን ሊቅ ጨምሮ፣ በርካታ ምሁራን*

ክፍሉ ኢየሱስን እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ብሎታል በሚለው ጒዳይ ላይ ጠንካራ አቋም አላቸው።

ዮሐንስ 17÷3 ባሉ ቦታዎች ላይ እግዚአብሔር አብ "እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት" እንደ ተባለው ሁሉ፣ በዚህ ክፍል ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ተብሎአል (እንዲሁም 1ዮሐንስ 1÷2 ይመለከቷል)። ሐዋርያው ዮሐንስ በወንጌሉ መግቢያና በወንጌሉ ማጠቃለያ ላይ ኢየሱስ "አምላክ" እንደ ሆነ እንደ ገለጸው ሁሉ (ዮሐንስ 1÷1፤ 20÷28) በመጀመሪያ መልእክቱ መግቢያና መቋጫ ላይ፣ "የዘላለም ሕይወት" መሆኑንም ይገልጻል (1ዮሐንስ 1÷2፤ 5÷20)። በዐውዱ ውስጥ "የዘላለም ሕይወት" የተባለው አብ ሳይሆን ወልድ ከሆነ (1ዮሐንስ 1÷2፤ 5÷20፤ 11÷25፤ 14÷6) እንዲሁም "እርሱ" (ግሪክ "ሆውቶስ ኢስቲን" "oὗτός ἐστιν") የሚለው አመልካች ተውላጠ ስም አብን ሳይሆን ኢየሱስን ማመልከቱ (1ዮሐንስ 5÷6፤ 2ዮሐንስ 7)፣ በምንባቡ ውስጥ ኢየሱስ፣ "እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት" የመሆኑ ጒዳይ የማንሸሽው ሐቅ ይሆናል።

አንዳንድ ሰዎች፣ "እርሱ" ("ሆውቶስ ኢስቲን" "oὗτός ἐστιν") የሚለው አመልካች ተውላጠ ስም፣ በአቅራቢያው ያለውን ዐውድ ብቻ ላያመለክት ይችላል፤ ስለዚህ "እርሱ" የሚለው አመልካች ተውላጠ ስም አብን ሊያመለክት ስለሚችል (1ዮሐንስ 5÷11) "እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት" የተባለው ወልድ ሳይሆን አብ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አላቸው። ይህ የሙግት ነጥብ ጠንካራ የማይሆንበት ዐቢይ ምክንያት፣ "እርሱ" ("ሆውቶስ" "oὗτός") የሚለው አመልካች ተውላጠ ስም፣ በአቅራቢያው ያለውን ወልድን ሳይሆን፣ ከምንባቡ ርቆ የሚገኘውን አብን ያመለከተበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ በግልጽ አልሰፈረም። የሐዲስ ኪዳን ግሪክ ሰዋሰውንም ሆነ የሌሎች ቋንቋዎችን ሰዋስው የተመለከትን ከሆነ፣ ተውላጠ ስሞች በአቅራቢያቸው የሚገኙትን ባለቤቶች የሚያመለክቱ እንጂ ከዐውዱ ርቆ የሚገኘውን አካል ሊያመላክቱ አይችሉም። ያጣቅሳሉ እንኳ ቢባል በቅርብ የሚገኘውን የዐረፍተ ነገሩን ባለቤት ሳይሆን፣ በሩቅ ያለውን አካል የሚያመለክትበት አጥጋቢ ምክንያት ምን እንደ ሆነ መቅረብ ይኖርበታል።

በአጠቃላይ ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ማስረጃዎች በግልጽ እንደሚያመለክቱት 1ዮሐንስ 5÷20 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው የሚል ግልጽ ትምህርት አለው።

# II. የኩርዮስ (κύριός) ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንታኔ

ከወንጌል ዘማቴዎስ እስከ ራእዩ ለዮሐንስ አቡቀለምሲስ ያሉትን ሃያ ሰባት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንዲያው በግልቡ የዘለቃባቸው ማንኛውም ሰው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዐልፎ ዐልፎ "አምላክ" ወይም "እግዚአብሔር" የመባሉን ያህል፣ "ጌታ" በሚለው ስያሜ ግን እጅግ ተደጋጋሚ በሆነ መልኩ ኢየሱስ ክርስቶስን በሚያመለክትበት መልኩ ጥቅም ላይ እንደ ዋለ በቀላሉ ማስተዋል ይችላል። በርካታ ሰዎች፣ "አምላክ" የሚለው ስያሜ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት እንደሚያሳይ፣ "ጌታ" የሚለው ስያሜ ግን ቢያንስ "አምላክ" ከሚለው ስም ይልቅ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በማሳየቱ ረገድ ያነሰ ጠቀሜታ እንዳለው ሊገምቱ ይችላሉ።



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

“ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊ ስም አለው!” በሚለው ጥናት መጀመሪያ ላይ ለማየት እንደ ሞከርነው፣ በብሉያትም ሆነ በሐዲሳት፣ “እግዚአብሔር” ወይም “አምላክ” (ግሪክ “ቴዎስ” “θεὸς”) የሚለው የግሪክ ቃል በተለያየ ዐውድ ውስጥ የተለያየ ትርጕም ወክሎ ጥቅም ላይ እንደ ዋለ ቅቡል የመሆኑን ያህል፣ “ጌታ” (ግሪክ “ኩርዮስ” “κύριός”) የሚለውም ቃል የተለያየ ትርጕም ወክሎ ጥቅም ላይ ውሎአል::

የሰብዓ ሊቃናት በመባል የሚታወቀው የብሉይ ኪዳን የግሪክ ትርጕም፣ የእግዚአብሔር የተጸውዖ ስም የሆነውን ያህዌ የሚለውን የዕብራይስጥ መጠሪያ፣ አብዛኛውን ጊዜ “ጌታ” (ግሪክ “ኩርዮስ” “κύριός”) በሚለው የግሪክ ቃል ነው የተካው[81]:: አዲሱ መደበኛ ትርጕም በመባል የሚታወቀው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጕም፣ “ያህዌ” የሚለውን ስም፣ “እግዚአብሔር” ብሎ ሲተረጕመው (የሥነ ጽሑፉን ውበት ለመጠበቅ አንዳንድ ጊዜ ጌታ ማለቱ እንደ ተጠበቀ ሁሉ) የተቀሩት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጕሞች ግን፣ “ጌታ” እንዲሁም “እግዚአብሔር” የሚለውን ስያሜ በማቀያየር ተጠቅመዋል::

የብሉይ ኪዳን ምንባባት ያህዌ ብቻ እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ በአጽንኦት ይገልጻሉ (ዘዳግም 4÷35:39፤ 32÷39፤ 2ሳሙኤል 22÷32፤ ኢሳይያስ 37÷20፤ 43÷10፤ 44÷6-8፤ 45÷5:14:21-22፤ 46÷9):: በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ዕብራውያን “ያህዌ”[82] የሚለውን ስም ያለመጥራት ወይም ብሉያትን በሚያነቡበት ጊዜ “ያህዌ” የሚለውን ስም “አዶናይ” በሚለው ስም ተክቶ የማንበብ ልማድ ነበራቸው፤ ለዚህ እንደ ዋነኛ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው የሕጉ መጽሐፍ፣ “የአምላክህን የእግዚአብሔር ስም በከንቱ አትጥራ” ስለሚል፣ ምናልባት የአምላካችንን ስም በከንቱ ጠርተን አምላካችንን ልናሳዝነው እንችላለን ከሚል ፍርሓት የመነጨ ነው[83]::

የሐዲስ ኪዳን የግሪክ መጻሕፍት፣ “ያህዌ” የሚለውን ስምም ሆነ፣ እግዚአብሔር የሚጠራባቸውን ሌሎች ስሞችን አንድ ጊዜ እንኳ ተጠቅመው አናገኝም:: የሐዲስ ኪዳን ጸሓፍያን ብሉይ ኪዳንን አጣቅሰው በጻፉባቸው ቦታዎች ሁሉ እንኳ፣ ያህዌንም ሆነ ሌሎች

---

[81] “ያህዌ” ስለሚለው ስም ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን* (አዲስ አበባ፤ ራዕይ አሳታሚ ድርጅት) ገጽ 60-74 ይመለከቷል::

[82] “ያህዌ” የሚለው ስም እግዚአብሔር አምላክ የራሱ መጠሪያ እንዲሆን ለራሱ ካወጣቸው ስሞች መኻል አንዱ ቢሆንም ይህ ስም በትክክል እንዴት እንደሚጠራ/ሚነበብ ማንም አያውቅም:: ይህ ስም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከስድስት ሺህ ጊዜ በላይ የተጠቀሰ ቢሆንም የቃሉን ትክክልኛ አነባበብ ምን እንደ ሆነ አንድም ሰው አያውቀውም:: ቃሉ “ዮድ ሔ ዋው ሔ” (יְהוָה) ከተባሉት አራት ተነባቢ የዕብራይስጥ ፊደላት የተዋቀረ ስለሆነ (እነዚህ አራት ፊደላት ቴትራግራማተን ወይም ቴትራግራም በመባል ይታወቃሉ) ትክክለኛው አነባበብ የቱ እንደ ሆነ አንድም ሰው አያውቅም::

[83] በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነበረው አይሁዳዊው የታሪክ ጸሓፊ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን (Josephus)፣ ያህዌ የሚለውን የእግዚአብሔር ስም ለመጻፍ ወይም ብሉያትን አጣቅሶ ለመዘገብ በሚበልግበት ጊዜ ሁሉ ያህዌ የሚለውን ስም ጌታ በሚለው ስያሜ ተክቶ ይጽፍ ነበር:: በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በእስክንድርያ ይኖር የነበረው አይሁዳዊው ፈላስፋ ፊሎ (Philo of Alexandria) እንድ ዮሴፍ ወልድ ኮርዮን በጽሑፎቹ ውስጥ ሁሉ ያህዌ የሚለውን ስም አዶናይ (ጌታዬ) በሚለው ስያሜ ተክቶ ይጠራና ይጽፍ ነበር:: ሙት ባሕር አካባቢ ቀኍምራን በመባል በሚጠራው ስፍራ የተገኙትና የሙት ባሕር ጥቅሎች በመባል የሚታወቁት ዕደ ክታባት፣ የቀኍምራኑ ማኅበረሰብ ያህዌ የሚለውን ስም አዶናይ (ጌታዬ) በሚለው ስም ተክቶ ይገለገልበት እንደ ነበረ እነዚህ ድርሳናት ይገልጻሉ::

የእግዚአብሔርን ስሞች በቀጥታ ከመጥቀስ ይልቅ፣ "ቴዎስ" (θεός) ወይም "ኩርዮስ" (κύριος) የሚሉትን ግሪካዊ ስያሜዎችን ነው የተጠቀሙት[84]::

በአጠቃላይ የሐዲስ ኪዳን የግሪክ ዕደ ክታባት፣ "ያህዌ" የሚለውን የብሉይ ኪዳን ስም በጽሑፎቻቸው ውስጥ ያልተጠቀሙ ሲሆን፣ ከብሉይ ኪዳን የተጠቀሱትም ክፍሎች ቢሆኑ፣ "ኩርዮስ" እና "ቴዎስ" በሚለው ግሪካዊ ስያሜ ነው የተተኩት:: የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀው የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት፣ ከዚህ እውነት ጋር በተቃረነ መልኩ፣ "የአዲሲቱ ዓለም ትርጒም" (NWT)[85] በመባል በሚታወቀው የድርጅቱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም፣ "ያህዌ" የሚለውን ስም በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ 237 ጊዜ ተጠቅሞበታል[86]:: ምሁራን ይህ የድርጅቱ አካሄድ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ነው እንዲሁም ከአብ ያንሳል የሚለውን አስተምህሮውን እንዲደግፍለት ምን ያህል እንደ ጠ ቀመው የሚከተሉትን ክፍሎች ከአዲሲቱ ዓለም ትርጒም ላይ ይመለከቷል (የሐዋርያት ሥራ 2÷1፤ 10÷13፤ ማቴዎስ 11÷27፤ ዮሐንስ 20÷28):: ስመ ጥር የሚባሉ የግሪክ ቋንቋ ሊቃውንት ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም በአንድ ድምፅ፣ "ለድርጅቱ አስተምህሮ ሎሌ ያደረ፣ ምሁራዊ ያልሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም" ሲሉ ኰንነውታል[87]:: የመጠመበቂያ ግንብ ድርጅት ያህዌ በሚለው የአምላክ ስም ላይ የሚሰጠውን የተሳሳተ ትምህርት እዚህ ላይ ገታ አድርገን በሐዲስ ኪዳን ምንባባት ኢየሱስ ክርስቶስ "ጌታ" መባሉ፣ ብሉይ ኪዳን ይህዌ ከሚለው ስም ጋር ያለው ቊርኝት አንድ ዐይነት መሆኑን እንመልከት::

---

[84] ዛሬ ከ5,700 በላይ እጅግ ጥንታዊ የሚባሉ የግሪክ ዕደ ክታባት በእጃችን ላይ ያሉ ሲሆን፣ እነዚህ ዕደ ክታባት በአንዳንድ ምንባባት ላይ የተወሰነ ልዩነት ያላቸው ቢሆንም አንድም ዕደ ክታብ የብሉይ ኪዳኑን የእግዚአብሔርን ስም በቀጥታ አልጻፈም::

[85] *New World Translation of the Holy Scriptures: With References* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1984).

[86] ድርጅቱ ያህዌ በሚለው ስም ላይ የሚሰጠውን ትምህርት ከሚከተለው መጽሐፍ ላይ የመለከቷል *ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1994), 191-199. ድርጅቱ በዚሁ ርእሰ ጒዳይ ላይ፣ "ለዘላለም ጸንቶ የሚኖረው መለኮታዊ ስም" በሚል ርእስ ያሳተመውን ቡሮሹር (መለስተኛ መጽሐፍ) ይመለከቷል:: ይህ የድርጅቱ አስተምህሮ የተሳሳተ ነው የሚለውን የተስፋዬ ሮበሌ፤ *የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን* (አዲስ አበባ፤ ራዕይ አሳታሚ ድርጅት) ገጽ 60-74 መጽሐፍ ይመለከቷል:: የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ያህዌ የሚለውን ስም በተመለከተ የሚሰጠውን ትምህርት አስመልክቶ ማወቅ ያለብን መሠረታዊው ቊም ነገር (1) እግዚአብሔር አምላክ ያህዌ በሚል ስም ተጠርቶአል:: (2) ይህ የእግዚአብሔር ስም እንዴት እንደሚነበብ ማንም ሰው አያውቅም:: (3) ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ያህዌ በሚለው ስም ጠርቶት አያውቅም:: ኢየሱስ አባቱን "አባቴ" ብሎ ነው:: (4) አማኞች እግዚአብሔርን "አባታችን" ብለው የመጥራት መብት ተሰጥቶአቸዋል:: (5) ያህዌ የሚለው ስም በአንድም የሐዲስ ኪዳን የግሪክ ዕደ ክታባት ላይ አይገኝም:: (6) ዘፀአት ትልቅ ትኵረት የሚሰጠው በእግዚአብሔር ስም ላይ ሳይሆን ትውልድ ሁሉ ሊያውቀው በሚገባው ከስሙ በስተጀርባ ባለው የእግዚአብሔር ባሕርይ ይኸውም በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ዘላለማዊነት ላይ ነው (ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የይሖዋ ምስክሮች* ገጽ 67-68)::

[87] Robert M. Bowman Jr., *Understanding Jehovah's Witnesses: Why They Read the Bible the Way They Do* (Grand Rapids: Baker, 1991), 109-122.

በአራቱም ወንጌላት በመግቢያቸው ላይ፣ "የጌታን መንገድ አዘጋጁ"[88] የሚለውን የመጥምቁ ዮሐንስን አገልግሎት ዘግበዋል። መጥምቁ ዮሐንስ የጌታን መንገድ አዘጋጁ የሚለው አገልግሎቱ የትንቢተ ኢሳይያስ 40÷3 ትንቢት ፍጻሜ ነው (ማቴዎስ 3÷3፤ ማርቆስ 1÷3፤ ሉቃስ 3÷4፤ 1÷16፤ ዮሐንስ 1÷23)። ትንቢተ ሚልክያስ 3÷1 እንዲህ ይላል:— "'እነሆ፤ በፊቴ መንገድ እንዲያዘጋጅ መልእክተኛዬን እልካለሁ፤ የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ ቤተ መቅደሱ ይመጣል፤ ደስ የምትሰኙበትም የቃል ኪዳኑ መልእክተኛ ይመጣል' ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት"። ከላይ በተዘረዘሩት ምንባባት ላይ "የጌታ መልእክተኛ" የተባለው መጥምቁ ዮሐንስ ሲሆን እርሱም "ጌታ" እንዲሁም "እግዚአብሔር ጸባኦት" ከተባለው አምላክ ፊት ፊት ይሄዳል፤ ይህም እግዚአብሔር ጸባኦት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረው አገልግሎቱ፣ "ጌታ፣ ጌታ" ("ኩሬ ኩሬ" "κύριε κύριε") የሚሉ እንዲሁም በስሙ ተኣምራትን እንደሚያደርጉ የሚያውጁ ነገር ግን እርሱን የማይታዘዙትን ሰዎች እንደሚቀጣ በግልጽ አስጠንቅቆአል (ማቴዎስ 7÷21-23፤ ሉቃስ 1÷16፤ ዮሐንስ 1÷23)። ይህ፣ "ጌታ፣ ጌታ" ("ኩሬ ኩሬ" "κύριε κύριε") የሚለው ስያሜ በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም የተለመደ ሲሆን፣ የዕብራይስጡ "ጌታ ያህዌ" (ዘዳግም 3÷24፤ 9÷26፤ 1ነገሥት 8÷53፤ መዝሙር 69÷6፤ ሕዝቅኤል 20÷49፤ አሞጽ 7÷2:5) ወይም "ያህዌ ጌታ" (መዝሙር 109÷21፤ 140÷7፤ 141÷8) ለሚለው ስም አቻ ስያሜ ነው። ይህም በብሉይ ኪዳን ያህዌን እንጂ ሌሎችን አካላት በፍጹም የማያመለክት መሆኑ፣ "ጌታ" የሚለው ስም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ማሳየቱ ተኣማኒ ይሆናል።

ኢየሱስ፣ በገሊላ ባሕር ደቀ መዛሙርቱ ዓሣ ያጠምዱባት በነበረችው ጀልባ ውስጥ ተኝቶ ሳለ፣ ኀይለኛ ማዕበል በባሕሩ ላይ ተነሥቶ ጀልባዋን በናጣት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ፣ "'ጌታ ሆይ! ጠፋን፤ አድነን' አሉት" ("ጌታ ሆይ አድነን" "ኩሬ ሶውሶን" "Κύριε, σῶσον" ማቴዎስ 8÷25)። ኢየሱስን በውሃ ላይ ሲሄድ የተመለከተው ጴጥሮስ፣ "ጌታ" በውሃ ላይ እንዲመጣ እንዲያዘው ከጠየቀ በኋላ፣ በውሃው ላይ መሄድ ጀመረ፤ የንፋሱ ብርታት እጅግ ያሳሰበው ጴጥሮስ መስመጥ በመጀመሩ ምክንያት፣ "ጌታ ሆይ አድነኝ ብሎ ጮኸ" ("ጌታ ሆይ አድነኝ" "ኩሬ ሶውሶን ሚ" "ὁ κύριε, σῶσόν" ማቴዎስ 14÷30)። ይህ ዐይነቱ የትድግና ጥሪ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የእግዚአብሔርን ታዳጊነት በመሻት ቀርቦ መገኘቱ ("ጌታ ሆይ አድነን" "ሆ ኩሬ ሶውሶን" "Κύριε, σῶσόν με" መዝሙር 118÷25) ኢየሱስ "ጌታ" የተባለበትና እግዚአብሔር አብ "ጌታ" የተባለበትን ዐውድ አንድ ስለሚያደርገው፣ "ጌታ" የሚለው ስም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት አመላካች ይሆናል[89]።

[88] "መንገድ አዘጋጁ" ማለት፣ እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች ከመንገድ ላይ አስወግዱ ማለት ነው (ኢሳይያስ 57÷14፤ 62÷10)። በጥንት የመካከለኛ ምሥራቅ አገሮች ልማድ፣ ንጉሥ አንድን ስፍራ ከመጐብኘቱ በፊት መልእክተኞች ሁኔታውን ማመቻቸት እንዳለባቸው የሚያመለክት ሐሳብ ነው። ምሳሌነቱም ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም ከመምጣቱ በፊት አውራ ጐዳናው መስተካከል እንዳለበት ያመለክታል። መጥምቁ ዮሐንስ መንገድ አዘጋጁ የሚለው ጥሪው ንስሓ በመግባት ለክርስቶስ ምጽአት ራስን ማዘጋጀትን የሚያመለክት ነው።

[89] ማቴዎስ ከዚህ መዝሙር በርካታ ምንባባትን ጠቅሶ መገኘቱ ይህ አነጋገር ከብሉይ ኪዳን ምንባባት ጋር አንድ መሆኑን አመላካች ነው (መዝሙር 118÷22-23:26፤ ከማቴዎስ 21÷9:42 ጋር እንዲሁም መዝሙር 118÷25፤ ከማቴዎስ 8÷25፤ 14÷30 ያነጻጽሩ)።

*በሐዋርያት ሥራ* የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ በርካታ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ አብ ጌታ በተባለበት ዐውድ ጌታ ተብሎ ይገኛል። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ትረካውን የሚጀምረው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ለመጨረሻ ጊዜ መታየቱን እንዲሁም በደቀ መዛሙርቱ ፊት ወደ ላይ ማረጉን በመግለጽ ነው (ሐዋርያት ሥራ 1፥1-11)። ደቀ መዛሙርት የመንፈስ ቅዱስን ምጽአት በመጠባበቅ ወደ ኢየሱስ "ጌታ ሆይ" እንዲሁም፣ "የሰዎችን ልብ ሁሉ የምታውቅ" እያሉ ጸሎት ሲያደርሱ እንመለከታለን (ሐዋርያት ሥራ 1፥24)[90]። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የሰዎችን ልብ ሁሉ የሚያውቀው አምላክ ያህዌ እንደ ሆነ ያስረዳሉ (1ነገሥት 8፥39)።

በመጀመሪያው ክርስቲያናዊ ስብከት፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ ትንቢተ ኢዮኤል በመጥቀስ፣ "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል" ሲል ሰበከ (ሐዋርያት ሥራ 2፥21፤ ኢዩኤል 1፥1-11) ጴጥሮስ "ጌታ" የሚለውን ነቢዩ ኢዩኤል፣ "ያህዌ" ይለዋል፤ ይህም "ጌታ" የሚለው ስያሜ ያህዌ ከሚለው ስም ጋር ተነጻጽሮ መቅረቡን እንዲሁም የኢዮኤል ትንቢት "ያህዌ" እያለ የሚጠራው ኢየሱስን እንደ ሆነ እንመለከታለን)። በዚህ ስብከት ድምዳሜ ላይ፣ በጴጥሮስ እንዲህ ሲል ስብከቱን ይቋጫል፣ "እንግዲህ፣ እግዚአብሔር ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፣ ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ ይረዳ!" (ሐዋርያት ሥራ 2፥36)። በሉቃስ ጽሑፎች ውስጥ (ማለትም የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ መጻሕፍት) "ጌታም ክርስቶስም አደረገው" ሲል በፊት ኢየሱስ፣ "ጌታና ክርስቶስ" አልነበረም ማለት አይደለም። ሉቃስ፣ ኢየሱስ ከመወለዱም በፊት ጌታና ክርስቶስ እንደ ነበር ገልጾአል (ሉቃስ 2፥11)። ጴጥሮስ፣ "ጌታም ክርስቶስም አደረገው" ሲል፣ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከፍ ከፍ ስላደረገው፣ ሰዎች አሁን ጌታና ክርስቶስ መሆኑን በእግዚአብሔር ርዳታ ተገነዘቡ ለማለት ነው[91]።

ወደ ጌታ ኢየሱስ በቀጥታ ከቀረበው ከመጀመሪያው ጸሎትና ከመጀመሪያው ክርስቲያናዊ ስብከት ወደ መጀመሪያው የጌታ ሰማዕት እንሻገር። እስጢፋኖስ ለሞት በድንጋይ በሚወገርበት ጊዜ ኢየሱስን ሁለት ጊዜ፣ "ጌታ" ብሎ በመጥራት ነፍሱን እንዲረከበው እንዲሁም ይህን በደል በሚፈጽሙት ሰዎች ላይ ኀጢአታቸውን እንዳይቈጥርባቸው ሲማጠነው እንመለከታለን (ሐዋርያት ሥራ 7፥59-60)። ወደ ኢየሱስ መጸለዩ የኸውም ትንቢተ ኢዩኤል "የጌታን ስም መጥራት" (ኢዩኤል 2፥32) ከሚለው እንዲሁም ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት ላይ ከሚገልጸው ሐሳብ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ይህን አነጋገር የሐዋርያት ሥራ በተጻፈበት ትረካዊ ዐውድ ማንበብ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጌታዬ እያለች ጸሎትን ወደ ኢየሱስ ማቅረቧ ከብሉያት አስተምህሮ ጋር ሲነጻጸር የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚያሳይ ነው።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ፣ ደቀ መዛሙርት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምሩት ትምህርት "የጌታ ቃል" ተብሎ መጠራቱ (ሐዋርያት ሥራ 8፥25፤ 13፥44:48-49፤ 15፥35-36፤ 16፥32፤ 19፥10፤ እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል 1ተሰሎንቄ 1፥8፤ 2ተሰሎንቄ 3፥1)፣ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ) ለነቢያቱ ከሚሰጣቸው ትንቢታዊ መልእክት ጋር የሚነጻጸር ነው (ለምሳሌ 2ሳሙኤል 24፥11፤ 1ነገሥት 13፥1-2፤ 2ዜና 36፥21፤

---

[90] ደቀ መዛሙርት "ጌታ" የሚሉት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ሆነ ምዕራፍ ሦስት ላይ በትክክል ተገልጾአል።

[91] ልክ እንደዚሁ ሁሉ ሐዋርያው ጳውሎስም ኢየሱስ፣ "ከሙታን በመነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኀይል ተገለጠ" (ሮሜ 1፥4) ይለናል።

ኢሳይያስ 1÷10፤ ኤርምያስ 1÷4፤ ሕዝቅኤል 1÷3፤ ሆሴዕ 1÷1-2፤ ኢዩኤል 1÷1፤ አሞጽ 8÷11-12፤ ዮናስ 1÷1፤ ሚክያስ 1÷1፤ ሚልክያስ 1÷1)። የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት "የጌታ ቃል" የሚለው የሐዋርያቱ ንግግር፣ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት "የያህዌ ቃል" ከሚሉት ጋር መነጻጸሩ "ጌታ" የሚለው ስያሜ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት እንደሚያሳይ የሚገልጽ ነው።

በአጠቃላይ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ጸሎት የሚያደርሱለት፣ የሰዎችን ሁሉ ልብ የሚያውቅ፣ ደቀ መዛሙርት ለስሙ ሰማዕት ሆነው በሚያልፉበት ጊዜ ነፍሳቸውን እንዲረከብ የሚጠሩት፣ ደቀ መዛሙርቱ ለስሙ ክብር የሚኖሩለትና ለስሙም ክብር የሚሞቱለት፣ ቃሉን የሚያምኑና ቃሉን በመስበክና በማስተማር ሌሎች እንዲያምኑ ጥሪ የሚያቀርቡለት "ጌታ" ነው። በዚህ ዐውድ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ "ጌታ" መባሉ ከብሉይ ኪዳኑ ያህዌ ጋር እኩል የሚያደርገው ነው[92]።

***በሐዋርያው ጳውሎስ ጽሑፎች*** ኢየሱስ ከያህዌ ጋር በተስተካከለ መንገድ በበርካታ ምንባባት ውስጥ ጌታ ተብሎ ተጠርቶአል። በዚህ ጥናት የተወሰኑትንና አንኳር አንኳር የሚባሉትን ምንባባት በዳሰሳ መልክ እንቃኛቸዋለን። ሐዋርያው በሮሜ መልእክቱ፣ "'ኢየሱስ ጌታ ነው' ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን፣ ትድናለህ። የምትጸድቀው በልብህ አምነህ ነው፤ የምትድነውም በአፍህ መስክረህ ነውና" (ሮሜ 10÷9-10) ይላል። ሐዋርያው፣ "ኢየሱስ ጌታ ነው" ("ኩርዮስ" "κύριός") እንዲሁም "እግዚአብሔር ከሙታን እንዳስነሣው" ማመን ድነት እንደሚያስገኝ ይገልጻል። እንዲሁም በዚሁ ዐውድ ውስጥ ሐዋርያው ብሉያትን ጠቅሶ፣ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም" (ቍጥር 11) ይላል[93]። የማያፍረው ጌትነቱን እንዲሁም ከሙታን መነሣቱን የሚያምን ሰው ነው። በዚሁ ዐውድ ሐዋርያው ለትምህርቱ ማጠናከሪያ የጠቀሰው የኢሳይያስ 28÷16 ምንባብ እንዲህ ይላል፣ "'እነሆ፤ ሰዎች እንዲደናቀፉ የሚያደርግ ድንጋይ፣ እንዲወድቁ የሚያደርግ ዐለት፣ በጽዮን ላይ አስቀምጣለሁ፤ በእርሱም የሚያምን አያፍርም'"። አይሁድ የተሰናከሉበትና የወደቁበት ድንጋይ/ዐለት ኢየሱስ ነው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ምንባቦች ይመለከቷል ማቴዎስ 21÷42-44፤ ማርቆስ 12÷10-12፤ ሉቃስ 20÷17-18፤ ሐዋርያት ሥራ 4÷10-12፤ 1ጴጥሮስ 2÷6-8፤ ኤፌሶን 2÷20)።

በመቀጠል ሐዋርያው እንዲህ ይላል፣ "በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ልዩነት የለም፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፤ የሚለምኑትንም አብዝቶ ይባርካል" (ሮሜ 10÷12)። ሐዋርያው፣ ለድነት ክርስቶስን ማመን ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብም ጭምር ነው፤ ምክንያቱም፣ "አንዱ ጌታ የሁሉም ጌታ ነውና" ("ኩርዮስ" "κύριός")። ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ ነው ብሎ መጥራት ጸሎትና የእምነት አቋም እንጂ እንዲያው ዝም ብሎ በዋዛ ፌዛዛ የሚቀርብ የስማ በለው ዐይነት ጥሪ አይደለም (1ቆሮንቶስ 1÷2)።

በዚህ ዐውድ ጳውሎስ ለሦስተኛ ጊዜ ኢየሱስን ክርስቶስን ጌታ ይለዋል፣ "'የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል'" (ሮሜ 10÷13)። ይህ ክፍል የተጣቀሰው ከኢዩኤል 2÷32 ሲሆን፣ ጴጥሮስ በመጀመሪያው ክርስቲያናዊ ስብከቱን ባቀረበ ጊዜ ብሉያትን የጠቀሰው የመጀመሪያ

[92] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place*, 161.

[93] "ጋር ሂ ግራፌ" ("γὰρ ἡ γραφή") የሚለው ሐረግ፣ ሐዋርያው ለትምህርቱ ማናከሪያ ብሉያትን መጥቀሱን የሚያሳይ ነው።

ክፍል ነው (ሐዋርያት ሥራ 2÷21)። ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንኑ የብሉይ ኪዳን ክፍል በመጥቀስ የኢየሱስን ጌታ ነው ብሎ የሚያምን ሰው ድነት እንደሚያገኝ ይገልጻል። በዚህ ዐውድ ጌታ የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ሆነ ድረስ እንዲሁም ይህ ጌታ ከኢዩኤል ጋር ተጣቅሶ መቅረቡ ጌታ የሚለው ስም ከብሉይ ኪዳኑ ያህዌ ከሚለው ስም ጋር እኩል እንደ ሆነ ያመለክታል[94]።

ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልእክቶቹ ውስጥ ለርካታ ጊዜ፣ ኢየሱስን ከብሉይ ኪዳኑ አብ ጋር አቻ ባደረገ መልኩ "ጌታ" ሲለው እናነባለን። በአንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ አንድ ላይ ብቻ በ10 ቁጥሮች ውስጥ ሦስት ጊዜ ኢየሱስ፣ "ጌታ" ተብሎ ሲጠራ እንመለከታለን። "በቆሮንቶስ ላለችው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ተቀድሰው፣ የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ሆነው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት" (1ቆሮንቶስ 1÷2) የሚለው የጳውሎስ አነጋገር የጌታን ስም መጥራት ከአምልኮ ጋር በተያያዘ መልክ የቀረበ ነው። ይህ ደግሞ ብሉያት የያህዌን ስም እንድንጠራ ከሚያስተምሩን ምንባባት ጋር የሚነጻጸር ነው (ለምሳሌ ኢዮኤል 2÷32 ላይ ያለውን ክፍል ሐዋርያው ከኢየሱስ ጋር ያያይዘዋል ሮሜ 10÷13)። ከጥቂት ቁጥሮች በኋላ፣ "በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ያለ ነቀፋ እንድትገኙ እርሱ እስከ መጨረሻው ድረስ አጽንቶ ይጠብቃችኋል" (1÷8 ከ5÷5 ጋር ያነጻጽሯል) የሚለው የሐዋርያው አነጋገር በተለይ ደግሞ "ያለነቀፋ" ("አኔንክሌቶስ" ἀνεγκλήτους) የሚለው ቃል፣ በብሉይ ኪዳን የሚቀርበውንና ነቀፋ የሌለበትን የመሥዋዕት እንስሳ የሚያሳይ ሲሆን፣ ይህ የፍርድ ቀን ብሉያት "የያህዌ ቀን" (ለምሳሌ ኢዮኤል 1÷15፤ 2÷1:11:31) ሲሉት፣ ሐዲስ ኪዳን ደግሞ፣ "የጌታ ቀን" ይለዋል (በኢዮኤል 1÷2 ላይ "የጌታን ስም መጥራት" እና "የጌታ ቀን" በአንድ ምንባብ ውስጥ ተነጻጽረው መገኘታቸውን ልብ ይሏል፤ የሐዋርያው ጳውሎስም ንግግር ይህን ክፍል ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይችላል)። ሐዋርያው በመልእክቶቹ ውስጥ ስለዚህ መጻኢ የጌታ ቀን በተደጋጋሚነት ተናግሮአል (2ቆሮንቶስ 1÷14፤ ፊልጵስዩስ 1÷6:10፤ 1ተሰሎንቄ 5÷2፤ 2ተሰሎንቄ 2÷1-2፤ 2ጢሞቴዎስ 1÷18)[95]።

ከላይ በተመለከትነው ትርጉሙ ሐዋርያው ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ የሚልባቸው በርካታ ምንባባት አሉ[96]:—

- ሐዋርያው ትንቢተ ኤርምያስን ጠቅሶ እግዚአብሔርን ብቻ ትምክህት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ከገለጸ በኋላ (ለምሳሌ ኢዮኤል 1÷15፤ 2÷1:11:31)፣ የቆሮንቶስ መልእክቱን፣ “ክርስቶስና እርሱም ብቻ እንደ ተሰቀለ” (1ቆሮንቶስ 1÷31፤ 2÷2) መወቅ ዋነኛ ጉዳይ ነው ሲል ይገልጸዋል። እንደ ሐዋርያው ገለጻ የተሰቀለው ኢየሱስ “የክብር ጌታ”

---

[94] ሁሉም የግሪክ ዕደ ክታባት “ጌታ” (“ኩርዮስ” “κύριός”) የሚሉ ቢሆንም እንዲሁም “ያህዌ” የሚል አንዳችም ጥንታዊ የግሪክ ዕደ ክታብ በሌለበት ሁኔታ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ያሳተመው የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም “ጌታ” የሚለውን ቃል ያህዌ/ጆሆቫ ብሎ ተርጉሞታል። ይህ ዐይነቱ ለውጥ ኢየሱስን ያህዌ/ጆሆቫ ነው ለማለት ተፈልጎ ሳይሆን፣ ክፍሉ ስለ ኢየሱስ ሳይሆን ስለ አብ የሚናገር ነው ለማለት ነው። አስገራሚው ጉዳይ ድርጅቱ ሮሜ 10÷9 እንዲሁም ቁጥር 12 “ጌታ” የሚለውን ቃል ቢጠቀምም እንዲሁም “ጌታ” የሚለው ቃል ኢየሱስን እንደሚያመለክት ቢስማማም ከዚህ በተቃረነ መልኩ ቁጥር 13 ስለ አብ የሚናገር ነው የሚለው ትምህርቱ አንዳችም ድጋፍ የለውም።

[95] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place*, 162-63.

[96] ዝኒ ከማሁ፤ 163-165።

(1ቆሮንቶስ 2÷8) ነው:: ሐዋርያው የነቢዩ ኤርምያስን ቃል ጠቅሶ፣ "በጌታ ታመኑ" የሚለው ንግግሩ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያሳይ ከሆነ፣ (እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ገላትያ 6÷14፤ ፊልጵስዩስ 3÷3) ኢየሱስ ጌታ መባሉ ብሉያት ያህዌን በሚያመለክቱበት መንገድ ነው፤ ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚያሳይ ነው::

- ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "የእግዚአብሔርን መንፈስ የተረዳ፣ አማካሪውስ ሆኖ ያስተማረው ማነው?" የሚለውን የኢሳይያስ 40÷3ን ምንባብ በመጥቀስ፣ "እኛ ግን የክርስቶስ ልብ (አስተሳሰብ) አለን" (1ቆሮንቶስ 2÷16) ይላል:: ይህ ማለት የእግዚአብሔር አስተሳሰብ ማወቅ የምንችለው እርሱ ራሱ ሐሳቡን ሲገልጽልን ብቻ ነው ማለት ነው:: በኢሳይያስ መጽሐፍ ያህዌ የሚለው ምንባብ በሐዲስ ኪዳን ኢየሱስን ለማመልከት "ጌታ" ተብሎ መቅረቡ እንዲሁም፣ "ያህዌን ማወቅ" "ጌታን ከማወቅ" ጋር መነጻጸሩ የኢየሱስን አምላክነት የሚያስተምር ነው::
- ሐዋርያው ሒስ የሚሰነዝሩበትን ሰዎች አስመልክቶ፣ "በእኔ ላይ የሚፈርድ ጌታ ነው" (1ቆሮንቶስ 4÷4) በሚለው ንግግሩ "ጌታ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው፤ ምክንያቱም የሐዲስ ኪዳን ምንባባት ኢየሱስ በፍርድ ወንበር ላይ የሚቀመጠው እርሱ እንደ ሆነ በግልጽ ይናገራሉና (1ቆሮንቶስ 1÷8 ያስታውሷል፤ እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል 1ቆሮንቶስ 11÷32፤ 2ቆሮንቶስ 5÷10):: "ስለዚህ ጊዜው ሳይደርስ በምንም ነገር አትፍረዱ፤ ጌታ እስኪመጣ ጠብቁ:: እርሱ በጨለማ ውስጥ የተሰወረውን ወደ ብርሃን ያመጣዋል፤ በሰዎች ልብ ውስጥ ያለውንም ሐሳብ ይገልጠዋል" (1ቆሮንቶስ 4÷5):: ይህን የሚያደርገው ጌታ ኢየሱስ ከሆነ እንዲሁም ብሉያት ይህን የሚያደርገው ያህዌ እንደ ሆነ መግለጻቸው (1ነገሥት 8÷39፤ 1ዜና 28÷9፤ መዝሙር 96÷13፤ 139÷23-24፤ ምሳሌ 16÷2፤ 17÷3፤ ኤርምያስ 17÷10)፣ "ጌታ" የተባለው ኢየሱስ ከያህዌ ጋር ተነጻጽሮ እንደ ቀረበ፣ የሚያስተምር ሲሆን፣ ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚያሳይ ይሆናል::
- የብሉይ ኪዳን ጉባኤዎች በያህዌ ስም የሚጠሩ ሲሆን፣ የሐዲስ ኪዳን ጉባኤዎች የሚሰበሰቡት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም (1ቆሮንቶስ 5÷4፤ ሮሜ 16÷16) መሆኑ፣ ጌታ ስያሜ ከያህዌ ጋር የሚነጻጸር ይህም ጌታ የተባለውን ኢየሱስ ከያህዌ ጋር እኩል የሚያደርገው ይሆናል::
- ብሉያት ሰዎች ሁሉ የሚጸድቁት በያህዌ እንደ ሆነ የሚገልጹ (ለምሳሌ ኢሳይያስ 45÷25) ሲሆን፣ የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች (ለምሳሌ 1ቆሮንቶስ 6÷11) ደግሞ ጽድቅ በጌታ በኢየሱስ ብቻ መሆኑን መግለጻቸው፣ ጌታና ያህዌ በተመሳሳይ ዐውድ ውስጥ መነጻጸራቸውን ይህም ጌታ የተባለው ኢየሱስ ከያህዌ ጋር እኩል መሆኑን የሚያሳዩን ናቸው::
- "ብቻ እያንዳንዱ ሰው ጌታ እንደ ወሰነለት፣ እያንዳንዱም እግዚአብሔር እንደ ጠራው በዚያው ይመላለስ" (1ቆሮንቶስ 7÷17) ይህ ምንባብ ለድነት የሚጠራ እግዚአብሔር አብ እንደ ሆነ ሁሉ፣ የሰዎችን ዕድል ፈንታ የሚወስነው ደግሞ "ጌታ" ኢየሱስ መሆኑን ይገልጻል:: በዚህ ዐውድ "ጌታ" የተባለው ኢየሱስና "እግዚአብሔር" የተባለው አብ መለኮታዊ ባሕርያትን በሚያሳይ መልኩ ተነጻጽረው መገኘታቸው (ይኸውም የሰዎችን መጻኢ ዕድል ፈንታ ለዘላለም መወሰን እንዲሁም ሰብአውያንን ለድነት መጥራት) የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚያስተምር ነው::
- 1ቆሮንቶስ 7÷32-35 ባለው ክፍል ጌታን ደስ ስለማሰኘት የሚናገር ሲሆን፣ የብሉይ ኪዳን ምንባባት ደግሞ፣ የሕይወት ቀዳሚይ ግብ ያህዌን ደስ ማሰኘት እንደ ሆነ ያስተምራሉ (ለምሳሌ ዘፀአት 15÷26፤ ዘዳግም 6÷18):: በተጨማሪም በ1ቆሮንቶስ 7÷35 ላይ፣

"ዩፓርዴሮን" (εὐπάρεδρον) የሚለው የግሪክ ቃል በአዲሱ መደበኛ ትርጉም፣ "ልባችሁ ሳይከፈል" ተብሎ የተተረጐመ ሲሆን፣ በዚሁ በጳውሎስ መልእክት ውስጥ "በቤተ መቅደስ የሚያገለግሉ ምግባቸውን ከቤተ መቅደስ እንደሚያገኙ፣ በመሠዊያውም የሚያገለግሉ ከመሥዋዕቱ እንደሚካፈሉ አታውቁምን?" (1ቆሮንቶስ 9÷13) በሚለው ምንባብ "ፓርድሩዌንቴስ" (παρεδρεύοντες) የሚለው የግሪክ ቃል "የሚያገለግሉ" የሚለውን ቃል ተክቶአል:: ሐዋርያው በእነዚህ ምንባባት ሃይማኖታዊ የሆነው አገልግሎት ለጌታ ኢየሱስ እንደሚሰጥ ሲገልጽ ብሉያት ደግሞ ለያህዌ እንደሚቀርብ ያስተምራሉ:: ይህ ንጽጽር ጌታ የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ያህዌ ከሚለው ቃል ጋር አቻ እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው::

- "የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ በአንድ ላይ መጠጣት አትችሉም፤ ከጌታ ማዕድና ከአጋንንት ማዕድ ተካፋይ መሆን አትችሉም" (1ቆሮንቶስ 10÷21) በሚለው የሐዋርያው ማስጠንቀቂያ ላይ፣ "የጌታ ጽዋ" የሚለው ሐረግ፣ የጌታን ራት የሚያመለክት ነው (1ቆሮንቶስ 10÷16፤ 11÷20):: "የጌታ ማዕድ/ገበታ" የሚለው አገላለጽ በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን መሥዋዕት የሚያመለክት ነው (ሚልክያስ 1÷7:12):: ሐዋርያው የጌታን ራት ለሰይጣን ከሚሠዋው ከአረማውያኑ ሐሰተኛ አምልኮ ጋር ማነጻጸሩ (1ቆሮንቶስ 10÷20፤ ዘዳግም 32÷21) አረማዊውን አምልኮ ከክርስቲያናዊው አምልኮ ጋር ማነጻጸሩ ጌታ የተባለው ኢየሱስ አምልኮ እንደሚቀርብለት ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚያመለክት ነው:: ሐዋርያው ክርስቲያናዊውን አምልኮ ለጣዖት ከሚቀርበው አምልኮ ጋር በማነጻጸር፣ "ጌታን እናስቀናውን?" (1ቆሮንቶስ 10÷22) የሚለው አነጋገሩ፣ በዘዳግም 32÷21 ላይ ሕዝበ እስራኤል አምላኩን ያህዌን ትቶ ለጣዖት በመሠዋቱ ምክንያት እግዚአብሔር፣ "አምላክ ባልሆነው አስቀኑኝ፤ በከንቱ ጣዖቶቻቸው አስቈጡኝ" የሚለውን ንግግሩን ታሳቢ ያደረገ ነው:: "ማዕድ"፣ "አምልኮ"፣ "አምላክን"፣ "ማስቀናት" ወዘተ የሚሉት ቃላት፣ በብሉይ ኪዳን አምልኮ ለያህዌ ብቻ እንደ ሆነ ሁሉ፣ በሐዲስ ኪዳን እውነተኛ አምልኮ ለጌታ ኢየሱስ ተደርጎ መቅረቡን የሚያመለክት ሲሆን፣ ጌታ የተባለው ኢየሱስ በብሉያት አብ ያህዌ የተባለበትን አካሄድ የተከተለ ሆኖ እናገኘዋለን፤ ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚያመለክት ነው::
- ሐዋርያው፣ በአንደኛ ቆሮንቶስ 16÷22-23 ባለው የመለእክቱ ማጠናቀቂያ ክፍል፣ "ጌታን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን:: ጌታ ሆይ፤ ና! የጌታ ኢየሱስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን" በተለይ፣ "ጌታን የማይወድ ሰው የተረገመ ይሁን" የሚለው አነጋገሩ እንዲሁም ጌታ በቶሎ እንዲመጣ ወደ ጌታ ጸሎት የሚያደርሰው ንግግሩ፣ አምላካዊ ባሕርይ የሆኑትን ጸሎትን መሰማትንና "እግዚአብሔር አምላክህን ብቻ መውደድን" (ዘዳግም 6÷5 ጀምሮ ያለውን ክፍል ይመለከቷል) መሠረት ያደረጉ ናቸው:: ይህ ጉዳይ፣ "ጌታ" የተባለው ፍጹም ኢየሱስ አምላክ መሆኑን የሚያስተምር ነው::

እንደ አንደኛ ቆሮንቶስ ሁሉ፣ የሐዋርያው የጳውሎስ በፊልጵስዩስ መልእክቱም ኢየሱስ ክርስቶስን "ጌታ" እያለ ከአብ ጋር እኩል ያደረጋባቸው ምንባባት አሉ:: ነገር ግን ጥናታችን ዳሰሳዊ ከመሆኑ የተነሣ ፊልጵስዩስ 2÷9-11 ያለውን ምንባብ ብቻ ለማየት እንሞክራለን[97]::

[97] የሚለው የብሉይ ኪዳንን ዐውድ በተከተለ መንገድ ኢየሱስ "ጌታ" (ግሪክ "ኩርዮስ" κύριος) መባሉ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ያሳያል በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ሰፊ ጥናት ከፈለጉ የሚከተሉትን መጻሕፍት ይመለከቷል:— David B. Capes, *Old Testament Yahweh Texts in Paul's Christology,* WUNT 2.47 (Tübingen: Mohr, 1992) ይህ የዶክተር ካፐስ መጽሐፍ፣ ጀርመን አገር በሚገኘው የቱቢንገን ዩኒቨርስቲ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ ሲሆን፣ አብዛኛው ሰው ሊጠቀምበት በሚችል መንገድ ተዘጋጅቶ ለንባብ የቀረበ ነው:: Gordon D. Fee, *Pauline Christology: An Exegetical-*

ከቍጥር 9-11 ባለው ክፍል ኢየሱስ ክርስቶስ በጽንፈ ዓለሙ ውስጥ ያለውን ቦታ እንዲህ ሲል ይገልጻል:—

> "ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፤ ይኸውም በሰማይና በምድር፣ ከምድርም በታች፣ ጕልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከክ ዘንድ፣ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው"::

ከዚህ ምንባብ ሁለት መሠረታዊ ቍም ነገሮችን እንማራለን፤ ይኸውም:— (1) ይህ ክፍል ኢየሱስ ክርስቶስ ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ ስም እንዳለው እንዲሁም ይህ ስም "ጌታ" (ግሪክ "ኩርዮስ" "κύριος") የሚለው ስም መሆኑን (በዕብራውያኑ ዐውድ ውስጥ ይህ ስም ያህዌ የሚለው ስም ነው):: (2) በዚህ ክፍል "ጌታ" የሚለው ስም፣ በብሉይ ኪዳን "ያህዌ" የሚለው ስም ከቀረበበት ዐውድ ጋር በንጽጽር መቅረቡ "ጌታ" የተባለውን ኢየሱስን ፍጹም አምላክ መሆኑን የሚያሳይ ነው:: (3) "ጕልበት ሁሉ" የሚንበረከክለት፣ "ምላስም ሁሉ ጌትነቱን የሚመሰክርለት" የብሉይ ኪዳን "ያህዌ" (ኢሳይያስ 45÷23) በአዲስ ኪዳን ደግሞ "ጌታ" ኢየሱስ (ፊልጵስዩስ 2÷10-11) መሆኑ የኢየሱስን አምላክነት ፍንትው አድርጐ የሚያሳይ ነው:: የሚከተሉትን ሁለት ምንባባት ያነጻጽሯል:—

| ምንባብ | (በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም) | አማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|
| **ኢሳይያስ** 45÷23 | κάμψει πᾶν γόνυ καὶ ἐξομολογήσεται πᾶσα γλῶσσα | **ጕለበት ሁሉ በእኔ ፊት ይንበረከካል፤ አንደበትም ሁሉ በእኔ ይምላል::** |
| ምንባብ | (በሐዲስ ኪዳን ግሪክ) | አማርኛ ትርጉም |
| **ፊልጵስዩስ** 2÷10-11 | ἵνα ἐν τῷ ὀνόματι Ἰησοῦ πᾶν γόνυ κάμψῃ ἐπουρανίων καὶ ἐπιγείων καὶ καταχθονίων καὶ πᾶσα γλῶσσα ἐξομολογήσηται ὅτι κύριος Ἰησοῦς Χριστὸς εἰς δόξαν θεοῦ πατρός. | **ይኸውም ለኢየሱስ ክርስቶስ ስም *ጕልበት ሁሉ ይንበረከካል*** [πᾶν γόνυ κάμψῃ] **በሰማይም ሆነ በምድርም እንዲሁም ከምድር በታች፤ *ምላስም ሁሉ* ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ *ያውጅ ዘንድ*** [καὶ πᾶσα γλῶσσα ἐξομολογήσηται]:: |

ዶክተር ዴቪድ ካፕስ ይህን ጕዳይ አስመልክተው እንዲህ ይላሉ:—

> "ጕልበት ሁሉ ይንበረከካል"፣ "ምላስም ሁሉ ይምሰክራል" የሚሉት ዐረፍተ ነገሮች ለብሉይ ኪዳኑ የአሐዱ አምላክ ሃይማኖት መሠረቶች ከመሆናቸውም በላይ ዐረፍተ ነገሮቹ በቀጥታ ያህዌን የሚያመለክቱ ናቸው[98]::

---

*Theological Study* (Peabody, MA: Hendrickson, 2007). ይህ የፕሮፌሰር ፊ መጽሐፍ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን "ጌታ" ባለባቸው ምንባባት ላይ ሰፊ ትንተና ያቀርባል::

[98] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place,* 167. ከDavid B. Capes, *Old Testament Yahweh Texts in Paul's Christology,* WUNT 2.47 (Tübingen: Mohr, 1992), 159. ጠቅሰው እንደ ጻፉት::

**በ**እነዚህ ሁለት ምንባባት ላይ የተቀመጡት ቁልም ነገሮች በርካታ የነገረ መለኮት ምሁራን “ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው” የሚለውን ምንባብ (ፊልጵስዩስ 2÷9-11) ልክ እንደ አብ ኢየሱስ ክርስቶስም ያህዌ ነው እንዲሉ አድርገዋቸዋል[99]::

**አ**ንዳንድ ሰዎች፣ “ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲንበረከክ እንዲሁም ምላስ ሁሉ ጌታ ነው እንዲል ***የሰጠው***” እግዚአብሔር አብ (ቁጥር 9) ነው፤ ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ “ጌታ” መባሉም ሆነ “ጉልበት ሁሉ ለእርሱ መንበርከኩ” ፍጹም አምላክ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም የሚል የሙግት ነጥብ አላቸው:: ነገር ግን ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ሚዛን ሊደፋ የማይችልበት ምክንያት:—

***(1)*** ለክብሩ የሚቀናው አምላክ “ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም ከእኔ በኋላም አይሆንም” እንዲሁም “”ክብሬን ለማንም አልሰጥም" የሚሉትን የብሉይ ኪዳን ምንባባት (ለምሳሌ ኢሳይያስ 43÷10፤ ዘፀአት 20÷2-7) ያመሳከረ ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ***(2)*** በፊልጵስዩስ ምዕራፍ ሁለት ዐውድ ውስጥ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን፣ "ከፍ ከፍ" በማድረግ "ጌታ" የሚለውን ከስም ሁሉ በላይ ስም የሰጠበት እንዲሁም "ጉልበት ሁሉ እንዲንበረከክለት" ያደረገበት ዐቢይ ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ "በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው የማይገባ ነገር አድርጎ ስላልቈጠረው" (ፊልጵስዩስ 2÷6) በሌላ አገላለጽ፣ "ራሱን ባዶ" ስላደረገ እንዲሁም ***(3)*** ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ ትስብእት፣ ትስብእትም ሆነ ድኅረ ትንሣኤ፣ "ዘላለማዊ የሆነ አምላክ እንደ ሆነ" በግልጽ ማስተማራቸው (ለምሳሌ ዮሐንስ 1÷1:18፤ 20÷28፤ ዕብራውያን 1÷8) ኢየሱስ ክርስቶስ ከስም ሁሉ በላይ ስም የተሰጠው እንዲሁም ጉልበት ሁሉ የተንበረከከለት በዘመነ ሥጋዌ ራሱን ባዶ በማድረጉ ብቻ ነው ማለት ስሕተት ነው::

***በሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክትም*** ውስጥ ኢየሱስ ከያህዌ ጋር በተስተካከለ መንገድ ቢያንስ በሁለት ምንባባት ውስጥ “ጌታ” ተብሎ ተጠርቶአል:: ሐዋርያው ጴጥሮስ አዳዲስ አማኞች በእምነታቸው ይጸኑ ዘንድ በጻፈው የማበረታቻ መልእክት ውስጥ፣ “ጌታ መልካም መሆኑን ቀምሳችኋልና” (1ጴጥሮስ 2÷3) ይላል:: ይህ ምንባብ መዝሙር 34÷8 ላይ፣ “እግዚአብሔር ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እዩ” የሚለውን ምንባብ ተሳቢ ያደረገ ነው:: 1ጴጥሮስ 2÷3 ላይ “ጌታ” የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስን ነው (ቁጥር 4 ይመለከቷል):: ሐዋርያው፣ “ሕያው ድንጋይ” የሚሉትን የብሉይ ኪዳን ምንባባት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሚያመለክቱ ገልጾአል (ለምሳሌ ቁጥር 6-8 ያለውን ክፍል ከኢሳይያስ 28÷16፤ መዝሙር 118÷22፤ ኢሳይያስ 8÷14 ጋር ያወዳድሯል):: በተለይ ኢሳይያስ 8÷14-14 ላይ ያለው ክፍል፣ "ሕያው ድንጋይ" የሚለው ገለጻ ያህዌን የሚያመለክት ነው:—

> “'እነዚህ ሰዎች፣ አድማ' ብለው የሚጠሩትን፣ ማንኛውንም ነገር፣ 'አድማ' አትበሉ፤ እነርሱ የሚፈሩትን አትፍሩ፤ አትሸበሩለትም:: ልትቀድሱ የሚገባው የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔርን ብቻ ነው፤ ልትፈሩት የሚገባው እርሱን ነው፤ ልትንቀጠቀጡለት የሚገባውም እርሱ ነው:: እርሱም መቅደስ ይሆናል፤ ለሁለቱ የእስራኤል ቤት ግን

[99] ዝኒ ከማሁ::



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

*የሚያደናቅፍ ድንጋይ የሚያሰናክልም ዐለት ይሆንባቸዋል፤ ለኢየሩሳሌም ሕዝብም ወጥመድና አሽክላ ይሆናል"።*

**ሐዋርያው ጴጥሮስ "የሚያሰናክል፣ የሚጥላቸውም ዐለት" (1ጴጥሮስ 2÷8) የሚለው ገለጻው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ በተጨማሪም 1ጴጥሮስ 3÷10-12 ከመዝሙር 34÷12-16 ካለው ክፍል መጠቀሱ እንዲሁም ቍጥር 3 ላይ ኢየሱስን ጌታ ማለቱ ኢየሱስን ያህዌ ከሚለው ስም ጋር አቻ የሚያደርግ ነው።**

| ምንባብ | (በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም) | አማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|
| **ኢሳይያስ** 8÷12-13 | τὸν δὲ φόβον αὐτοῦ οὐ μὴ φοβηθῆτε οὐδὲ μὴ ταραχθῆτε,<br><br>κύριον αὐτὸν ἁγιάσατε, | **ነገር ግን እነርሱ የሚፈሩትን ነገር አትፍሩ አትታወኩም፤**<br><br>**ነገር ግን ራሱን ጌታ ቅዱስ አድርጋችሁ** |
| ምንባብ | (በሐዲስ ኪዳን ግሪክ) | አማርኛ ትርጉም |
| **1ጴጥሮስ** 3÷13-15 | τὸν δὲ φόβον αὐτῶν μὴ φοβηθῆτε μηδὲ ταραχθῆτε,<br><br>κύριον δὲ τὸν Χριστὸν ἁγιάσατε | **ነገር ግን እነርሱ የሚፈሩትን ነገር አትፍሩ አትታወኩም፤**<br><br>**ነገር ግን ክርስቶስን ቅዱስ አድርጋችሁ** |

**ኢሳይያስ "እርሱ ራሱን" ("አውቶን" "αὐτὸν") ሲል ጴጥሮስ "ክርስቶስን" ("ክርስቶን" "Χριστὸν") ከማለት ውጪ በኢሳይያስ 8÷12-13 እና በ1ጴጥሮስ 3÷13-15 ባሉት ክፍሎች ውስጥ አንዳችም ልዩነት የለም። ኢየሱስ "ቅዱስ" የሆነ "ጌታ" መሆኑን ይህ ደግሞ ኢየሱስን ከያህዌ ጋር አቻ እንደሚያደርገው የሚያስተምር ነው።**

**በአጠቃላይ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ ያሉበት ዐውድ ብሉያት አብን ያህዌ በሚሉበት ዐውድ መሆኑ እንዲሁም የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን "ኢየሱስ ጌታ ነው" የሚለው ዐዋጅዋ "የናዝሬቱ ኢየሱስ ያህዌ ነው" የሚለውን መሠረተ እምነቷን የሚወክል ነው[100]።**

**[100] "የኢትዮጵያ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመባል የሚታወቀው ሳባልዮሳዊ አስተምህሮ ያለው መናፍቃዊ ድርጅት፣ "ኢየሱስ ያህዌ ነው" የሚለውን ይህን ትምህርት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር አብ ተብሎ የሚጠራው ነው በሌላ አገላለጽ አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው ለሚለው የተሳሳተ ድምዳሜ እንደ ግብአት ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ ልክ እንደ አብ ፍጹም አምላክ ነው ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አብ ነው ማለት በፍጹም አይደለም። "ተስፋዬ መምህር ነው" "አማረ መምህር ነው" ማለት ተስፋዬ የሚባለው ሰው አማረ ተብሎ የሚጠራው ሰው ነው ማለት አይደለም። ነገር ግን እነዚህ ግለሰቦች የማስተማርን ባሕርይ ይጋራሉ ማለት እንጂ። "አብና ወልድ አንድ አካል ናቸውን?" በሚለው ርእስ ሥር የአብና የወልድን አካላዊ ልዩነት በሰፊው ለማየት እንሞክራለን።**

# III. "አልፋና ዖሜጋ" (Ἄλφα καὶ τὸ Ὦ) ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንታኔ

ኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጥሮአል የሚለው አርዮሳዊ ትምህርት፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ የሚያስተምሩትን ትምህርት መሠረት ያደረገ አይደለም። ብሉያት እግዚአብሔር አብ አልፋና ዖሜጋ መሆኑን እንደሚያስተምሩት ሁሉ፣ ሐዲስ ኪዳንም ኢየሱስ ክርስቶስ አልፋና ዖሜጋ እንደ ሆነ ያስረዳል። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር አብ ጅማሬ እንደሌላው ሁሉ፣ ኢየሱስም ጅማሬ የሌለው አምላክ መሆኑን የሚያስተምር ነው።

"አልፋና ዖሜጋ" የሚለው ስያሜ በሐዲስ ኪዳን ምንባባት ውስጥ በራእይ ዮሐንስ ላይ ብቻ የሚገኝ ሲሆን[101]፣ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተለይ በትንቢተ ኢሳይያስ ላይ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል፣ "እኔ እግዚአብሔር ከፊተኛው ከኋለኛውም ጋር እኔው ነኝ...የፊተኛውም እኔ ነኝ የኋለኛውም እኔ ነኝ...እኔ እኔ ነኝ፤ ፊተኛው እኔ ነኝ፤ ኋላኛውም እኔ ነኝ" (ኢሳይያስ 41÷4፤ 44÷6፤ 48÷12)። በትንቢተ ኢሳይያስ እግዚአብሔር "እኔ ፊተኛና ኋላኛ ነኝ" ያለበት ዐውድ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነው ሕዝበ እስራኤል፣ ለተሐድሶ ታላቅ የሆነ አይቀሬ ተስፋ እንዳለው በሚናገርበት ክፍል ነው።

የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ፣ "አልፋና ዖሜጋ"፣ "ፊተኛውና ኋላኛው"፣ "መጀመሪያውና መጨረሻው" የሚለውን ስያሜ ለኢየሱስ ጥቅም ላይ ማዋሉ፣ የሚያሻማ ጉዳይ አይደለም። ለምሳሌ፣ "አትፍራ፤ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም እኔ ነኝ፤ እኔ ሕያው ነኝ፤ ሞቼ ነበር፤ እነሆ አሁን ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፤ የሞትና የሲኦል መክፈቻም በእጄ ነው" (ራእይ 1÷17-18)። "የመጀመሪያውና የመጨረሻው ሞቶም የነበረውና ሕያው የሆነው እንዲህ ይላል" (ራእይ 2÷8)።

እነዚህ ምንባባት የተነገሩት ኢየሱስ በሞቱና በትንሣኤው ሞትን ድል እንደ ነሣ እንዲሁም በእርሱ ተስፋ የሚያደርጉ ሰዎች ልክ እንደ እርሱ በመጨረሻ ሞትን ድል እንደሚነሡ በሚያስተምሩ ዐውዶች ውስጥ ነው። በዚህ መልኩ ሲታይ በኢሳይያስም ሆነ በዮሐንስ ራእይ ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው ተመሳሳይ መልእክት በወከሉ ዐውደ ምንባቦች ውስጥ ነው።

አንዳንድ ግለሰቦችም ሆኑ የሃይማኖት ድርጅቶች አልፋና ዖሜጋ፣ መጀመሪያውና መጨረሻው (ራእይ 1÷8፤ 21÷6) የሚሉት ስያሜዎች ጥቅም ላይ የዋሉት፣ ለሁሉን ቻዩ አምላክ ለአብ እንጂ፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ አይደለም ባዮች ናቸው። ነገር ግን በዚያው ዐውድ ውስጥ በማያሻማ መልኩ ስያሜው ለኢየሱስ ክርስቶስ ጥቅም ላይ ውሎ እናገኘዋለን፡—

> "እነሆ ቶሎ እመጣለሁ፤ ዋጋዬ በእኔ ዘንድ አለ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍለዋለሁ። አልፋና ዖሜጋ፣ ፊተኛውና ኋላኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ" (ራእይ 22÷12-13)።

[101] ዕብራውያን 12÷2 ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "የእምነታችን ራስና ፈጻሚ" (ἀρχηγὸν καὶ τελειωτὴν) ነው የሚለው ዐረፍተ ነገር ከዚህ ስያሜ ጋር ተያያዥነት ቢኖረውም አልፋና ዖሜጋ የሚለው ስያሜ ግን የሚገኘው በራእይ ዮሐንስ ላይ ብቻ ነው።



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

“እነሆ በቶሎ እመጣለሁ” የሚለው ማነው የሚለው ጉዳይ ለዚህ ውይይት መሠረታዊ ነው:: ይህን ቃል የሚናገረው አብ ነው ወይስ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ራእይ መልስ ይሰጣል፣ “እነዚህን ነገሮች የሚመሰክረው 'አዎ ቶሎ እመጣለሁ' ይላል:: አሜን፤ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና” (ራእይ 22÷20):: በዚሁ መጽሐፍ መግቢያ ላይ ኢየሱስ ራሱ እርሱን ባልታመኑ ሰዎች ላይ ለመፍረድ፣ የታመኑትን ሰዎች ደግሞ ለመሸለም እንደሚመጣ ተናግሮአል (ራእይ 2÷16፤ 3÷11):: ኢየሱስ ሰዎች በሥራቸው መጠን እንደሚከፍላቸው በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ አስታውቆአል (ራእይ 2÷23፤ 20÷13):: ስለዚህ እነሆ በቶሎ እመጣለሁ የሚለው ተናጋሪ ነው “እኔ አልፋና ዖሜጋ ነኝ” የሚለው (ራእይ 22÷12-13)::

በአጠቃላይ “አልፋና ዖሜጋ”፣ “ፊተኛውና ኋላኛው”፣ “መጀመሪያውና መጨረሻው” የሚሉት ዐረፍተ ነገሮች፣ ተመሳሳይ ትርጒም የወከሉ እንዲሁም እመጣለሁ የሚለውን አካል ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያሳዩ ናቸው:: የራእይ 1÷7-8 ክፍል ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፣ “እነሆ በደመና ይመጣል፤ የወጉት እንኳ ሳይቀሩ ዐይን ሁሉ ያየዋል፤ የምድርም ሕዝቦች ሁሉ ከእርሱ የተነሣ ዋይ ዋይ ይላሉ:: አዎ! ይህ ሁሉ ይሆናል፤ አሜን:: 'ያለውና የነበረው፣ የሚመጣውም፣ ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ፣ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ' ይላል”::

ቍጥር 7 ይመጣል የተባለለት፣ “ሁሉን ቻዩ ጌታ አምላክ” ኢየሱስ መሆኑ አያከራክርም፤ ይህ ሁሉን ቻይ የሆነው ጌታ አምላክ አልፋና ዖሜጋ መሆኑን ቍጥር 8 ያስረግጣል:: አልፋና ዖሜጋ ስለሚለው ስያሜ ማወቅ የሚገባን ሊላው ቍም ነገር፣ “አልፋና ዖሜጋ” የሚለው የማዕረግ ስም ዘላለማዊነትን አመላካች የመሆኑ ጉዳይ ነው:: “ያለ (አሁን)፣ የነበረ (ባለፉት ጊዜያት)፣ ወደ ፊትም የሚኖር (መጪውን ጊዜ)” (ራእይ 1÷4) “ያለውና የነበረው፣ የሚመጣውም” (ራእይ 1÷8)[102]:: “ያለና የነበረ” የሚለው የአልፋና ዖሜጋ ትንታኔ ያህዌ ለሚለውም ስም ትርጒም ሆኖ የቀረበ ሲሆን (ዘፀአት 3÷4 የመለከቷል):—

| ምንባባት | ግሪክ | የአማርኛ ቍም ትርጉም |
|---|---|---|
| ዘፀአት **3÷14** (በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም) | Ἐγώ εἰμι ὁ ὤν | **እኔ ያለሁ ነኝ** |
| ራእይ **1÷8** (በሐዲስ ኪዳን ግሪክ) | Ἐγώ εἰμι…ὁ ὢν | **እኔ…ያለሁ ነኝ** |

“የሚመጣው” (ግሪክ "ሆ ኤርኮሜኖስ" ὁ ἐρχόμενος) የሚለው ገለጻ ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ዐይነተኛ ባሕርይ መሆኑን ከሐዲስ ኪዳን ምንባባት ይመለከቷል (ለምሳሌ:— ማቴዎስ 11÷3፤ 21÷9፤ 23÷39፤ ማርቆስ 11÷9፤ ሉቃስ 7÷19:20፤ 13÷35፤ 19÷38፤ ዮሐንስ 6÷14፤ 12÷13፤ እንዲሁም ዕብራውያን 10÷37 ይመለቷል)::

---

102 የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ “ኀያል አምላክ” (ኢሳይያስ 9÷6) እንጂ፣ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም የሚል ትምህርት አላቸው:: ይህም “ኀያል አምላክ” የተባለው ኢየሱስ “ሁሉን ቻይ አምላክ” ከተባለው አብ ያነሰ ነው ለማለት ነው:: አስገራሚው ጉዳይ ግን ሁሉን ቻይ አምላክ የተባለው አብ ራሱ “ኀያል አምላክ” መባሉ (ኢሳይያስ 10÷21) ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስም “ሁሉን ቻይ አምላክ” ተብሎ መጠራቱ ነው (ለምሳሌ ራእይ 1÷8):: ከዚህ የምንማረው ቍም ነገር በቅዱሳት መጻሕፍት፣ “ኀያል አምላክ” በሚለው ስያሜና “ሁሉን ቻይ አምላክ” ከሚለው ስም መካከል አንዳችም ልዩነት እንደ ሌለ የሚያሳይ ነው:: ለመሆኑ የይሖዋ ምስክሮች “ኀያል አምላክ” በሚባል አምላክና “ሁሉን ቻይ አምላክ” በሚባል አምላክ የሚያምኑ የመድብለ አማልክት አምላኪዎች ናቸው ማለት ነው?



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

"የ ለ፣ የነበረ፣ ወደ ፊትም የሚኖር" የሚለው የራእይ ዮሐንስ ገለጻ፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው" (ዕብራውያን 13÷8) ከሚለው በለሦስት ፊርጅ ገለጻ ጋር ሊነጻጸር የሚችል ነው:: ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ እንደ ነበረ እንዲሁም የማይለወጥ አምላክ እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው[103]::

# IV. "ሙሽራውና ሙሽራዪቱ" (νύμφη καὶ νυμφίος) ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንታኔ

በብሉይ ኪዳን ምንባባት ያህዌ ለእስራኤል እንደ ባል ሆኖ ተገልጦአል:—

> "ባልሽ ፈጣሪሽ ነውና፤ ስሙም የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው፤ ታዳጊሽ የእስራኤል ቅዱስ ነው፤ እርሱም የምድር ሁሉ አምላክ ይባላል" (ኢሳይያስ 54÷5)::
>
> "ጐልማሳ ድንግሊቱን እንደሚያገባ፣ ልጆችሽ እንዲሁ ያገቡሻል፤ ሙሽራ በሙሽራዪቱ ደስ እንደሚለው፣ አምላክሽ በአንቺ ደስ ይለዋል" (ኢሳይያስ 62÷5)::

ነቢዩ ኢሳይያስ፣ እግዚአብሔር እስራኤል ጋር ያለውን ይህን መሰል ግንኙነት ይፋ ያደረገበት ዐውድ እስራኤል በሚያሳዝን መንገድ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን በተሳናት ጊዜ ነው:: እንደ ሌሎቹ የእስራኤል ነቢያት ሁሉ ኢሳይያስም እስራኤልን የሚያቀርባት ለትዳሯ ታማኝ እንዳልሆነች ሚስት ነው:: እስራኤል ከእግዚአብሔር ሌሎችን አማልክት ማምለኳ ወይም የአረማውያንን መድብለ አማልክት በእግዚአብሔር ላይ መደበኳ ነቢያቱ ሁሉ ራሷን ለዝሙት አሳልፋ እንደ ሸጠች ሴት አድርገው ነው ያቀረቧት (ኢሳይያስ 54÷4-8፤ 62÷4-5፤ ኤርምያስ 2÷2፤ 3÷1-14፤ ሕዝቅኤል 16÷8-63፤ 23÷1-49፤ ሆሴዕ 2÷1-3÷5):: እስራኤል ለአምላኳ ለእግዚአብሔር ታማኝ በልሆነችባቸው በእነዚህ ዐውዶች ውስጥ፣ ነቢያቱ አሻግረው የሚናገሩት እግዚአብሔር ራሱ ሕዝቡን ከእርሱ ጋር ወደሚደረግ ትክክለኛ ኅብረት እንደሚያመጣ ነው:: በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ እግዚአብሔር ሙሴያዊ ከሆነው ኪዳን በተለየ መልኩ፣ ከእስራኤል ጋር፣ "አዲስ ቃል ኪዳን እንደሚያደርግ" ይገልጻል:: ምክንያቱም የእስራኤል ልጆች ሙሴያዊውን ኪዳን አፍርሰዋልና:—

> "'ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር' ይላል እግዚአብሔር፤ 'አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ጊዜ ይመጣል:: ከግብፅ አወጣቸው ዘንድ፣ እጃቸውን ይዤ በመራኋቸው ጊዜ ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ኪዳን አይደለም፤ የእነርሱ ባል ሆኜ ሳለሁ፣ ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋልና' ይላል እግዚአብሔር" (ኤርምያስ 31÷31-32)::

ነቢዩ ሆሴዕም እስራኤል ከጥመቷ ተመልሳ አምላኳ እስራኤልን የምታመልክበት ጊዜ እንደሚመጣ ተንብዮአል:—

> "ከዚያ በኋላ እስራኤላውያን ተመልሰው አምላካቸውን እግዚአብሔርንና ንጉሣቸውን ዳዊትን ይፈልጋሉ፤ በመጨረሻውም ዘመን በመንቀጥቀጥ ወደ እግዚአብሔርና ወደ በረከቱ ይመጣሉ" (ሆሴዕ 3÷5)::

[103] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place,* 181.

በዚህ ዐውድ ዳዊት የመጠቀሱ ምክንያት በሰሜኑ ግዛት የሚገኙት እስራኤላውያን የዳዊትን ንግሥና በውል እንደሚገነዘቡ የሚያሳይ ሲሆን፣ የትንቢቱ የሩቅ ዘመን ፍጻሜ ደግሞ የዳዊት ንግሥና ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ስለሚነሣው የዳዊት ዘር ስለሆነው ስለ መሲሑ የሚናገር ነው (ሆሴዕ 3÷4፤ ኤርምያስ 30÷9፤ ሕዝቅኤል 34÷24)።

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ኢየሱስ ክርስቶስ መሲሕ ብቻ ሳይሆን፣ ሙሽራም እንደ ሆነ ያስተምራሉ። ኢየሱስ፣ ደቀ መዛሙርቱ ጾምን የማይጾሙት ለምንድን ነው የሚል ጥያቄ በተጠየቀ ጊዜ፣ "እንዲህ አላቸው፤ 'ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎቹ ሊጾሙ ይችላሉን? ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሊጾሙ አይችሉም" (ማርቆስ 2÷19)። በዚህ ክፍል ኢየሱስ ራሱን እንደ ሙሽራ ደቀ መዛሙርቱን ደግሞ እንደ ሚዜዎች አቅርቦአል።

ኢየሱስ ስለ ዐሥሩ ቈነጃጅት በተናገረው ምሳሌ ላይ (ማቴዎስ 25÷1-13)፣ ራሱን ሙሽራ አድርጎ አቅርቦአል (ማቴዎስ 25÷5:10-13 እንዲሁም የሚከተለውን ክፍል ይመለከቷል 24÷42-44)። በሌላ ስፍራ ደግሞ ኢየሱስ፣ "መንግሥተ ሰማይ ለልጁ ሰርግ የደገሰ ንጉሥ ትመስላለች" (ማቴዎስ 22÷2) ሲል ተናግሯል። በዚህ ዐውድ ደግሞ ንጉሡ እግዚአብሔር አብ ሲሆን የንጉሡ ልጅ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ሐዋርያው ዮሐንስም ኢየሱስን እንደ ሙሽራ የኢየሱስን ደቀ መዛሙርት ደግሞ እንደ ሙሽሪት አድርጎ አቅርቦአል:—

> "ሙሽራዪቱ የሙሽራው ነች፤ ድምፁን ለመስማት በአጠገቡ የሚቆመው ሚዜ ግን፣ የሙሽራውን ድምፅ ሲሰማ እጅግ ደስ ይለዋል፤ ያ ደስታ የእኔ ነው፤ እርሱም አሁን ተፈጽሞአል" (ዮሐንስ 3÷29)።

ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ ሐዋርያት ግልጽ በሆኑ ዐረፍተ ነገሮች ይህን እውነት አስቀምጠዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖች ለጌታ ታማኝ መሆን እንዳለባቸው የተናገረው ንግግር የብሉይ ኪዳን ነቢያት በተናገሩበት መልኩ ነው:—

> "በእግዚአብሔር ቅናት እቀናላችኋለሁ፤ እናንተን እንደ ንጽሕት ድንግል ለክርስቶስ ለማቅረብ ለአንድ ባል አጭቻችኋለሁና" (2ቆሮንቶስ 11÷2)።

በሌላ ስፍራ ሐዋርያው ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ሙሽራ አድርጎ አቅርቧታል:—

> "ክርስቶስ አካሉ ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት ቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ባልም የሚስቱ ራስ ነውና። ባሎች ሆይ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፣ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት እንድትቀደስ፣ እንዲሁም ጒድፍ ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዳች እንከን ሳይገኝባት ቅድስትና ነውር አልባ የሆነች ክብርት ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ለራሱ ሊያቀርባት ነው" (ኤፌሶን 5÷23:25-27)።

የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍም በቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ መካከል ያለውን ግንኙነት በባልና ሚስት መስሎ የሚያቀርብባቸው በርካታ ምንባባት አሉ:—

> "የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ፣ የእርሱም ሙሽራ ራሷን ስላዘጋጀች፣ ደስ ይበለን፤ ሐሤት እናድርግ

ክብርም እንስጠው። የሚያንጸባርቅና ንጹሕ፣ ከተልባ እግር የተሠራ ቀጭን ልብስ እንድትለብስ ተሰጣት። ከተልባ እግር የተሠራው ቀጭን ልብስ የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ ነው። መልአኩም፣ 'ወደ በጉ ሰርግ ራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው' ብለህ ጻፍ አለኝ፤ ቀጥሎም፣ 'እነዚህ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃሎች ናቸው' አለኝ" (ራእይ 19÷7-9)።

"ቅድስቲቱ ከተማ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባሏ እንደ ተዋበች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። ሰባቱ የመጨረሻ መቅሠፍቶች የሞሉባቸውን ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ፣ 'ና፤ የበጉ ሚስት የሆነችውን ሙሽራ አሳይሃለሁ' አለኝ" (ራእይ 21÷2:9)።

በዮሐንስ ራእይ ምዕራ 21 ላይ የሚገኘው፣ "የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም" በዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ትምህርት ላይ የተመሠረተች መሆኗ በትእምርታዊ ራእይ የተገለጠ ሲሆን (ራእይ 21÷14፤ ከኤፌሶን 2÷20 ጋር ያነጻጽሯል)፣ ጳውሎስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን መልአኩ የክርስቶስ ሙሽራ ሲል ይጠራታል (ኤፌሶን 5÷25-27)።

ኢየሱስን እንደ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያንን ደግሞ እንደ ሙሽሪት አድርገው ያቀረቡት እነዚህ ምንባባት፣ በብሉይ ኪዳን እስራኤልን እንደ ሚስት ያህዌን ደግሞ እንደ ባል ከሚያቀርቡበት ንጽጽር ጋር አንድ መሆኑ ልክ እንደ ያህዌ ሁሉ ኢየሱስ ፍጹም አምላክ መሆኑን የሚያስተምሩን ናቸው።

## V. "የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ" (κύριος κυρίων καὶ βασιλεὺς βασιλέων) ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንታኔ

ታላቋ ባቢሎን እንደምትጠፋና እንደሚፈረድባት በሚገልጽበት የዮሐንስ ራእይ ምንባብ (ራእይ 17-18)፣ ዮሐንስ ከአውሬው ጋር ስለሚተባበሩ ነገሥታት እንዲሁም ከአውሬው ጋር በመተባበር "እነዚህ በጉን ይዋጋሉ፤ በጉ ግን ድል ይነሣቸዋል፤ ምክንያቱም እርሱ የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ነው" (ራእይ 17÷14) ይላል። ዮሐንስ በአቡቀለምሲስ መጽሐፉ ወስጥ፣ ኢየሱስን ተምሳሌታዊ መሆነ መልክ በግ አድርጎ ያቀርበዋል (በተለይ ራእይ 5÷6-14)።

"የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ" (ግሪክ "ኩርዮስ ኩርዮን ካይ ባስሊውስ ባስልዮን" "κύριος κυρίων καὶ βασιλεὺς βασιλέων") የሚለው ገለጻ ኢየሱስ የጌቶች ሁሉ የበላይ ጌታ የነገሥታትም ሁሉ የበላይ ንጉሥ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህ ስያሜ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አብን በሚያሳይ መልኩ ተደጋግሞ ተገልጾአል፣ "አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ፣ የጌቶች ጌታ፣ ታላቅ አምላክ፣ ኀያልና የሚያስፈራ፣ አድልዎ የማያደርግ፣ መማለጃም የማይቀበል ነውና" (ዘዳግም 10÷17)፣ "የአማልክትን አምላክ አመስግኑ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። የጌቶችን ጌታ አመስግኑ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና" (መዝሙር 136÷2-3)።

ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ ኢየሱስን፣ "የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ" ሲል የጠራበት ክፍል በቀጥታ የተጣቀሰው፣ ከትንቢተ ዳንኤል 4÷37 (ከሰባዓ ሊቃናት ትርጉም) ላይ ነው[104]። በዚህ ስፍራ ነጉሡ ናቡከደነፆር እግዚአብሔር እንጂ እርሱ ታላቅ ንጉሥ እንዳይደለ ይገልጻል።

| **ዳንኤል** 4÷37<br>**(በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም)** | **ራእይ** 17÷14 |
|---|---|
| "ምክንያቱም እርሱ ብቻውን የአማልክት አምላክ"፣ "የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ነው" | "ምክንያቱም እርሱ የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ነው" |
| "ὅτι αὐτός ἐστι θεὸς τῶν θεῶν καὶ κύριος τῶν κυρίων καὶ βασιλεὺς τῶν βασιλέων" | "ὅτι κύριος κυρίων ἐστὶν καὶ βασιλεὺς βασιλέων" |

ትንቢተ ዳንኤል ጭብጥ የሚያጠነጥነው፣ የባቢሎናውያኑ ግዛተ ዐፄ እንደሚጠፉና እንደሚዋረድ በመግለጽ ነው። ዮሐንስም ስለ ባቢሎን በሚናገርበት ዐውድ ውስጥ በዚህ ክፍል የሚገኘው ምንባብ በራእዩ ውስጥ ተጠቅሶ መገኘቱ በአጋጣሚ የተከሡተ ጉዳይ ነው ሊያስብል አይችልም። ዕብራውያን በቀጥታ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚያውሉትን ስያሜ ዮሐንስ ለበጉ ለኢየሱስ ሰጥቶ መገኘቱ የኢየሱስን አምላክነት አመላካች የማይሆንበት አንዳችም ምክንያት የለም። አውሬውና እርሱን የሚረዱት ነገሥታት በመጨረሻ በእሳት ባህር ውስጥ መጣላቸው የበጉን ሉዓላዊነት አመላካች እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

## VI. "አዳኝ/መድኅኒት" (σωτηρ) ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንታኔ

በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የኢየሱስ ክርስቶስ "አዳኝ" ወይም "መድኀኒት" (ግሪክ "ሶቲር"/ "ሶቲሮስ" "σωτῆρ"/ "σωτῆρος") በሚለው ስያሜ በርካታ ጊዜ ተጠርቶአል። በብሉይ ኪዳን ይህ ስያሜ እስራኤልን ከጨቋኝ መንግሥታት ነጻ ያወጡትን መሳፍንት ለማመልከት የዋለባቸው ምንባባት ያሉ ቢሆንም (መሳፍንት 3÷9:15፤ 12÷3፤ ነህምያ 9÷27) ቃሉ ቢያንስ ስምንት ጊዜ እግዚአብሔር አብን ለማመልከት ውሎ ይገኛል። ከዚህ በስተቀር ይህ ስያሜ ለመላእክትም ሆነ ለሌሎች ሰማያዊ ፍጡራን ቃሉ ጥቅም ላይ ውሎ አይገኝም።

ቃሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ጥቅም ላይ የዋለባቸው ስፍራዎች የኢየሱስን አምላክነት የሚያስተምሩ መሆናቸው ቢያንስ ሦስት ትልልቅ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ***አንደኛ፣*** የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ የሚሉባቸው ምንባባት ኢየሱስ የፍጡራን ሁሉ አዳኝ/መድኀኒት መሆኑን በሚያሳይ መንገድ እንጂ እንደ እስራኤል መሳፍንት ከባዕድ ጨቋኞች ነጻ የሚያወጣ የሚያስተምር ብቻ አይደለም። በርግጥ ኢየሱስ እስራኤልን የሚታደግ አዳኝ ነው (ሐዋርያት ሥራ 13÷23) ነገር ግን ከዚህም በሚልቅ መልኩ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም አዳኝ ነው (ዮሐንስ 4÷42፤ 1ዮሐንስ 4÷14)። ኢየሱስ የሰብአውያን ሁሉ ሰማያዊ አዳኝ/መድኀኒት

104 "የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ" የሚለው ስያሜ በዕብራይስጡም ሆነ በአረማይስጡ ቅጅ ላይ አይገኝም። ከዚህም የተነሣ በአማርኛቹም ሆነ በእንግሊዝኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ላይ አይገኝም። G. K. Beale, *The Book of Revelation: A Commentary on the Greek Text,* NIGTC (Grand Rapids: Eerdmans; Milton Keynes, UK: Paternoster, 1999), 881.

ስለሆነ (*ፊልጵስዩስ* 3፥20፤ *ቲቶ* 2፥13)፣ *ሕዝቡን ከኀጢአትና ከሞት ነጻ ያወጣል* (*ሐዋርያት ሥራ* 5፥31፤ 2ጢሞቴዎስ 1፥10፤ *ቲቶ* 2፥14)።

**ሁ*ለተኛ፤*** ኢየሱስ ክርስቶስ *አዳኝ የተባለው፣ "እግዚአብሔር" (ግሪክ "ቴዎስ"* "θεὸς") *ወይም "ጌታ"* (*ግሪክ* "ኩርዮስ" "κύριός") *ከሚሉት ስሞች ጋር ተጣምሮ ነው፤ ይኸውም፣ "ጌታችንና መድኀኒታችን"* (2ጴጥሮስ 1፥11፤ 2፥20፤ 3፥2:18 *እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ሉቃስ* 2፥11፤ *ፊልጵስዩስ* 3፥20)፣ *"ታላቁ አምላካችንና መድኀኒታችን"* (*ቲቶ* 2፥13) *"አምላካችንና መድኀኒታችን"* (2ጴጥሮስ 1፥1)[105]። *በሐዲስ ኪዳን ምንባባት "መድኀኒት" የሚለው ስያሜ "ጌታ" ወይም "እግዚአብሔር" ከሚለው ስያሜ ጋር በጥምረት የቀረበ መሆኑ በብሉይ ኪዳን መድኀኒት የሚለው ስያሜ አብን የሚያመለክተው "ያህዌ" ከሚለው ስም ጋር ተጫፍሮ ነው* (*ዘዳግም* 32፥15፤ *መዝሙር* 25፥5፤ 27፥9፤ 62፥2:6፤ 65፥5፤ 79፥9፤ 95፥1፤ *ኢሳይያስ* 12፥2፤ 17፥10፤ 45፥15:21፤ *ሚክያስ* 7፥7፤ *ዕብራውያን* 3፥18) *ይህ ሁኔታ የሐዲስ ኪዳን ጸሐፍት ኢየሱስን "ጌታና መድኀኒት" ወይም "አምላክና መድኀኒት" የሚሉበት ስያሜ፣ ከብሉይ ኪዳኑ "ያህዌ" ጋር የሚነጻጸር ነው*።

**ሦ*ስተኛ፤*** *የሐዲስ ኪዳን ምንባባት ኢየሱስን አዳኝ ባሉበት ዐውድ ውስጥ እግዚአብሔር አብን አዳኝ ብለው ጠርተዋል። ለምሳሌ በቲቶ መጽሐፍ ውስጥ በተመሳሳይ ዐውድ አብ ሦስት ጊዜ "አዳኛችን" እንደ ተባለው ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስም ሦስት ጊዜ "አዳኛችን" ተብሎአል (ከዚህ በታች ያለወን ሰንጠረዥ ይመለከቷል)። አብ "አዳኝ" በተባለበት ዐውድ ውስጥ ኢየሱስ አዳኝ በማሉ ብቻ ሳይሆን አብ፣ "አዳኛችን እግዚአብሔር" እንደ ተባለ ሁሉ ወልድም "ታላቁ አምላካችንና አዳኛችን" ወይም "ጌታችንና አዳኛችን" ተብሎ መጠራቱ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በግልጽ የሚያሳይ ነው*[106]።

| **በቲቶ መጽሐፍ አብና ወልድ አዳኝ/መድኀኒት የተባሉባቸው ምንባባት** | |
|---|---|
| እርሱ በወሰነውም ጊዜ በአዳኛችን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ለእኔ ዐደራ በተሰጠኝ ስብከት በኩል ቃሉን ይፋ አደረገ **(1፥3)**<br><br>τοῦ σωτῆρος ἡμῶν θεοῦ | የጋራችን በሆነው እውነተኛ እምነት ልጄ ለሆነው ለቲቶ፤ ከእግዚአብሔር አብ፣ ከአዳኛችንም ከክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋና ሰላም ይሁን **(1፥4)**<br><br>Χριστοῦ Ἰησοῦ τοῦ σωτῆρος ἡμῶν |
| በሁሉም መንገድ የአዳኛችን የእግዚአብሔር ትምህርት ይወደድ ዘንድ ፍጹም ታማኝ መሆናቸውን እንዲያስመሰክሩ ነው **(2፥10)**<br><br>τοῦ σωτῆρος ἡμῶν θεοῦ | ይህም የተባረከ ተስፋችን የሆነውን የታላቁን የአምላካችንንና የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ በመጠባበቅ ነው **(2፥13)**<br><br>τοῦ μεγάλου θεοῦ καὶ σωτῆρος ἡμῶν Ἰησοῦ Χριστοῦ |

---

105 *ቲቶ* 2፥13 *እንዲሁም* 2ጴጥሮስ 1፥1 *ላይ ያቀረብነውን ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንታኔ ይመለከቷል።*

106 Larry W. Hurtado, *Lord Jesus Christ: Devotion to Jesus in Earliest Christianity* (Grand Rapids: Eerdmans, 2003), 515-16.

| በቲቶ መጽሐፍ አብና ወልድ አዳኝ/መድኀኒት የተባሉባቸው ምንባባት | |
|---|---|
| ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር በተገለጠ ጊዜ፣ (3÷4) | እግዚአብሔር በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእኛ ላይ አትረፍርፎ አፈሰሰው (3÷6) |
| τοῦ σωτῆρος ἡμῶν θεοῦ | Ἰησοῦ Χριστοῦ τοῦ σωτῆρος ἡμῶν, |

# VII. "እኔ" ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንታኔ

*"እኔ" የሚለው አመልካች ተውላጠ ስም፣ ስም እንዳልሆነ በግልጥ ይታወቃል። ነገር ግን ራሳችንን የምናመለክትበት እንዲሁም ስማችንን ተክቶ የሚገባ ቃል ነው። እግዚአብሔር ለአብርሃም ራሱን የገለጠው፣ "እኔ ኤልሻዳይ ነኝ" (ዘፍጥረት* 17÷1) *በማለት ነው። እግዚአብሔር ዐሥርቱ ትእዛዛትን ከመስጠቱም በፊት ራሱን ያስተዋወቀው "እኔ ነኝ" በማለት ነው፣ "ከግብፅ ከባርነት ምድር ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ" (ዘፀአት* 20÷2)። *በኦሪት ዘሌዋውያን* 19÷10-37 *ላይ ብቻ እግዚአብሔር አምላክ ዐሥራ ሦስት ጊዜ ያህል፣ "እኔ አምላክ ነኝ" ብሎአል።*

*አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር፣ "እኔ እርሱ ነኝ" ያለባቸው በርካታ የብሉይ ኪዳን ምንባባት አሉ። ዕብራይስጡ፣ "እኔ ነኝ" (ዕብራይስጥ "አኒ ሁ") የሚለውን ቃል የሰባዓ ሊቃናት ትርጉም "ኢጎ ኢሚ"* ("ἐγὼ εἰμί") *ይለዋል*[107]:—

> *"እኔ ራሴ እርሱ* [ὅτι ἐγώ εἰμι] *እንደ ሆንሁ እዩ፤ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም"*
>
> (*ዘዳግም* 32÷39)።
>
> *"ይህን የሠራና ያደረገ፣ ትውልድን ከጥንት የጠራ ማን ነው? እኔ እግዚአብሔር ከፊተኛው፣ ከኋለኛውም ጋር፣ እኔው ነኝ* [ἐγώ εἰμι]"
>
> (*ኢሳይያስ* 41÷4)።
>
> *"እስከ ሽምግልናችሁ፣ እስከ ሽበትም፣ የምሸከማችሁ እኔ ነኝ* [ἐγώ εἰμι]*፤ እኔው ነኝ። ሠርቻችኋለሁ፤ እሸከማችኋለሁ፤ እደግፋችኋለሁ፤ አድናችኋለሁ"*
>
> (*ኢሳይያስ* 46÷4)።

*በእነዚህ ስፍራዎች ላይ የሚገኘው፣ "እኔ ነኝ" የሚለው ቃል ከዘፀአት* 3÷14 *ጋር ያለውን ቀጥርነት ልብ ይሏል። "'እግዚአብሔርም ሙሴን፣ እኔ ያለሁና የምኖር ነኝ፤ ስለዚህም፣ 'ያለና የሚኖር' ልኮኛል ብለህ ንገራቸው አለው" (ዘፀአት* 3÷14)። *"ሄይ አሸር ሄይ" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል፣ በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም "ኢጎ ኢሚ ሆ ኦን"* (Ἐγώ εἰμι ὁ ὤν) *ተብሎ የተተረጐመ ሲሆን፣ "እኔ እኔ ነኝ" ወይም "ያለሁና የምኖር እኔ ነኝ"*[108] *ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። ይህም የእግዚአብሔር ያልነበረበት ጊዜ እንደሌለ፣ እርሱ የማይኖርበት ጊዜ*

---

[107] *"እኔ ነኝ" የሚለው ሐረግ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ያሳያል በሚለው ጉዳይ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣* Robert M. Bowman Jr., *Jehovah's Witnesses, Jesus Christ and the Gospel of John* (Grand Rapids: Baker 1989) *ይመለከቷል። ይህ መጽሐፍ በዮሐንስ* 1÷1 *እንዲሁም ዮሐንስ* 8÷58 *ላይ ብቻ የተጻፈ የዐቃቤ እምነት መጽሐፍ ነው።*

[108] "I am who I am" OR "I will be what I will be"

እንደማይኖር እንዲሁም ፍጥረታት ሁሉ እግዚአብሔርን ታምነውና ተመክተው እንደሚኖሩ በአንጻሩ ደግሞ እግዚአብሔር ከራሱ ውጪ ባለ በአንዳችም ነገር እንደማይመካ የሚያሳይ ነው:: በአራት ዘዳግምና በትንቢተ ኢሳይያስ መጻሕፍት ላይ ቃሉ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት እንዲሁም እግዚአብሔር ብቻ እውነተኛ አምላክ መሆኑን በሚያሳይ ትርጒሙ ጥቅም ላይ ውሎ ይገኛል[109]::

እጅግ ከፍተኛ ቊጥር ያላቸው የሐዲስ ኪዳን ምሁራን በዮሐንስ ወንጌል ላይ የሚገኙት፣ "እኔ" የሚሉት ቃላት በተለይ ከትንቢተ ኢያሳይያስ ጋር ተመሳሳይ ትርጒም እንደሚወክሉ ያስረዳሉ:: ለዚህ ጥሩ አስረጅ የሚሆነው፣ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ከኢሳይያስ 43÷10 ጋር ጠንካራ በሆነ ሁኔታ ተነጻጽሮ መገኘቱ እንዲሁም ኢየሱስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር በተነጋገረበት ጊዜ፣ "'የማነጋግርሽ እኮ እኔ እርሱ ነኝ' [Ἐγώ εἰμι] ሲል ገልጦ ነገራት" (ዮሐንስ 4÷26) የሚለው ቃል ሴቲቱ መሲሕ ሲመጣ ይህን ጒዳይ እንደሚገልጠው ስትናገር ኢየሱስ የተናገረው ንግግር ኢሳይያስ 52÷6 ላይ ያህዌ፣ "አስቀድሜ የተናገርሁ እኔ መሆኔን ይረዳል፤ እነሆ፤ እኔው ነኝ" የሚለውን ቃል የሚየሳስብ ነው (በእነዚህ ሁለቱ ምንባባት ላይ "'የማነጋግርሽ እኮ እኔ እርሱ ነኝ'" የሚለውን ቃል "አስቀድሜ የተናገርሁ እኔ ነኝ" ከሚለው ጋር ያነጻጽሯል፤ ከዚህ በታች ያለውን የንጽጽር ሠንጠረዥ ይመለከቷል)::

ኢየሱስ ይህን ንግግር በተናገረበት ጊዜ ንግግሩ በአድማጮቹ ዘንድ ያስተላለፈው መልእክት፣ የንጽጽሩን እውነተኝነት በግልጥ የሚያሳይ ነው:: ለምሳሌ በዮሐንስ 8÷58 ላይ፣ "ኢየሱስ፣ እውነት እላችኋለሁ፤ አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ" ሲላቸው አድማጮቹ በንግግሩ ግራ ሲጋቡ ሳይሆን፣ በአነገገሩ ሲበሳጩ እንመለከታለን (ቊጥር 25፣ 27፣ 59 ይመለከቷል):: በተለይ በቊጥር 58 ላይ፣ "ኢየሱስ፣ 'እውነት እላችኋለሁ፤ አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ'" ሲላቸው፣ ቊጥር 59 ላይ አድማጮቹ፣ "በዚያን ጊዜ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ" ይላል:: ለዚህ ዐቢይ ምክንያቱ ብሔረ ኦሪት፣ "የእግዚአብሔርን ስም የሚሳደብ ማንኛውም ሰው ይገደል፤ ማኅበሩ ሁሉ ይውገሩት፤ መጻተኛም ሆነ የአገር ተወላጅ የእግዚአብሔርን ስም ከሰደበ ይገደል" (ዘሌዋውያን 24÷16 እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ዘፀአት 22÷28፤ 1ነገሥት 21÷10:13) ስለሚል ነው:: በተመሳሳይ መንገድ ኢየሱስን ለመያዝ የመጡ ወታደሮችና የካህናት አለቆች ኢየሱስ፣ እርሱ "እኔ ነኝ" ሲላቸው፣ "ወደ ኋላ አፈግፍገው መሬት ላይ ወደቁ" ይላል (ዮሐንስ 18÷5-6)::

እንዲህ ካሉት መረጃዎች በግልጽ የምንረዳው ቊም ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ በእነዚህ ምንባባት ላይ፣ "እኔ ነኝ" ብሎ ሲናገር እንዲያው ራሱን ለማስተዋወቅ "አዎን እኔ ነኝ" ሲል የመለሰው መልስ ሳይሆን፣ ኢየሱስ ራሱን ከአብ ጋር በማነጻጸር አብ አምላክ እንደ ሆነው ሁሉ ኢየሱስም አምላክ መሆኑን የሚያስረዳ ነው::

| ኢሳይያስ<br>(በሰብዓ ሊቃናት ትርጒም) | ዮሐንስ ወንጌል |
|---|---|
| "አስቀድሜ የተናገርሁ እኔ መሆኔን ይረዳል፤ እነሆ፤ እኔው ነኝ" (52÷6)<br>***ἐγώ εἰμι*** αὐτὸς ***ὁ λαλῶν,*** | "ኢየሱስም፣ 'የማነጋግርሽ እኮ እኔ እርሱ ነኝ' ሲል ገልጦ ነገራት" (4÷26)<br>***'Εγώ εἰμι, ὁ λαλῶν*** σοι |
| "በውሃ ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ...ከአንተ | "እርሱ ግን፣ እኔ ነኝ አትፍሩ አላቸው" (6÷20) |

[109] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place,* 177.



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

| | |
|---|---|
| ጋር ነኝና አትፍራ" (43÷2:5)<br>***μὴ φοβοῦ,*** ὅτι μετὰ σοῦ ***εἰμι,*** | <br>Ἐγώ ***εἰμι· μὴ φοβεῖσθε.*** |

| ኢሳይያስ (በሰብዓ ሊቃናት ትርጕም) | ዮሐንስ ወንጌል |
|---|---|
| "ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ፣ እርሱ እኔ እንደ ሆንሁ ትረዱ ዘንድ፣ እናንተ ምስክሮቼ፣ የመረጥሁትም ባሪያዬ ናችሁ...እኔ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም ሌላ የሚያድን የለም...ነገር ግን የኀጢአት ሸክምህና ጫንህብኝ፤ በበደልህም አደከምኸኝ... " (43÷10:11:24)<br><br>ἵνα ***γνῶτε*** καὶ ***πιστεύσητε*** καὶ συνῆτε ὅτι ἐγώ εἰμι...***ἐν ταῖς ἁμαρτίαις σου*** | "በኀጢአታችሁ እንደምትሞቱ ነግሬአችኋለሁ፤ እኔ እርሱ ነኝ ስላችሁ እኔ እረሱ እንደ ሆንሁ ካላመናችሁ፣ በኀጢአታችሁ ትሞታላችሁ....ያ ያልሁት እርሱ እኔ እንደ ሆንሁና አብ ያስተማረኝን እንደምናገር፣ በራሴም ፈቃድ ምንም እንደማላደርግ ታውቃላችሁ" (8÷24:28)<br><br>ἐὰν γὰρ ***μὴ πιστεύσητε ὅτι ἐγώ εἰμι,*** ἀποθανεῖσθε ***ἐν ταῖς ἁμαρτίαις ὑμῶν...***τότε ***γνώσεσθε ὅτι ἐγώ εἰμι,*** |
| "ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ፣ እርሱ እኔ እንደ ሆንሁ ትረዱ ዘንድ፣ እናንተ ምስክሮቼ፣ የመረጥሁትም [ἐξελεξάμην] ባሪያዬ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር" (43÷10)<br><br>***ἵνα*** γνῶτε καὶ ***πιστεύσητε*** καὶ συνῆτε ***ὅτι ἐγώ εἰμι*** | "ስለ ሁላችሁ መናገሬ አይደለም፤ የመረጥኋቸውን [ἐξελεξάμην] ዐውቃለሁ...ሲፈጸም እኔ እንደ ሆንሁ ታምኑ ዘንድ፣ ይህ ከመሆኑ በፊት አሁን ነገርኋችሁ" (13÷18-19)<br><br>***ἵνα πιστεύσητε*** ὅταν γένηται ***ὅτι ἐγώ εἰμι.*** |

# VIII. "አማኑኤል" ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትንታኔ

ኢሳይያስ ምዕራፍ 7 እስከ 12 ያለው ክፍል የመሲሑን አምላክነት በግልጥ ከሚናገሩ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት መካከል አንዱ ነው። ክፍሉ በሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚመጣ እንዲሁም ይህ ፍርድ በእየሩሳሌምና በደቡቡ የእስራኤል መንግሥት ላይ የሚያስከትለውን እንድምታ በግልጽ የሚያሳይ ምንባብ ነው።

ይህ ክፍል በነቢዩ ኢሳይያስ ዘመን የአሶራውያን ግዛተ ዐፄ እስራኤልን ድል ስለመንሣቱ የሚናገር ቢሆንም፣ የኢሳይያስ ትንቢት በዘመኑ በነበረው ነባራዊ ሁኔታ ላይ ብቻ የሚያጠነጥን ሳይሆን፣ የዳዊትን ዘርዐ ሐረግ ተከትሎ ስለሚመጣው መሲሕ የመናገርም ምንባብ ነው፡—

> "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፣ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች"
>
> (ኢሳይያስ 7÷14)።

ይህ ምንባብ በይሁዳ ንጉሥ በአካዝ ዘመነ መንግሥት ስለተወለደውና አማኑኤል በሚል ስያሜ ስለሚጠራው ሕፃን ትንቢት የሚናገር ሲሆን[110]፣ ይህ "አማኑኤል" በሚል ስያሜ የሚጠራው ሕፃን ወደ ብስለት በሚደርስበት ጊዜ ("ክፉውን መተውና መልካሙን መምረጥ ሲችል"[111]) የአካዝ ሁለቱ ጥላቶች ማለትም አሶርና እስራኤል፣ "ባድማ" ይሆናሉ (7÷1-9:15-16)። "አማኑኤል" የሚለውም ስያሜ፣ አካዝ በጠላት በተከበበ ጊዜ እግዚአብሔር ከከበባው ነጻ እንደሚያወጣው ተስፋ የሚሰጥ ቃል ነው። ይህ በኢሳይያስ ዘመን የተወለደውና "አማኑኤል" በሚል ስያሜ የተጠራው ሕፃን፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌት ነው።

ምሁራን ኢሳይያስ 7÷14 አስመልክቶ ከፍተኛ ውዝግብ አላቸው። ዕብራይስጡ "አልማህ" የሚለውን ቃል የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም "ድንግል" ብሎ መተርጎሙ እንዲሁም ማቴዎስ 1÷23 ቃሉ ከሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ጋር በተዛመደ መልኩ "ድንግል" ማለቱ፣ የውዝግቡ ዐቢይ ምክንያት ነው። ይኸውም ማቴዎስ (1÷23) ኢሳይያስን (7÷14) በመጥቀስ፣ ድንግል እንደምትፀንስ ወንድ ልጅም እንደምትወልድ የተናገረው ትንቢት፣ የኢየሱስ እናት ማርያም በድንግልናዋ ኢየሱስን ፀንሳ እንደምትወልድ የሚያስረዳ ትንቢታዊ መልእክት ነው የሚለው ጉዳይ ነው። በዕብራይስጡ "አልማህ" የሚለው ቃል ወጣት የሆነች ልጅ ማለት እንጂ ድንግል ማለት አይደለም፤ በዕብራይስጥ ድንግል ለማለት ከተፈለገ፣ "አልማህ" ከሚለው ይልቅ "ቤቱላ" የሚለው ተመራጭ ቃል በቦታው ጥቅም ላይ ውሎ መገኘት ነበረበት የሚለው ሙግት ነው።

"አልማህ" የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል "ድንግል" ብሎ መተርጎም ስሕተት ነው በሚል ከነባሩ የቃለ እግዚአብሔር ትንተና ጋር መጣረስ ትክክል የማይሆንባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ:—

*(1)* "አልማህ" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል፣ ያላገባችን ወጣት ሴት ማመልከቱ እሙን ከሆነ፣ እስካላገባች ድረስ ድንግል መሆኗ ሊያከራክር አይገባም (ዘፍጥረት 24÷43፤ ዘፀአት 2÷8፤ መዝሙር 68÷25፤ ምሳሌ 30÷19፤ ማሕልየ 1÷3፤ 6÷8)። ለምሳሌ በዘፍጥረት 24÷43 ላይ፣ "አልማህ" የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም፣ "ድንግል" (ግሪክ "ፓርቴኖስ" "παρθένος") ሲል የተረጎመው ሲሆን፣ በሌሎቹ ክፍሎች ደግሞ "ኒያኒስ" (νεᾶνις) የሚለውን ቃል ተጠቅሞአል፤ "ኒያኒስ" ወጣት የሆነችን እንስት የሚያመለክት ሲሆን፣ ክብረ ንጽሕናን አመላካች ቃል ነው (እስካላገባች ድረስ ድንግል መሆኗ የግድ ይሆናል)። ለዚህም ነው በዕብራይስጥ ቋንቋ ላይ የተዘጋጁ መዝገበ ቃላት፣ "አልማህ ወጣት የሆነችን እንስት የሚያመለክት ሲሆን፣ የዚህም አንዱ ባሕርይ ድንግልና ነው"[112] የሚሉት።

*(2)* ክፍሉ ከጊዜው ነባራዊ ሁኔታ ያለፈ ትንቢታዊ የሆነ ጥልቅ መልክት አለው ለሚለው ድምዳሜ ሌላው ማስረጃ፣ ኢሳይያስ ሕፃኑ ስለመወለዱ ትንቢት ከመናገሩ በፊት አካዝን፣

---

[110] በዚህ ዐውድ አማኑኤል የተባለው የነቢዩ ኢሳይያስ ልጅ፣ መኸር-ሻላል-ሃሽ-ባዝ ሊሆን ይችላል 8÷3:8:10።

[111] ይህ በ12 እና በ13 ዕድሜ ክልል ሲደርስ ማለትም 722 ወይም 723 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው የአዲሱ መደበኛ ትርጉም የጥናት መምሪያ ይመለከቷል።

[112] Allan A. MacRae, *The Theological Wordbook of the Old Testament,* ed. R. Laird Harris, Gleason L. Archer Jr., and Bruce K. Waltke (Chicago: Moody Press, 1980), 2:672.



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

"ከጥልቁ ጥልቅ ወይም ከከፍታው ከፍታ ምልክት እንዲሰጥህ ከእግዚአብሔር ከአምላክህ ለምን" (ኢሳይያስ 7÷11) የሚለው አነጋገር፣ እግዚአብሔር የዳዊትን ሥልጣነ ንግሥና እንደሚጠብቅ ተኣምራዊ የሆነ ትእምርት/ምልክት እንደሚሰጥ የሚያሳይ ነው (ኢሳይያስ 7÷10-14)። ይህም "የአማኑኤል" ውልደት ፍጹም ተኣምራዊ እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው (ኢሳይያስ 38÷7-8)።

(3) የኢሳይያስ ትንቢት ነቢዩ ባገለገለበት ማለትም ከ701 እስከ 681 ዓ.ቅ.ክ በሉት ጊዜያት ተፈጥሮአዊ በሆነውና በተለመደው መልኩ ስለተወለደ አንድ ብላቴና የሚናገር ትንቢት ላለመሆኑ በዚሁ ዐውድ ውስጥ ኢሳይያስ የሚሰጠው ማረጋገጫ ሌላው ምስክር ነው:—

> "ሕፃን ተወልዶልናል፤ ወንድ ልጅ ተሰጥቶናል፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም፣ ድንቅ መካር፣ ኀያል አምላክ የዘላለም አባት፣ የሰላም ልዑል ይባላል። ለመንግሥቱ ስፋት፣ ለሰላሙም ብዛት ፍጻሜ የለውም፤ ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፣ መንግሥቱን በፍትሕና በጽድቅ ይመሠርታል፤ ደግሞ በመያዝም ያጸናዋል። በዳዊት ዙፋን ይቀመጣል፤ አገሩንም ሁሉ ይገዛል፤ የሰራዊት ጌታ አግዚአብሔር ቅናት ይህን ያደርጋል"
>
> (ኢሳይያስ 9÷6-7)

የዚህ ምንባብ ዐውድ፣ ከኢሳይያስ 7÷14 ዐውድ ጋር አንድ ነው። የኢሳይያስ 7÷14 እና የኢሳይያስ 9÷6-7 ዐውድ እግዚአብሔር አሦራውያንን በመጠቀም የሰሜኑን የእስራኤል ግዛት ቢቀጣም እንዲሁም ይህ ፍርድ በተወሰነ ደረጃም እንኳ ቢሆን ይሁዳን የሚነካ ፍርድ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ኪዳኑን በመጠበቅ ዘላለማዊ የሆነውን የዳዊትን ዙፋን እንደሚያጸና የሚናገር ዐውድ ነው። ሁለቱም ምንባባት እግዚአብሔር "ሊሰጥ" ስላለው "ሕፃን" እና "ወንድ ልጅ" የሚናገሩ ከመሆናቸውም ባሻገር ሕፃኑ፣ "አማኑኤል" በሚል ስያሜ እንደሚጠራ ይህም የእግዚአብሔርን ህልዎት የሚያስረግጥ ነው። ስለዚህ ኢሳይያስ 9÷6-7 ያለው ትንቢት፣ "አማኑኤል" ተብሎ ስለሚጠራው ሕፃን ተጨማሪ መረጃዎችን የሚሰጠን ነው። ይህ ሕፃን በዳዊት ዙፋን ላይ ለዘላለም መቀመጡ (ኢሳይያስ 9÷7) ከዳዊት ዘር የሚመጣውን መሲሕ መመልከቱ እርግጥ ይሆናል።

በአጠቃላይ ኢሳይያስ 7÷14 እና ኢሳይያስ 9÷6-7 ይህ ሕፃን አምላክ እንደ ሆነ በግልጽ የሚያስተምሩ ናቸው። ኢሳይያስ 7÷14 ሕፃኑ፣ "አማኑኤል" (ይህ በማቴዎስ 1÷23 መሠረት፣ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ማለት ነው) ተብሎ እንደሚጠራ የሚናገር ሲሆን፣ ኢሳይያስ 9÷6-7 ደግሞ ሕፃኑ፣ "ድንቅ መካር"፣ "ኀያል አምላክ"፣ "የዘላለም አባት"፣ "የሰላም ልዑል" እንደ ሆነ ይገልጻል [ዕብራይስጡ ኤልጊቡር የሚለው ሲሆን፣ እግዚአብሔር አብ ራሱ በዚሁ ዐውድ "ኤልጊቡር" (ኢሳይያስ 10÷21) ተብሎ መጠራቱን ልብ ይሏል] እንዲሁም "ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፣ መንግሥቱን በፍትሕና በጽድቅ ይመሠርታል፤ ደግሞ በመያዝም ያጸናዋል" (ቍጥር 7) የሚለው ትንቢት በነቢዩ ኢሳይያስ ዘመን የተወለደው ሰብአዊ ሕፃን፣ አምላክነትን የሚያሳዩ የእነዚህ ስሞች ሁሉ ባለቤት ነው ማለት በፍጹም የሚቻል አይደለም—"ኾድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" ካልሆነ በስተቀር።

ነቢዩ ኢሳይያስ መጻኢው መሲሕ፣ "ኀያል አምላክ" መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር አምላክ ሕዝቡን ለመታደግ፣ ለማደስና ለመምራት እንደሚመጣ በግልጽ ተናግሯል (ኢሳይያስ 40÷9-11፤ 43÷10-13፤ 59÷15-20)። ለምሳሌ:—



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው

*የዐዋጅ ነጋሪ ድምፅ እንዲህ ይላል፤*
*የእግዚአብሔርን መንገድ፣ በምድረ በዳ አዘጋጁ፤*
*ለአምላካችን አውራ ጐዳና፣ በበረሓ አስተካክሉ*
(ኢሳይያስ 40÷3)

*የሚለውን ይህን የኢሳይያስ ክፍል ምስስለ ወንጌላት መንገድ የሚያዘጋጀው መጥምቁ ዮሐንስ እንደ ሆነ የሚያዘጋጀውም መንገድ የጌታ ኢየሱስ መሆኑን ያስረዳሉ (ማቴዎስ 3÷3፤ ማርቆስ 1÷3፤ ሉቃስ 3÷4-6)። ይህ ደግሞ መልእክተኛውን የሚልከው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ያስተምራል።*

# ማጠቃለያ

*አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ አምላካዊ ስም ባለቤት መሆኑ አምላክ መሆኑን የሚያመለክት አይደለም ለሚለው ሐሳባቸው የሚያቀርቡትን የተለያዩ ሙግቶች በጥናታችን መጀመሪያ ላይ መመልከታችን ይታወሳል። ለሚያቀርቧቸውም ሙግቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊና ምክንዮአዊ የሆነ መልስ የሰጠን ይመስለናል። ምናልባት በጀማሮው ላይ ያላቀረብነው ነገር ግን ቢያንስ በማጠቃለያው ላይ ማቅረብ ያለበን አንድ ሙግት የሚከተለው ነው፦*

*በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አንዳንድ ሰዎች፣ "አምላካዊ የሆነ ስም"[113] ባለቤት የሆኑበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ "ኤልያስ" የሚለው ስም የ"ኤል" እና የያህዌ አጭር ንበት የሆነው "የያህ" ጥምረት ነው። ነገር ግን ኤልያስ አምላክ እንዳልሆነ እሙን ነው። ልክ እንደዚሁ ሁሉ በትንቢተ ኤርምያስ ላይ ለሴዴቅያስ (ምንም እንኳ እንደ ስሙ ባይኖርም) ኋላም መሲሑ፣ "እግዚአብሔር ጽድቃችን" ተብለው እንደሚጠሩ ይናገራል (ኤርምያስ 23÷6)። ልክ እንደዚሁ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "አማኑኤል" (እግዚአብሔር ከእኛ ጋር) መባሉ (ኢሳይያስ 7÷14) እንዲሁም የሐዲስ ኪዳን ምንባባት ኢሳይያስን ጠቅሰው ቢጽፉም ስሙ መጀመሪያ የተሰጠው ማኸር ሻላል ሃሽ ባዝ ኢሳይያስ 8÷3 ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ የሚያመለክተው ሰብአውያን ራሳቸው አምላክ በተጠራበት ስም እንደ ተጠሩ ቢያሳይም ከተጠሩበት ስም ተነሥተን አምላክ ናቸው ማለት እንደማንችለው ሁሉ፣ ኢየሱስም አምላካዊ ስም ባለቤት መሆኑ አምላክነቱን አያሳይም ለሚለው ሙግት መልስ አለን[114]። መልሳችንም እነሆ፦*

*(1) እነዚህ ስሞች ትንቢታዊ በሆነ መልኩ መሲሑ ኢየሱስን የሚያመለክቱ እንጂ ግለሰቦቹን የሚያሳዩ አይደሉም። (2) ኢየሱስ እንዲያው ለመጠሪያነት የተሰጠው ቴዎፎሪክ ስም ሳይሆን፣ ስሞቹ በተገለጹበት ዐውድ ሁሉ እነዚህ ስሞች አምላካዊ ባሕርይውን፣ አምላካዊ ክብሩን፣ አምላካዊ ሥራውን እንዲሁም አምላካዊ መንበሩን የሚያሳዩ ናቸው። (3) እነዚህ ስሞች ለአብ በተሰጡበት ተመሳሳይ ዐውድ ውስጥ ለኢየሱስ ተሰጥተው መገኘታቸው እንዲሁም ሃይማኖታዊ አምልኮን፣ ክብርን ወዘተ በሚያሳይ መልኩ ለኢየሱስ መዋላቸው አምላክነቱን ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ይሆናሉ።*

---

[113] ይህ በነገረ መለኮቱ ዓለም፣ "ቴዎፎሪክ" (theophoric) ስም በመባል ይታወቃል።

[114] Bowman and Komoszewski, *Putting Jesus in His Place,* 272 ከTimo Eskola, *Messiah and the Throne: Jewish Merkabah Mysticism and Early Christian Exaltation Discourse,* WUNT 2.142 (Tübingen: Mohrsiebeck, 2001), 139-142. ጠቅሰው እንደ ጻፉት።

**በ**አጠቃላይ ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔር አብን አምላክ በሚሉበት ዐውድ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ማለታቸው (ዮሐንስ 1÷1:18፤ 20÷28፤ ሐዋርያት ሥራ 20÷28፤ ሮሜ 9÷5፤ ቲቶ 2÷13፤ 2ጴጥሮስ 1÷1፤ ዕብራውያን 1÷8፤ 1ዮሐንስ 5÷20) ወይም የብሉይ ኪዳን ምንባባት አብን "ያህዌ" (የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም "ጌታ") በሚሉበት ትርጉሙ በሐዲስ ኪዳን ምንባባት ኢየሱስ "ጌታ" መባሉ (ለምሳሌ:— ሮሜ 10÷9-13፤ 1ቆሮንቶስ 8÷6፤ ፊልጵስዩስ 2÷9-11፤ 1ጴጥሮስ 3÷13-15) እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አብ "የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ"፣ (ለምሳሌ:— ራእይ 17÷14፤ 19÷1)፣ "አዳኝ/መድኀኒት" (ቲቶ 2÷13፤ 2ጴጥሮስ 1÷11)፣ "እኔ" (ዮሐንስ 8÷24:28:58)፣ "አልፋና ዖሜጋ" (ራእይ 1÷7-8:17-18፤ 2÷8፤ 22÷12-13) ወዘተ መባሉ አምላካዊ ባሕርይውን የሚያሳይ ነው። የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የኢየሱስ ክርስቶስ ስም የክርስትና እምነት ታሪካዊ ዐለት እንደ ሆነ በተደጋጋሚ ከማስተማራቸውም በላይ ኢየሱስ ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ ስም እንዳለው በግልጽ ያስተምራሉ (ኤፌሶን 1÷21፤ ፊልጵስዩስ 2÷9-11፤ ቈላስይስ 3÷17)።



ይህን ጽሑፍ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው